**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2020-11-04

# þÿ%• a“Ê u ``Í@q 5é `¥•E M ¥“ þÿM«, a“Ê •ce

þÿ • í È•ñ+ô

http://hdl.handle.net/123456789/11523

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂውማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ- ትምህርት ክፍል

# ሥነልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም *በእንቅልፍ እና እድሜ*፤

ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ

በ

አንለይ ወንዲራድ

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

ባሕር ዳር

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ፡-አማርኛ-ትምህርት ክፍል

# ሥነ ልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም በእንቅልፍ እና እድሜ፤ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፤ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ

አማርኛ-ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

አማርኛ ሥነ ጽሑፍ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

በ፡-

አንለይ ወንዲራድ

አማካሪ፡-ዶ/ር ተስፋየ ዳኘው (ተ/ፕሮፌሰር)

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

ባህር ዳር

# መግለጫ

ይህ "ሥነልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም እንቅልፍ እና እድሜ፣ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ" ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲ ፋኩሊቲ፣

ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ቴሲስ ሲሆን

ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሙያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

አንለይ ወንዲራድ ሐምሌ /2012 ዓ/ም ባህር ዳር

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ- ትምህርት ክፍል

### የቴሲስ ፈተና ውጤት ማረጋገጫ

እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘሩት የፈተና ቦርድ አባላት "ሥነ ልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም እንቅልፍና እድሜ፣ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ" የሚለውን የማስተር ቴሲስ ፈትነን-------------- ውጤት በጋራ ተስማምተን አጽድቀናል፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| ------------------------------- | ------------- | ------------------------ |
| **የውጭ ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| -------------------------------- | --------------- | -------------------------- |
| **የውስጥ ፈታኝ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ----------------------- | -------------- | --------------------- |
| **የፈተናው ሰብሳቢ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |

# ምስጋና

ከነሙሉ አካሌ ፈጥረህ በጥሩ ሁኔታ አሳድገህ ለአስራ ስምንት ዓመት ከቆየሁበት የእርሻ ስራ አውጥተህ እንድማር እና ለዚህ እንድበቃ ላደረከኝ አምላኬና ፈጣሪዬ ክብር ምስጋና ላንተ ይሁን፡፡

መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ተስፋዬ ዳኘው ይህ ጥናት የተሳካና ምሉዕ እንዲሆን የምልከውን ረቂቅ በማረምና በማስተካከል የተሻለ ሃሳብ በማመላከት በቅንነት የተሞላ እገዛ በእግዚአብሄር ስም ላቅ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ትምህርቴን በግሌ እንድጀምር ላነሳሳችሁኝ፣ ከጀመርኩት በኋላም በገንዘብ ፣በቁሳቁስ፣ በሃሳብ ላበረታታችሁኝ፣ በቂ ጊዜ አጥቼ ስቸገር የስራ ሰዓትም ጭምር በመፍቀድ፣ልዩ ልዩ አስተዋፅዖ ላበረከታችሁ የስራ ባልደረቦቼ፣ ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ፣ በተለይም ለባለቤቴ ወ/ሮ የሺ ካሳ እና ለልጆቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ደስ ብሎኛል ደስ ይበላችሁ፡፡

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት "ሥነ ልቡናዊ ሞት በበውቀቱ ስዩም* በእንቅልፍ እና እድሜ *፤ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በሚል ርዕስ የተደረገ ነው፡፡ ጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ሞት የቀረበባቸውን ጉዳዮች መተንተን የሚል ዋና ዓላማን መሰረት አድርጎ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ ለጥናቱ ማያነት የተመረጠው ደግሞ የሲግመንድ ፍሮይድ ፍካሬ ልቦና (Psychoanalysis) ሲሆን ለትንተና የተመረጠው ዘዴ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብን ተጠቅሞ የሃቲት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ የሃቲት ትንተና ደግሞ የመተንተኛ ስልትም ነው ፡፡ ፍርሃት፣ጭንቀት ፣ተስፋ መቁረጥ እና የዝቅተኝነት ስሜት የሥነ ልቡናዊ ሞት ጭብጦች* ***በመሆን*** *አገልግለዋል፡፡*

*ገጸ ባህሪያቱን ላልተፈለገ ሥነ ልቡናዊ ጫና የሚያጋልጧቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ሁኔታዎች ሲታዩም በጥናቱ እንደተረጋገጠው የኢኮኖሚ ጥገኝነት፣ የከፋ የልጅነት አስተዳደግ ፣ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት እና የቤተሰብ ሞት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የገጸ ባህርያቱ የመጨረሻ እጣ ፈንታም ሲታይ ከህገ ልቡናና ከማህበረ ልቡና እየተፋቱ ለሞት፣ ለብቸኝነትና ለስደትና እየተጋለጡ ከማህበራዊ ኑሯቸው እየተፈናቀሉ ራዕያቸውን እየተነጠቁ ከንቱ ሁነው ሲቀሩ ጥናቱ ያሳያል ፡፡*

*በመሆኑም* በእንቅልፍና እድሜ' *ልብ ወለድ ውስጥ ባሉ ታሪኮች የሚገኙት ገጸባህሪያት በፍርሃት፣ በጭንቀት፣ በቀቢጸ ተስፋ እና ለራሳቸው በሚሰጡት ዝቅተኛ ክብር አጠቃላይ ሥነ ልቡናዊ ማንነታቸው ያነከሰ፣ በዙሪያቸው ለሚከሰት ሥነ ልቦናዊ ጫና የተጋለጡ፣ የራሳቸውን ማንነት አጥተው በአዲስ ማንነት ውስጥ የገቡና ከገቡበት ያልነበረ ማንነት ለመውጣት ከጫፍ ጫፍ የሚረግጡ ነገር ግን የማይሳካላቸው እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል ፡፡*

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........................................ i

አጠቃሎ ........................................ ii

ማውጫ ........................................ iii

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

መግቢያ ........................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ........................................ 4

1.3.1. ዋና ዓላማ ........................................ 4

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........................................ 4

1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች ........................................ 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 5

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................ 5

1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................ 6

1.7.1. የቴክስት (ልብወለድ) አመራረጥ መስፈርት ........................................ 6

1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ 6

1.7.3. የመረጃ አተናተን ዘዴና ሂደት ........................................ 7

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ........................................ 7

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 9

2 . ንድፈ ሀሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 9

2.1. ፍካሬ ልቡና /psychoanalysis/ ........ 9

2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........ 12

2.2.1. ሞት /Death/ ........ 12

2.2.2. የሞት ፍርሀት /Fear of Death/ ........ 14

2.2.3. የስነ ልቡና ቀውስ /Psychologicale Disturbance/ ........ 20

2.3. የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ........ 25

ምዕራፍ ሦስት ........ 33

3 የሥነ ልቡናዊ ሞት ጭብጦች ትንተና ........ 33

3.1. የልብ ወለዱ አጽመ ታሪክ ........ 33

3.2. ፍርሃት/Fear/ ........ 35

3.3. ጭንቀት /Anxiety/ ........ 42

3.4. ቀቢፀ ተስፋ /Despair ........ 50

3.5. ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምት /Low self Esteem/ ........ 56

ምዕራፍ አራት ........ 60

ማጠቃለያ ........ 60

ዋቢ ጽሑፎች ........ 62

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ሥነ ጽሑፍ ማለት እውነትን፣ህይወትን እና ውበትን አጠቃሎ የሚይዝ በሰዎች ለሰዎች ስለሰዎች የሚፃፍ ነው (ዘሪሁን ፣1992) ፡፡ ይህ ማለት በሰዎች ህይዎት ውስጥ የሚፈጠሩ የሰው ልጅ ባህሪያት ወይም ጠባያት መገለጫ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በደራሲው የምናብ ነጻነት ኪናዊ ውበት ተላብሰው በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ነው፡፡ ከነዚህ የሰው ልጅ የባህሪ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ሞት ነው፡፡

ሞት የነገረ ህላዌ መገለጫ ጭብጦች ከሆኑት (የርዕይ መነጠቅ ፣ ቀቢጸ ተስፋ ፣ራስ ውንጀላ ፣ ባይታወርነት፣ ግዞት እና ባዛናነት) አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በጭብጦቹ መካከልም ጥብቅ የሆነ ተዋረዳዊ ግንኙነት አንዳለ፡፡ እነዚህ ጭብጦች አንዱ ከሌላው ይዛመዳሉ፡፡ ይዋለዳሉ፡፡ ተዋረዳዊ የሚመስል ግንኙነትም በመካከላቸው እንዳለና በዚህ ተዋረድ ውስጥ ደግሞ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ እጣ የሆነው ሞት ትልቁን ስፍራ እንደሚይዝ (ቴዎድሮስ፤2001) ገልጸዋል፡፡

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለው ሞት "የሟች ማንነት፣ የአሟሟቱ እንዴትነት ፍች ይለውጣል፡፡ በየልቦለዱ ውስጥ የሚታየው ምስቅልቅል ምንጩ ሞት ነው" የነገረ ህላዌ ትራጅዲያዊ ገጽታ መገለጫ የሆኑት ተዋረዳዊ ትስስር አላቸው፡፡ በዚህ ትስስር ውስጥ ሞት የበላይነት አለው፡፡ ሞት የበለይነቱን ከያዘ ደግሞ ባላቸው ተዛምዷዊ እና ተዋለዳዊ ግንኙነት የሞት መገለጫ ባህሪ ከመሆን የሚያግዳቸው ምንም አይነት ምክንያት የለም፡፡ዝኒ ከማሁ

ሥነ ጽሑፍ ከዋነኛ ግቡ ከተዝናኖት ፈጠራ ባሻገር ለእውቀት ምንጭነትና ለእውቀት ሽግግር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ እጅግ በርካታ የእውቀት ዘርፎች ሥነጽሑፍን ምንጫቸው አድርገው ፈልቀዋል፡፡ ለዚህም ራሱን ሥነጽሑፍን፣ ታሪክንና ሥነምግባርን መጥቀስ የሚቻል ሲሆን እነዚህ የእውቀት ዘርፎች ሥነ ጽሑፍን መነሻቸው አድርገው በውስጡ በሚመዘዙ ንዑሳን መርሆዎች ዙሪያ የንድፈ ሃሳባቸውን አጥር ያጠሩ የእውቀት ዘርፎች ናቸው ፡፡(ቴዎድሮስ፣2001) ሌሎች ደግሞ ያላቸውን ንድፈ ሃሳባዊ እውቀት ከትውልድ ትውልድ ለማሻገር ሥነ ጽሑፍን የተጠቀሙ ወይም ለንድፈ ሃሳባቸው ማብራሪያነት ለእውቀታቸው ማሳያነት ሥነ ጽሑፍን የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ሥነ ጽሑፍ

የማይዳስሰው ሥነ ጽሑፍ የማይነከው የእውቀት ዘርፍ ማግኘት እንደሚያስቸግር ብዙወች ይስማማሉ፡፡ /ዝኒ ከማሁ/

ሥነጽሑፍን ለመረዳትና ለመተንተን ከሚያስችሉ በርካታ የእውቀት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ፍክሬ ልቡና ነው፡፡ ፍካሬ ልቡና የአዕምሮ ህሙማንን ያለፈ የህይዎት ታሪክ በማጥናትና ህልማቸውን በመፍታት ህሙማንን ለማከም ፍሮይድ ይጠቀምበት እንደነበረ የዘርፉ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ በተለይም ፍካሬ ልቡና ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ መረጃዎችን ከማስገኘት ባለፈ የሰው ልጅ በልጅነት ዘመኑ በኢ-ንቁ አዕምሮ ታምቆ (repressed) ሆኖ ያለፈ ፍላጎት በኋለኛው የህይዎት ዘመን የሚንጸባረቅባቸውን መንገዶችና የሚያስከትለውን ውጤት በመተንተን ተጠኝዎችን ለመርዳት አገልግሎት ላይ ይውል ነበር (Green and Bihan1996;144)፡፡

በፍካሬ ልቡና ንባብ በሥነጽሑፍ ውስጥ ከሚጠኑት በርካታ ጉዳዮች አንዱ ደግሞ ሞት ነው፡፡ ሞትን ሥነ ሕይወታዊ ፣ ሥነ ልቡናዊ ሞት እና ሥነ ምግባራዊ ሞት እያሉ ከፋፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ሥነ ልቡናዊ ሞት ላይ የተደረገ ነው፡፡ የሰው ልጅ የባህሪ መገለጭ ከሆኑት አስፈሪ፣ አስደንጋጭ፣ አሳዛኝ ፣ ተስፋ አስቆራጭ በአጠቃላይ ከተለመደ ባህሪ ውጭ የሆኑ ረቂቅ ጉዳዮች ጋር የሚታይና በሌላ በኩል ሥነሕይወታዊ ሞትን እና የራስ የሆነ ወይም የነበረ ነገርን ከማጣት ወይም መገለልን መነሻ በማድረግ በሟች ላይ ብቻ ሳይሆን በሟች ቤተሰቦች ላይ የሚከሰት የሞት ፍርሃት እና የሥነ ልቡና ቀውስ ስለሚፈጥረው ሥነልቡናዊ ሞትን መሰረት ተደርጎ የተጠና ነው፡፡

እንግዲህ በዚህ ጥናት ለማየት የተሞከረው ለጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ እነዚህ የሰው ልጅ የሥሜት እና የባሕሪያት መገለጫዎች በምን መንገድ እንደተገለጹ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ የሃቲት ትንተና ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በሥነ ልቡናዊ ሞት የሰው ልጅ የስሜት ጣጣ እና የባህሃሪ መገለጫዎች ናቸው በሚል ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ቀቢጸ ተስፋ እና ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር የሥነ ልቡና ሞት ጭብጦች በሚል ተለይተው ትንታኔው የሚታይባቸው ይሆናሉ፡፡ እነዚህ የሥነልቡና ሞት መገለጫዎች ናቸው ሲባል ሞትን የሚገልጹት በሁለት መንገድ ነው ፡፡ አንደኛው ሞትን በመፍራት /Fear of Death/ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሥነ ልቡና ቀውስ /Psychological disturbance/ በመፍጠር ነው፡፡ በገጸባህሪያቱ ላይ የሚታየው የሥነልቡና ቀውስ

መጨረሻው ሲታይ ገጸባህሪያቱን ከነበረ ማንነታቸው አስወጥቶ ለስነ ልቡናዊ ሞት ሲያጋልጣቸው የሚታይ በመሆኑ የሥነልቡና ቀውስ የሥነ ልቡናዊ ሞት መገለጫ ነው በሚል ለጥናቱ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ አጥንዖቱ የኔ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን የምርምር ርዕሰ ጉዳይ እንድመርጥ ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት  የደራሲ በእውቀቱ ስዩምን የአፃፃፍ ስልት፣ የይዘት ትኩረት እና የህይወት ፍልስፍና ዙሪያ ስራዎቹን በተደጋጋሚ የማንበብ እድሉ ነበረኝ፡፡ በሁሉም ስራዎቹ ውስጥ ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር፣ የጥፋተኝነት ስሜት፣ ተስፋ ቆራጭነት፣ ራስን የማጥፋት እሳቤ በስፋት ይታይበታል ፡፡ በዚህ ጊዜ ድርሰቶቹ የያዙትን ጉዳይ ሳይሆን ከሥነልቡናዊ ሞት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥልቀት እንዳይ አደረገኝ፡፡ ይህ ሀሳብም ድርሰቶቹን በጥልቀት ለመረዳት የጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ አድርጌ እንድመርጠው እና እነዚህ ጉዳዮች ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ በጥልቀት ቢጠኑ የድረሰቱን ትርጉም በጥልቀት ለመረዳት ፤የሥነጽሑፍ ጥበቡን በማጉላት  አንዳች ፋይዳ ያበረክታል የሚል እምነት  ስለአለኝ ነው፡፡

የበእውቀቱ ስዩም ስራ የሆነው እንቅልፍ እና እድሜ(1999) ልብወለድ "መውረድና መውጣት"፣ "ማየትና መጋረድ" እና "መቅረብና መራቅ" የሚሉ ሦስት ተከታታይ ክፍሎች ያሉት ነው፡፡ ልብወለዱ የተለያዩ ታሪኮችና ገጸባህሪያትን የያዘ ቢሆንም ተከታታይ ክፍሎችን መያዙ አንድ የሚያመሳስል ነገር እንዳላቸው ስለሚያመላክት ከረጅም ልቦለድ ዘውግ የሚመደብ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ያሉት ርዕሶች ሁለት ተቃራኒ (binary opposites) ሃሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል  ሁለት ሁለት አቢይ ገጸባህሪያት አሉ፡፡ አቢይ ገጸባህሪያቱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሲሆኑ ሁሉም በፍቅር የተሳሰሩ አብረው ለመኖር የሚጀምሩ ግን በሞት በስደትና በሽሽት ፍቅራቸው ወይም አብሮ የመኖር ህልማቸው  የሚቋረጥ ለፍሬ የማይበቃ ህይዎት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በገጸ ባህውሪያቱ ላይ የሚታየው የሥነ ልቡና ቀውስ እና የሞት ፍርሃት ከርዕሰ ጉዳዮቹ ተቃራኒ ሀሳብ አንጻር በፍካሬ ልቡናዊ ንባብ ቢጠኑ የርዕሰ ጉዳዮቹን የተቃርኖ ሚስጢር ከልብወለዱ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ይጠቅማል ከሚል እምነት ጭምር ነው፡፡

ፍካሬ ልቡና ንባብ መሰረት ተደርጎ የተጠኑ የቴዎድሮስ አለበል "ልጅነት በማህሌት አለንጋና ምስር ሥነ ልቡናዊ ንባብ" ፤የኢዩኤል እንደሻው "ድብቅ ባህሪያት እና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ሥነ ልቡናዊ ንባብ" የገብሬ ባይሌ "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በእሳት ዳር

አበቦች፣ ኗሪ አልባ ጎጆዎች እና የማለዳ ድባብ የግጥም መድበሎች" ቢኖሩም እኔ ያየዋቸው ልጅነትን፣ ህልውናዊነትን፣ ድብቅ ባህሪያትን፣ ባይታዎርነትን መሰረት ተደርገው የተጠኑ ሲሆኑ ሁሉም በሚባል ደረጃ ሞትን በርዕሰ ጉዳያቸው እንደ አንድ ጭብጥ በመውሰድ የተጠኑ ሲሆኑ ትኩረት ሠጥተው ያዩት ሥነሕይወታዊ ሞትን ነው፡፡ በመሆኑም ሞት ካለው ሰፊ ትርጉም አንጻር ራሱን ችሎ የተደረገ ጥናት ባለማግኜቴ ፤ ለጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ሞትን የሥነ ልቡና መከሰቻ ጣጣዎች ከሚባሉት ሥነ ህይወታዊ ሞት፣ የገንዘብ ማጣት ፣የፍቅር ማጣት፣ያልተገባ የልጅነት አስተዳደግ፣ ወሲብ ፣ፍርሃት፣ጭንቀት የመሳሰሉት ሰዋዊ ባህሪያት ስለሚንጸባረቁ በፍካሬ ልቡናዊ ንባብ ማየትን ርዕሰ ጉዳይ አድርጌ እንድመርጠው አነሳስቶኛል፡፡

በመሆኑም በድርሰቱ ውስጥ የሚታዩት የሰው ልጅ የስሜትና የባህሪ መገለጫ ጣጣዎች በድርሰቱ ገጸ ባህሪያት ላይ እያሳደሩት ያለው ውስጣዊና ውጫዊ ተጽእኖ በፍካሬ ልቡና ንባብ ቢጠኑ ለጥበቡ ማደግ የጎላ ሚናም ይኖረዋል ከሚልም እምነት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት ዋና እና ዝርዝር ዓለማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

### 1.3.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍ እና እድሜ (1999) ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ሞት ከሰው ልጅ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ግንኙነት ማሳየት ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት ፤

1. ከላይ በተጠቀሰው ልብ ወለድ ለሥነ ልቡናዊ ሞት መከሰት መንስኤ ሊሆኑ የቻሉትን ሰብዓዊ ባህሪያት መመርመር

2. የሥነ ልቡና ቀውስ በልብወለዱ ውስጥ የሚገኙ ገጸባህሪያትን እንዴት ለሥነ ልቡና ሞት እንደሚያጋልጣቸው መመርመር

3. በተመረጠው ቴክስት ውስጥ ከሚገኙ ገጸባህሪያት ለሥነልቡናዊ ሞት የሚጋለጡትን መለየትና መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች

ለጥናቱ በተመረጠው እንቅልፍ እና እድሜ ልብ ወለድ ውስጥ በሚደረገው ምርምር መልስ ያገኛሉ ተብለው የሚታሰቡት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. በተመረጠው ልብ ወለድ ውስጥ ለሥነ ልቡናዊ ሞት መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የቻሉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
2. የሥነ ልቡና ቀውስ ገጸባህሪያቱን እንዴት ለሥነ ልቡና ሞት ያጋልጣቸዋል ?
3. በተመረጠው እንቅልፍ እና እድሜ ልብወለድ ውስጥ ለሥነ ልቡናዊ ሞት የሚጋለጡት የትኞቹ ናቸው ? ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ጠቀሜታዎች የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ፖሊሲ አውጭዎች፣ ተመራማሪዎች፣ የስነ ሕዝብ ባለሙያወች... የሥነ ልቡናዊ ሞት መከሰቻ ምክንያቶችንና የሚያስከትሉትን ሰብአዊ ቀውስ እንዲገነዘብ ያግዛል፡፡ድርሰቱ የተደረሰበትን ዘመን የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ርዕዮተ ዓለማዊ መስተጋብር ከሥነ ልቡና ሞት እና ክስተት አንጻር በማንፀሪያነት ለማየት ያገለግላል፡፡ የሥነ ልቡናዊ ሁነቶች እና ሥነ ፅሑፍ ያላቸውን ትስስር ሊያሳይ ይችላል፡፡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ወይም ድርጅቶች የሥነልቡና ቀውሱ እያስከተለው ያለውን ማህበረሰባዊ ችግር በመረዳት መፍትሄ እንዲያፈላልጉ ያግዛል፡፡ ዘመነኛውን የልብወለድ የአጻጻፍ ቴክኒክ ተረድቶ ለሚነሳ ጸሐፊ የአቅጣጫ ጠቋሚነት ይኖረዋል፡፡ በሥነ ልቡና ዙሪያ ላይ ተጨማሪ ምርምር እንዲደርግ በር ሊከፍት ይችላል፡፡ በሥነ ሰብዕ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች መነሻ በመሆንም ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የበእውቀቱ ስዩም ስራ በሆነው እንቅልፍ እና እድሜ /1999/ ልብወለድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመድበሉ ውስጥ የሚገኙትን "መውረድና መውጣት"፣ "ማየትና መጋረድ" እና "መቅረብና መራቅ" በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች የተጸፉትን ታሪኮች ብቻ መሰረት ተደርጎ የተሰራ ነው፡፡ ሌሎች የደራሲውን ስራዎች አያካትትም፡፡ ጥናቱ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብን መሰረት ያደረገ ሲሆን በፍካሬ ልቡናዊ ንባብ ከሚታዩት የተለያዩ ጉዳዮች ውስጥም "ሞትን" ብቻ ነጥሎ የሚያይ ነው፡፡ ጥናቱ ሞትን ሲያይ ከሞትም አካላዊ ሞትን ሳይሆን

ሥነ ልቡናዊ ሞትን እና የሥነ ልቡና ሞት መከሰቻ የሆኑትን የሞት ፍርሃት እና የሥነ ልቡናዊ ቀውስ መከሰቻ ሰዋዊ ባህሪያት መሰረት በማድረግ የሀቲት ትንተና ማድረግ ላይ የተገደበ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ሲሆን፣ የቴክስት (ልብወለድ) አመራረጥ መስፈርት፤ የመረጃ መሰባሰቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ አተናተን ስልትና ሂደት የሚሉ ክፍሎች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

### 1.7.1. የቴክስት (ልብወለድ) አመራረጥ መስፈርት

ይህ ጥናት " ሥነልቡናዊ ሞት በበእውቀቱ ስዩም በእንቅልፍ እና እድሜ(1999)፤ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ" የሚል ርዕስ ሲኖረው በዚሁ ልብወለድ በሦስት ክፍሎች ተከፋፍለው የቀረቡትን "መውረድና መውጣት"፣"ማየትና መጋረድ" እና "መቅረብና መራቅ" በሚሉ ታሪኮች ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠና ስራ ነው፡፡ ጥናቱም በሰው ልጅ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚከሰቱ የሥነ ልቡናዊ ሞት መገለጫ ባህርያት የሆኑ የሞት ፍርሃት፤ ጭንቀት፤ ተስፋ መቁረጥ፤ ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር የሚሉ ሰዋዊ የስሜት ባህርያት በስራው ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ ለመመርመር የሚደረግ ጥናት ነው፡፡

በመሆኑም ቴክስቱ የተመረጠው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን ሥነልቡናዊ ሞት በፍካሬ ልቡና ንባብ አይቶ ለመፈከር ያስችላል ከሚል እምነት በመሆኑ እና የምርምሩ አይነት ምርምሩ በተመረጠው ቴክስት ላይ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ የሃቲት ትንተና ማድረግ በመሆኑ የምርምሩ አይነት አይነታዊ የምርምር ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም የቴክስት መምረጫ መስፈርቱ አላማ ተኮር የቴክስት (ልብወለድ) አመራረጥን በመጠቀም የተመረጠ ነው፡፡

### 1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ መረጃ ይገኙባቸዋል በሚል ሁለት የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ አንደኛው ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገለው ራሱ ታላሚ የሆነው እንቅልፍ እና እድሜ ልብወለድ ሲሆን በውስጡ አጭቆ የያዛቸው የስነ ልቡና ጣጣዎች በፍካሬ ልቡና ንባብ አይቶ ለመፈከር ስለሚያስችል የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግሏል፡፡ በሁለተኛ ወይም በዳህራይ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት በሥነ ልቡና ሁነቶች ዙሪያ

የተጻፉ የስነጽሑፍ ቲዎሪዎች፣ድርሰቶች እና የምርምር ስራዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጠውን ቴክስትና ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መረጃ ይገኝባቸዋል የተባሉ የሥነጽሁፍ ስራዎችን በመጠቀም መረጃው ተሰብስቧል፡፡

### 1.7.3. የመረጃ አተናተን ዘዴና ሂደት

የመረጃ መተንተኛ ዘዴው በተመረጠው ልብ ወለድ ስራ ውስጥ መረጃውን ለመተንተን የሚያስችሉ የሰው ልጅ የሥነልቡናዊ ሞት መገለጫ የሆኑት የሞት ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ቀቢጸ ተስፋ እና ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር የፍክሬ ልቡና ንባብ በማድረግ ትንታኔው ይካሄድባቸዋል፡፡ ለትንተናው እንዲያመች ለጭብጦች መንስኤ የሚሆኑ የሥነ ለቡና ጣጣዎች ምን ምን እንደሆኑ በምዕራፍ ሁለት በተለዩት መሰረት ከጭብጦቹ ጋር በማስተሳሰር ከቴክስቱ ማሳያ የሚሆኑ ሀሳቦች እየተመረጡ የሀቲት ትንተና ይደረጋል፡፡ ትንተናው መሰረት የሚያደርገው በያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ የሚገኙት ገጸባህሪያት በእለት ተዕለት እንቅስቃሴአቸው የሚያጋጥማቸውን የተመሰቃቀለ የህይዎት ውጣ ውረድ ከሞት ፍርሃት፣ ከሚታየው የሥነ ለቡና ቀውስ እና ከልጅነት አስተዳደጋቸው ጋር እያዛመዱ ማየት ነው፡፡

እንግዲህ የጥናቱ የአተናተን ዘዴና ሂደት ስልቱ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ለጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ እነዚህ የሥነልቡናዊ ሞት መገለጫ ባሕሪያት በምን መንገድ እንደተገለጹ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ የሃቲትና ትንተና ማድረግ ነው፡፡

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ መግቢያውን ተከትሎ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማዎች ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱን ወሰን እና የጥናቱ ዘዴ ተገልጸዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በሚል ርዕስ በንድፈ ሃሳባዊ ዳራው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የሆነው የሥነልቡናዊ ሞት፣ ምንነትና የ ሥነልቡናዊ ሞት መገለጫ ጭብጦች ናቸው በሚል የተለዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ከተለያዩ የስነ ጽሑፍ ቲዎሪ ፤ ከተለያዩ ደራሲያን ብያኔ እና ከመዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው አንጻር የታዩበት ነው፡፡ የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ስር ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተመሳሳይነት አላቸው የሚባሉ ስራዎች ተለይተው ተመሳሳይነትና ልዩነታቸው የታየበት ነው ፡፡ በምዕራፍ ሦስት

የሥነ ልቡናዊ የሞት መገለጫ ጭብጦች ተብለው በምእራፍ ሁለት የተጠቀሱት ከቴክስቱ ማሳያዎችን በመምዘዝ አጠቃላይ ትንተና የሚደረግ ሲሆን በምዕራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያና ለጥናቱ ያገለገሉ ዋቢ ጽሑፎች ይጠቀሳሉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ምዕራፍ ሦስት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ በመጀመሪያው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የሆነው “ሥነ ልቡናዊ ሞት” የሚታይበት የፍካሬ ልቡና (Psychoanalysis) ምንነት የሚታይበት ነው፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሥነ ልቡናዊ ሞት እና የመገለጫ ጭብጦቹ ምንነት በሁለት መንገድተ ከፍለው የሚታይበት ሲሆን፤ በሶስተኛው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ ፤ በሚጠቀሟቸው ስራዎች ፤በጭብጥም ሆነ በይዘት ተመሳሳይነት ያላቸው ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት የሚዳሰስበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1. ፍካሬ ልቡና /psychoanalysis/

ፍካሬ ልቡናዊ ሂስን ለሥነ ጽሑፍ ጥናት መጠቀም በስግመንድ ፍሮይድ ከ1856-1939 የተጀመረ መርህ እንደሆነ ብዙዎች የሚስማሙበት ነው፡፡ ፍካሬ ልቡና በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሰውን ልጅ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ የምንረዳበት ማያ መነጸር ነው፡፡ በዘመናችን እንደ አዲስ በቅለውና ገነው የስነ ጽሑፍን ንድፈ ሃሳብና ሂስ አቅጣጫና ትኩረት ከቀየሱ የእውቀት መስኮች አንዱ ፍካሬ ልቡና እንደሆነም ቴዎድሮስ (2001) ገልጸዋል፡፡ በጥናቱ ዳራ እንደተገለጸው ፍሮይድ ፍክሬ ልቡና ሂስን የአዕምሮ ህሙማንን ለማከም፣ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ መረጃዎችን ለማግኘትና በባለፈ የልጅነት ዘመን በኢ-ንቁ አዕምሮ ታምቆ (Repressed) ሆኖ ያለፈ ፍላጎት በኋለኛው ዘመን የሚንጸባረቅባቸው መንገዶችን፣ የሚያስከትለውን ውጤት ለመተንተንና ተጠኝዎችን ለመርዳት ይጠቀምበት ነበር፡፡ Keith (1996,144)

የሲግመንድ ፍሮይድን የፍካሬ ልቡና ሂስ መነሻ በማድረግ በርካታ ፀሃፍት የየራሳቸውን ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ (Gregory፣2007፣164) ስለ ፍካሬ ልቡና ሂስ ሲገልጹ

> Psychoanaiysis offers a systematic accounting to the psychic apparatus (especially the unconscious) and a theory of the mind and human psychic developmente.Sigemund Freud initially theorized "topographical" relation between the ego and the the unconscious. The former encompassed consciousness and the individual’s contacts with the external world.

ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ከሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀይል በላይ በሆነው /psychic/ በተለይም በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ በሚከሰት የአዕምሮ በሽታና ጤናማ አስተሳሰብ መካከል ስላለው የአዕምሮ እድገት እና የግለሰቦችን አመለካከት በስርዓት የሚቀርብበት መሳሪያ እንደሆነ ነው የገለጸው፡፡

ሌለው የፍካሬ ልቡና ጽንሰ ሃሳብ ከአጠቃላይ ተግባራዊ ሂስነቱ አንጻር ሲታይ በሁለት ይከፈላል ይላሉ፡፡ አንደኛው በፈጠራ ስራው የእድገት ሂደት፣ በስራው እና በደራሲው መካከል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት ለማብራራት የሚያገለግል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአንድ ስራ ውስጥ ያለን ገጸ ባህሪ በስራው ውስጥ ያለውን ግላዊ ትርጉም/ስሜት/ ለመተንተን፣ በስራው ውስጥ ከሚገኙ ምስሎችና ምልክቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ከስረ መሰረታዊ ሂስን /Archetypal pattern/ ማዕከል በማድረግ የሰውን ልጅ ስብእና ለማብራራት ያገለግላል በማለት ሲግመንድ ፍሮይድን ዋቢ በማድረግ ገልጸዋል፡፡ Shores (1966፣296)

ታይሰን (2006) ሲግመን ፍሮይድ ዋቢ በመጥቀስ እንደገለጹት ደግሞ በእያንዳንዱ ሰው ማንነት ውስጥ ሶስት ማንነቶች ይኖራሉ፡፡ እነሱም ኢድ/Id/፣ ኢጎ/Ego/ እና ሱፐርኢጎ /Superego/ እንደሆኑ በመጥቀስ የእያንዳንዳቸውን ምንነትና ተግባር እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

ኢድ/Id/ የሚባለው አንደኛው ማንነት ሲሆን ሰው ራስ ወዳድነት እንዲያድርበት የሚያደርግ፣ በኢንቂ ልቦና ውስጥ የሚከትም፤ የተመኘነውን ሁሉ የራሳችን እንድናደርግ የሚገፋፋ፤ በጣም ስሜታዊ እንድንሆን የሚያደርግ ፤ህግን፣ ባህልን፣ አሰራርን፣ እውነታን እንድንጥስ የሚያደርግ እና በአንድ ህፃን አዕምሮ ውስጥ ታምቀው የቆዩ ወይም በኢ-ንቂ አዕምሮ ውስጥ ተደብቀው የቆዩ ማንነቶች በሆነ አጋጣሚ እንዲከሰቱ የሚያደርግ ማንነት ነው፡፡

ሁለተኛው ማንነት ደግሞ ኢጎ /ego/ ወይም ትክክለኛው የማንነታችን ጠባቂ ሲሆን ተግባሩም ኢድ የተመኘውን ሁሉ እንዳያገኝ /እንዳይፈጽም/፤ አስፈላጊ ሁኔታዎችን እውናዊ በሆነ መንገድ ማመቻቸት ነው፡፡ ነባራዊ ሁኔታዎችን እንድንመዝን፤ ህግንና አሰራርን እንዳንጥስ፤ትክክለኛነትን እንድንመዝንና እንድንተገብር የሚያደርግ ማንነት ነው፡፡

ሶስተኛው ማንነት ሱፐር ኢጎ / super ego/ ሲሆን በንቁ ልቦና ውስጥ የሚከትምና የኢድንና የኢጎን አብዝቶ መሰልጠን በማመጣጠን በተለይም የኢድን ግልጽ ፍላጎት የሚያሰክን ከማህበራዊና ባህላዊ ስርዓት እንዳናፈነግጥ የሚያደርግ ሲሆን በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ስብእና ውስጥ የነዚህ የሶስቱ ፍጭት ዘዎትር የሚያጋጥም እና የፍጭቱ መቋጫ ደግሞ እንደ አሸናፊው ወገን የሚወስን እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የሦስቱ አዕምሮዎች ተቃርኖ ወይም ፍጭት በግለሰቡ ሥነልቡናዊ ጤንነት፣ አካላዊ ደህንነትና ከሌሎች ሰዎች /ከማህበረሰቡ/ ጋር በሚኖረውን ግንኙነት ላይ እንደ አሸናፊው ወገን የማበላሸትም ሆነ ሰላማዊ የማድረግ ኃይል አላቸው፡፡ ይህም ከለይ የእያንዳንዳቸውን ምንነት በተገለጸበት መንገድ ኢድ አሸናፊ /የበላይ/ በሚሆንበት ጊዜ ግለሰቡ ራስ ወዳድ በመሆን የራሱም ሥነልቡናዊ ጤንነትና አካላዊ ደህንነት ይጓደላል፤ ለሌሎች ደነታ ቢስ በመሆን ህግን ባህልንና አሰራርን በመጣስ ከሌሎች ወይም ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሰላማዊ እና ጤናማ አይሆንም፡፡ ኢጎ አሸናፊ ወይም የበላይ በሚሆንበት ግለሰቡ ለራሱም ሆነ ለሌሎች ሰላማዊና ጤናማ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡ ሱፐር ኢጎ አሸናፊ ወይም የበላይ በሚሆንበት ጊዜ የኢድን ግልጽ ፍላጎት በመጫን በኢድና በኢጎ መካከል ያለውን ፉክክር በማመጣጠን ግለሰቡ ትክክለኛ ማንንት እንዲኖረው ሚዛናዊ እንዲሆንና ከራሱም ሆነ ከማህበረሰቡ ጋር ጤናማና ሰላማዊ ህይወት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡

የፍካሬ ልቡና በሲግመንድ ፍሮይድ ተጀምሮ ለረጅም ጊዜ የሰውን ልጅ ባህሪ ለመረዳት ያገለገለ ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን የሰውን ባህሪ በተሻለ መንገድ ለመረዳት እያገለገለ እንዳለ

> we'll begin to understand human behaviors that until now may have seemed utterly baffling, and of cours, if psychoanalysis can help us better understanding human behavior, then it must certainly be able to help us understand literary texts. Which are about human behavior.ታይሰን (2006፣11) ገልጸለች፡፡

ከሥነ ልቡና አንጻር የሰውን ልጅ ባህሪ ከተለያየ አቅጣጫ በማየት የሚጠና ሲሆን ፍሮይድ በኢንቁ አዕምሮ የሚፈጠር ስሜት /The origin of unconscious/፣ የሥነ ልቡና መከላከል /defenses/፣ ጭንቀት /Anxiety/፣ ህልም እና የህልም ተምሳሌት /Dreams and dream symbols/ ፣የሞት ምንነት/ The meaning of death/፣ የወሲብ ምንነት/ The meaning of sexuality/፣ ምኞት /ፍላጎት/ /desire/፣ ጉጉት /Anxious/፣ የአዕምሮ

ዘገምተኝነት /Fixation/፣ ጤነኛ ያልሆነ እራስን ማምለክ /Narcissism/፣ ረቂቅ የሆነ እንግዳ ክስተት /Uncanny/፣ ጤነኛ ያልሆነ ፍርሃት ወይም ጥላቻ /Phobias/፣ በሚሉ ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለው ዕንጻዩት የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ (ታይሰን፣ 2006) እና Ryan,2004)

ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት የሚታየው ሥነ ልቡናዊ ሞት በመሆኑ በዚህ ጥናት ሞት እና የሞት መገለጫ ጭብጦች ተብለው የተሉዩት ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር እና ለእነዚህን ጭብጦች መከሰት ምክንያት የሚሆኑ የስሜት ባህሪያት በዋናነት የሚታዩ ሲሆን ሌሎቹ ለጥናቱ አስፈላጊ ሁነው ሲገኙ ብቻ የሚታዩ ይሆናል፡፡

## 2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.2.1. ሞት /Death/

ሞት ሰፊና ዝንቅ የሆነ ትርጉም ያለው ትዕምርት ነው፡፡ ከመዝገበ ቃላዊ ትርጉም ስንነሳ "ሞተ ፡- ነፍሱ ከስጋው ተለየች፣ ተዳከመ ፣ቀነሰ ፣አቅም አጣ ፣ሰነፈ ፣ተስፋ ቆረጠ ፣አንድን ነገር ከተገቢው በለይ አደረገ" የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) በሚል ገልጾታል ፡፡ በዚህ መዝገበ ቃላዊ ፍች ሞት ሁለት የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን እንደያዘ ያሳያል፡፡ አንደኛው የህይወት ፍጻሜን ሲያመላክት ሁለተኛው ደግሞ በሰው ልጅ የህይወት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የአቅም ማጣት፣ መዳከም፣ መቀነስ፣ መሸነፍ (ተስፋ መቁረጥ)፣ የማይገባ ስራ መስራት የሚሉ ሃሳቦችን እንደያዘ ያሳያል፡፡ ከመዝገበ ቃላዊ ፍች ባሻገር የተለያዩ ምሁራን በስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ስለሞት ከሰጡት ብያኔ የተወሰኑትን ለማ የት፡-

"ሞት" ተፈጥሯዊ ክስተት ብቻ አይደለም፡፡ የነገሮች መቁረጫ እና መፈጸሚያም አይደለም፡፡ ይልቁንም እንደየ ባህሉ፣ እንደየ ዘመኑ አንድም እየተባለ ሊፈከርና ሊተረጎም የሚችል ዝንቅ ትዕምርት ነው፡፡ ሞትን ከአሟሟቱ አኳያ ድንገተኛ ሞትና ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት በማለት በሁለት ይከፈላል፡፡ የሁለቱን አንድነትና ልዩነት ሲገልጹ ድንገተኛ ሞት በሰው ላይ የሚመጣ በሰው ላይ የሚደርስ ክስተት ነውና እጅጉን ከሥነ ህይወታዊ ሞት ጋር ይዛመዳል ፡፡ በአንጻሩ ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት በዋናነት ሰውን ከሌላ ክስተት ጋር ሳይሆን ከራሱ ጋር "ምን አደረኩ?" "የት ደረስኩ?)" በሚሉ ጥያቄዎች

ስለሚያሚግት ከሥነ ህይወታዊ ሞት ይልቃል እጅጉንም የፍለስፍና፤ የአንደምታ ጉዳይ ነው፡፡ (ቴዎድሮስ 2001፤157)

በሌላ በኩል ቴወድሮስ (2001፣145) ሜርሎጅ ዌይስትን ፋልን በመጥቀስ ሞት በጥቅሉ ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው አይነት ስነ ህይወታዊ ሞት ተብሎ ሲጠራ ሁለተኛው ደግሞ ነገረ ህልውናዊ ሞት ተብሎ ይጠራል ሲል ይገልጻል ፡፡ ሥነ ህይወታዊ ሞት ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ህይወት ያለውን ሁሉ የሚገዛ  በአደጋ፣ በረሀብ፣ በእርዛት፣... ይመጣል ሲል የሰው ልጅ የተለያዩ ማንነቶች ያሉት ፍጡር በመሆኑ ሥነ ማህበራዊ ማንነት ፣ሥነ ልቦናዊ ማንነት እና ሥነ ምግባራዊ ማንነት አለው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅም ከሥነ ህይዎታዊ ሞት በተጨማሪ ሥነ ምግባራዊ ሞት፣ ሥነ ማህበራዊ ሞት እና ሥነ ልቡናዊ ሞት አለው ሲል ያብራራል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከተጠቀሱት የሞት አይነቶች ሥነልቡና ሞትን  መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ሞት በማንኘውም ጊዜና ቦታ በሰው ልጅ የእለት ተለት የህይዎት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያጋጥም ወይም የሚከሰት የኑሮ ስጋት ነው፡፡ (Mohammed ,2016፣8)  በሌላ በኩል ይሁ ተመራማሪ  ሞት በሁለት የተለያዩ መንገዶች መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ አንደኘው መንገድ ከግል ስሜት ጋር /subjective/ በተያያዘ ሞት በእያንዳነዱ የእለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴያችን የምንገነዘበው ፤በማንኘውም እንቅስቃሴያችን የሚከሰት ተጨባጭ ምክንያት የማያስፈልገው ሁል ጊዜም አብሮን የሚኖር እስጊ ሁኔታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ማንኘውም እንቅስቃሴ ከሞት ጋር ትይዩ ነው፡፡ ሞት ያልተለመደ ድርጊት ሳይሆን ወደፊት በማንኘውም እንቅስቃሴ ውስጥ ሊከሰት የሚችል ጉዳይ ነው በማለት እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡

"Death means; the every single day of our life you realize that the death occur at any moment and there is no necessary reason why we should live another day. ---Death is always impending." (Mohammed, 2016፣8-10) በማለት ገልጾታል፡፡

ሁለተኛው የሞት መታያ መንገድ ሞትን ገሃዳዊው /objective/ በሆነው አለም መመልከት ነው፡፡ ሞት ታስቦ፣ አዘውትሮ ወይም ተደጋግሞ የሚመጣ አይደለም፡፡ በሰው ልጅ የኑሮ ሂደት ውስጥ ችግር በመሆን አንድ ቀን ድንገት የሚከሰት ድርጊት ነው፡፡ የሰው ልጅ ገሃዳዊ የሆነውን ሞት ተከላክሎ ወይም ወስኖ ማስቀረት አይችልም፡፡ዝኒ ከማሁ /ገጽ፣11/

ሞት ሰፊና ዝንቅ ትዕምርትን እንደሚወክል የተለያዩ ምሁራን ከዚህ በላይ ከሰጡት ብያኔ እና ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡ ለሞት አንድ ወጥ የሆነ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም

መስጠት እንደማይቻል ያሳያል፡፡ አንዳንዶቹ ስነ ህይወታዊ ሞትን፤ አንዳንዶቹ ማንነትን ፤አንዳንዶቹ ከነገረ ህላዌ ፍልስፍና አንጻር፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰው ልጅ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ከግል ስሜት ጋር የሚገናኘውን እና ሞትን ገሃዳዊ በሆነው ዓለም ውስጥ መመልከትን መነሻ ሲያደርጉ ታይሰን(2006) ደግሞ ከሞት ፍርሃት ጋር በማያያዝ አይታለች፡፡

ሥነ ልቡናዊ ሞት ፍካሬ ልቡናዊ ሂስን /psychoanaitic criticism/ መሰረት በማድረግ የሰውን ልጅ የእለት ተእለት የህይዎት እንቅስቃሴ እና ገጠመኝ ተከትሎ የሰውን ልጅ ስሜት፣ ባህሪንና ቤተሰባዊ ሁኔታ የሚጠናበት መንገድ ነው፡፡ በሥነ ልቡናዊ ንባብ ሞት በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡፡ ከመገለጫዎቹ የሞት ፍርሃት /Fear of Death/ እና የሥነ ልቡና ቀውስ /Psycholgical Disturbance/ ልንለው እንችላለን፡፡ በሞት ፍርሃት ስር የመገለል ፍርሃት፤ የመቀራረብ ፍርሃት እና ክህደትን መፍራት የሚታዩ ሲሆን በስነ ልቡና ቀውስ ስር ጭንቀት፣ ቀቢጸ ተስፋ፤ ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር፣ የሚሉትን እናያለን፡፡

በሌላ በኩል ሥነ ልቡናዊ ሞት አጅግ ረቂቅ እና በተለያየ መንገድ እንደሚከሰት ፍሮይድን ዋቢ በማድረግ ከገለጸች በኋላ የሥነ ልቡና ሀሳቦች በማለት የእህትማማች ፉክክር /sibling rivalry/፣ የዝቅተኝነት ስሜት /inferiority/፣ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ገልጻለች፡፡ የሰው ልጅ ባህሪ በንቁና በኢ.ንቁ አዕምሮአዊ /conscious and unconscious /አስተሳሰቦችና ልማዶች የሚገለጹ እና የሚታዩ አሳዛኝ እና ስሜታዊ ልማዶች መገለጫ የሆኑ እንደ የአዕምሮ መታወክ /wounds/፣ ፍርሀት /fear/፣ ጥፋተኝነት /Guilty desires/፣ ዝቅተኛነትና በቀላሉ የማይበርድ ግጭት /unresolved coanflict / ሳናውቀውና ሳንፈልገው በተዳከመ ስሜት ውስጥ የሚከሰት እንደሆነ ገልጻለች፡፡ታይሰን (2006)

### 2.2.2. የሞት ፍርሀት /Fear of Death/

የሰው ልጅ ሞትን የሚፈረው በእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴው ከአቅሙ በለይ የሆነ፣ በራሱ አቅም ሊወጣው የማይችልና ያልተለመደ ነገር ሲገጥመው ነው፡፡ በተለመደው ጤናማ አኗኗሩ ወጭ የሚያደርግ ችግር ሲገጥመው የሚከሰት የስሜት ባህሪ እንደሆነ፤ አንዳንዶች ደግሞ የሰው ልጅ አለመኖርን በመፍራት ከመወለዱ በፊት ቀድመውት በተዘጋጁለት ስርዓቶች ውስጥ በመግባት በአኗኗር ስርዓት፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በልማድ ፣ በስጋትና በፍርሃት እንደሚኖር ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ የሰው ልጅ ከመወለዱ በፊት ቀድመው የተዘጋጁለትን ስርዓቶች እየሰጋእና እየፈራ እንደሚኖር

> አለመኖር የሰው ልጅ ቀዳሚው ፍርሀት ነው፡፡ መኖር የሚጀምረው አለመኖርን ከመስጋት ነው፡፡ …ይህ ስጋት ታዲያ በህይወታችን ሙሉ የሚዘልቅ ነው፡፡ በየደረጃው በየእድሜያችን ለአለመኖር ስጋት እየተጋለጥን እንዘልቃለ፡፡ የምንኖርበት አለም ደግሞ የሰው ልጅ የዘመናት የአለመኖር ስጋቱን ለማስወገድ በመመኘት የገነባው የአኗኗር ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከመወለዳች ይረከበናል፡፡ ወላጆች፣ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ ሰፈር፣ ብሄር፣ ሀገር፣ ቋንቋ፣ ባህል ፣ሃይማኖት፣ ልምድ ያሉበት ዓለም ከእኛ ቀድሞ ይጠብቀናል፡፡ ይህ ሁሉ ባለበት ዓለም ተወልደን በእነኝህ ቀድመው በተዘጋጁ ስርዓቶች ውስጥ አለመኖርን ሸሽተን ለመኖር ስንል እንታሰራለን፡፡(ዳዊት፣2009፣6)

የሰው ልጅ ተወልዶ ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ከሱ በፊት ተዘጋጅተው በሚጠብቁት ማህበራዊ ፣ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች፣ ልማዶችና ዶግማዎች ውስጥ አውቆትም ሆነ ተገዶ ይገባል፡፡ በሂደትም ለመኖር ሲል የሱ አድርጎ ያጠልቃቸዋል፡፡ ይጠብቃቸዋል፡፡ ያዘልቃቸዋል፡፡ አለመኖሩን ፈርቶ ለመኖር በሚያደርገው የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ እነዚህን ስርዓቶች እንዳይጥስ እየፈራና እየሰጋ ይኖራል፡፡ ሞት ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር እጅግ የተቆራኘ እውነታ ስለሆነ የማይፋቅ ወይም ሊካድ የማይችል ክስተት ነው፡፡ ሞት በውስጣችን ያለ ተፈጥሯዊ እውነታ ቢሆንም የዚህ ግልባጭ የሆነው ሞትን መፍራት ከብዙዎቹ የስሜት ባህሪዎቻችን ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ታይሰን (2006) ገልጻለች ፡፡

ፍርሃት የሰው ልጅ የስሜትና የባህሪ መገለጫ ከሆኑት አንዱ እንደሆነ ከታይሰን ገለጻ ተመልክተናል፡፡ የሰው ልጅ ከስነ ለቡናዊ ሞት አንጻር ሞትን የሚፈረው በእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ በእውንና በሃሳብ በመከሰት መደበኛ እንቅስቃሴው በማጎል ፣አላስፈላጊ ድርጊት እንዲፈጽም ፣በራሱ እንዳይተማምን በማድረግና ለሌሎች አላስፈላጊ ባህርያት አሳልፎ በመስጠትና ከነበረ ማንነቱ በማስወጣት ከራሱ፣ ከቤተሰቡ እና ከማህበረሰቡ በመነጠል የተገለለ ወይም ብቸኛ ያደርገኛል ከሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

> ፍርሃት እውን/ ተጨባጭ /ወይም ምዕናባዊ /ሃሳባዊ/ ሊሆን ይችላል ፡፡ ፍርሃት ሰዎች እንግዳ የሆነ ነገር እንዲከውኑ ያደርጋቸዋል ፡፡ ፍርሃት የሚመነጨው ነገሮችን በተገቢው መንገድ ከመረዳት ችግር ነው፡፡ በፍርሃት መኖር ማለት በስሜት እስር ቤት ውስጥ መኖር ማለት ነው፡፡ ፍርሃት በራስ የመተማመንንና የደህንነት ስሜትን ከማጥፋቱም በለይ በውሳኔ ላይ ወላዋይ ያደርጋል፡፡ ፍርሃት እምቅ ብቃትንና ክህሎትን ያጠፋል፡፡ ፍርሃት ከተሰማን በተገቢው መንገድ ማሰብ ይሳነናል፡፡ ፍርሃት ጤናችን ያቃውሳል፣ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነትም ያበላሻል፡፡ ፍርሃት ጭንቀትን በማስከተል ምክንያታዊ ወደ አልሆነ አስተሳሰብ

> ይመራል፡፡ ...የፍርሃት ጤናማው አጸፌታ ሽሽት ነው፡፡ ሽሽት የፍርሃት ስሜትን ለጊዜው አስወግዶ የምቾት ቀጠና ውስጥ ያስቀምጠናል፡፡ በሃሳብ የተፈጠሩ ፍርሃቶች እውነተኛውን ችግር ያገዝፉሉ፡፡ ፍርሃት ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ ደስታንና መልካም ግንኙነትን የማንኮታኮት አቅም አለው፡፡/ማህሌትና ዳኘ፤2001፤93/

ይህን ጥቅስ በዚህ ቦታ መጠቀም ያስፈለገው ሞትን ከመፍራት ጋር አብሮ የሚሄድ ሁኖ ሳይሆን አጠቃላይ ሰለፍርሃት በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ የሰው ልጅ በሚያጋጥመው የሥነልቡና ሞት ክስተቶች ምክንያት የነበረ ማንነቱን ስቶ የሱ ባልሆነ እና ኢ. መደበኛ በሆነ ጊዜያዊ ማንነት ውስጥ ሆኖ በኢ-ንቁ አዕምሮ /unconscious/ የሚያስበው፣ የሚመኘው እና የሚከውነው ነገር ሁሉ ፍርሃት የወለዳቸው ወይም ከመደበኛው ስሜት ወጥተን ከጤናማ አስተሳሰብ ርቀን የኛ ባልሆነ አሰተሳሰብ የምንከውነው ተግባር ነው፡፡ ፍርሃት የኛ ያልሆነ ከጤናማ አስተሳሰብ ውጭ የሆነ ድርጊት እንደንፈጽም ከማድረጉም በለይ መደበኛው አስተሳሰባችን እንዲታሰር፣ በራስ መተማመናችን እንዲቀንስ፣ ከሌሎች ጋር ያለን መልካም ግንኙነት እንዲሻክር፣ የገጠመን እውነተኛ ችግር እንዲገዝፍ፣ ጤናችን እንዲታዎክ በማድረግ ከመደበኛ ስራችን የሚያስወጣ በተለያየ መንገድ የሚከሰት የሰው ልጅ የስሜት ባህሪ ነው፡፡

በሥነ ልቡና ሞት ውስጥ የሚታየው የሞት ፍርሃት በብዙ መንገድ ይገለጻል ፡፡ ከነዚህም መገለጫ ባህሪያቱ የመገለል ፍርሃት / Fear of Abandonment/፣ የመቀራረብ ፍርሃት /Fear of Intimacy/ ፣ የመክዳት ፍርሃት /Fear of Betrayal/ በማለት ትገልጻለች፡፡ (ታይሰን፣2006)

### 2.2.2.1 የመገለል ፍርሃት /Fear of Abandonment /

የሰውልጅ ሞትን ከሚፈራባቸው ችግሮች አንዱ መገለልን መፍራት ነው፡፡ መገለል ከቤተሰብ ወይም ከማህበረሰብ መለየት እና ብቸኛ መሆን በመሆን ይፈረዋል ፡፡ "For many of us the thought of our own death keys in to our fear of abandoment our fear of bing alone death is the ultimete abandoment no matter how important we are in our communities when we die we die alon." /ታይሰን 2006,22/

“abandonment” የሚለውን “መገለል” የሚል ትርጉም በመስጠት ለዚህ ጥናት ተጠቅሞበታል፡፡ ከሞት ጋር በተያያዘ የሰው ልጅ የስሜት መገለጫ ባህሪያት ከሆኑት

አንዱ ፍርሀት ነው ሲባል ሞትን የሚፈራው ከወዳጅ፣ ከጓደኛ፣ ከማህበረሰብ ነዋሎ የተገለለ ወይም የተተዎ ስለሚአደርግ ነው፡፡ የሞት የመጨረሻ ግቡ መለየት/ማግለል/ ነው፡፡ መገለል ደግሞ አስፈሪ ነው፡፡ ሰው በቤተሰቡ ከተገለለ በኋላ ብቸኛ ስለሚሆን ሞትን ይፈረዋል፡፡ በሌላ በኩል ሰው ከራሱ ሞት በተጨማሪ የሌሎችን ሞትም ይፈራል፡፡ "Fear of abandoment alos plays a role when we fear the death of others, when chiidrn lose a parent when adults lose a spous, the over whelming feeling of lose is often a feeling of adandoment." በማለት ገልጻለች፡፡ዝኒከማሁ

ሞትን የምንፈረው በራሳችን ላይ ደርሶ ከዘመድ ከወዳጅ ከማህበረሰብ ነዋሎ ብቸኛ ስለሚያደርገን ብቻ ሳይሆን ህጻናት ወላጆቻቸውን በማጣት፤ አዋቂዎች የትዳር ጓደኛቸውን በማጣት ተለይተው ብቸኛ ከመሆናቸውም በላይ ስሜታቸውንም በማዳከም ስለሚጎዳቸው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በወዳጁ፤ በጓደኛው እና በቤተሰቡ ሞት ስሜቱ የተጎዳ ሀዘንተኛ በፈጣሪውም እንደተተዎ በማሰብ የተለያዩ ጥፋቶችን ወይም ስህተቶችን ለማድረስ የሚያስችል የአዕምሮ /የሥነ ልቡና/ መታዎክ ጉዳት እንደሚደርስበት ትገልጻለች፡፡ /ዝኒ ከማሆም/

በሌላ በኩል ታይሰን የመገለል ፍርሃትን በአካል መገለል እና በስሜት መገለል በማለት በሁለት ትከፍለዋለች፡፡ "Fear of abandonment- the unshakable belief that our friends and loved ones are going to desert us /physical abandonment/ or don't really care about us /emotional abandonment/". በማለት ገልጸዋለች፡፡ ይህ ማለት ጓደኛ ወይም ቤተሰብ በአካል ሲርቀን እና በአካል አብሮን እየኖረም ስለኛ የማያስብ እና የማይጨነቅ ከሆነ ይህ ሰው በአካል ወይም በስሜት ትቶናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በአካልም ሆነ በስሜት በቅርብ ጓደኞቻችን ወይም ቤተሰቦቻችን ስንለይ ወይም ስንተው ብቸኝነት ስለሚሰማን ሞትን እንደምንፈራ ገልጻለች ፡፡

#### 2.2.2.2. መቀራረብን መፍራት/ Fear of Intimacy

በጥልቀት የመቀራረብ ፍርሃት የሞት ፍርሃትን የምናይበት አንዱ መንገድ እንደሆነና ብዙውን ጊዜ የዚህ ፍርሃት ውጤቱ የሚያያዘው ለህይዎታችን ወይም ለመኖር ካለን ፍርሃት ጋር ነው፡፡ ይህን ፍርሃት ታይሰን /2006፣23/ "Fear of intimacy, this is one of the ways we can see how fear of death often results in fear of life. That is, our

fear of death, of losing our life, can result in our fear of being intimately attached to life." በማለት ገልጸዋለች፡፡

የሰው ልጅ ካለው በጥልቅት መቀራረብ የተነሳ ሞትን ይፈራል፡፡ አካላዊ ሞቱን የሚፈራው ደግሞ የአካላዊ ሞቱን /የህይዎት ማለፉን/ ብቻ ሳይሆን ሞትን ተከትለው የሚመጡ በሞት ምክንያት የሚያጣቸው ብዙ ነገሮች ስለአሉ ነው ፡፡ ሰው ሞትን የሚፈራው በራሱ ብቻ ሳይሆን የቅርብ ቤተሰብን ሞት ጭምር እንደሆነ ከለይ አይተናል ፡፡ ምክንያቱም በራሱ ሞትም ሆነ በቤተሰቡ ሞት የሚያጣው ብዙ ነገር አለው፡፡ የሰው ልጅ ሞትንና ሞትን ተከትለው ከሚመጡ የሥነ ልቡና ጣጣዎች ጋር የሚኖረው ግኙነት ውሎ አድሮ ከፍርሀት አልፎ ጭንቀትን በማስከተል ተስፋ በማስቆረጥ እራስን እስከ ማጥፋት ሊያደርስ ይችላል፡፡

በሞት ምክንያት በሚያጣቸው ወዳጅ ዘመዶቹ የሚደርስበትን ከፍተኛ ሀዘንና የሥነ ልቡና ጫና መቋቋም ስለሚያቅተው አስቀድሞ በጥልቀት መቀራረብን መፍራት አንዱ የፍርሃት መገለጫ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም ታይሰን የሰው ልጅ ሞትን ይፈራል ሲባል ሞትን የሚፈረው ዝም ብሎ ሳይሆን ሥነ ሕይዎታዊ ሞቱ የሚያስከትለውን ስሜትና የሚያሳጣውን በመገንዘብ እንደሆነ ስትገልጽ::

> If we complicate matters by realizing that our fear of death is not merely fear of biological death. But translat for most of us in to fear of loss in general loss of my mate's attention, loss of my children's love, loss of my health, loss of job, loss of my looks, loss of my money-then we can see how death, emotionally death, if not biological death. /ገጽ፣23/ ገልጻለች፡፡

ሰው ሞትን ሲፈራ በአካል መሞቱን ወይም የህይዎት ማለፉን ወይም ስነ ህይወታዊ የሆነውን ሞት ብቻ ሳይሆን በሞት ምክንያት የሚአጣቸው በርካታ ፍርሀቱን የሚያባብሱ ቁሳዊና አካላዊ ነገሮችም እንዳሉ መረዳት ያስችላል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የትዳር ጓደኛን ማጣት፣ የልጅን ፍቅር ማጣት፣ ጤና ማጣት፣ ስራን ማጣት፣ የነበረን ውበትን ማጣት፣ ሃብትን ማጣት እንዚህ ሁሉ ሥነ ልቡናዊ ሞትን ከሚፈራባቸው አባባሽ ምክንያቶች እንደሆኑ ነው የተገለጸው፡፡

እንደ ታይሰን አገላለጽ ለፍርሀታችን ማደግ ዋና ዋና ምክንያቶች ለነገሮች ያለን ከፍተኛ ፍቅር እና ለመኖር ካለን ከፍተኛ የሥነ ልቡና ፍላጎት የተነሳ የሚያጋጥመን ታላቅ ድንጋጤ፣ ስቃይና፣ ጥላቻ የተነሳ እንደሆነ እና በሌላ በኩል የፍርሀታችን ውጫዊ አባባሽ በማለት የምናያቸው እና የምንሰማቸው ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ማለትም አስደንጋጭ ድራማዎች፤ /violent movies/ ወይም docudrams /አስደንጋጭ የሆኑ የመኪና አደጋዎች /roadside care wreck/፣ በልጆች ላይ ጉዳት ማድረስ /child abuse/፣ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል /rape/፣ ኤድስ /AIDS/ እና በቴሌቪዥን የሚታይ አሰቃቂ ድራማዎች ማለትም የትዳር ወይም የፍቅር ጓደኛን መግደል /kill the ir spouses/ የመሳሰሉትን ገልጻለች፡፡ /ገጽ፣24 /

### 2.2.2.3. ክህደትን መፍራት /Fear of Betrayal/

የመክዳት ፍርሃት በተለያየ መንገድ የሚገለጽ ቢሆንም በዋነኛነት በሚዋደዱ ጓደኛማቾች ወይም የፍቅር ጓደኝነት በጀመሩ ጥንዶች አለመተማመን ተከትሎ የሚፈጠር ወይም የሚከሰት ስጋት ወይም ፍርሀት ነው፡፡ ሊዋሸኝ ወይም ልትዋሸኝ ይችላል ወይም ትችላለች፤ ከጀርባ ሌላ ሰው አለው ወይም አላት:: አኔን እያሾፈብኝ/ችብኝ/ ነው:: ከሌላ ሰው ቀጠሮ ይኖረዋል /ታል/:: በሚል የሚኖር የጥርጣሬና ፍርሀት ነው፡፡ በጥቅሉ ይህ ፍርሃት አለመታመን የሚፈጥረው የመካካድ ፍርሃት ነው፡፡ይህን የመከዳዳት ፍርሃት ታይሰን 2006 /ገጽ፣16/ ላይ እንዲህ ትገልጸዋለች

"Fear of betrayal- the nagging feeling that our friends and loved ones can’t be trusted, for example, can’t be trusted not to lie to us, not to laugh at us behind our backs, or in the case of romantic paretners not to cheat on us by dating others."

ክህደት የሚፈጥረው ፍርሃት በፍቅረኛሞች ወይም በባለትዳሮች መካከል ብቻ የሚፈጠር ሳይሆን በማንኛውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፤ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ሁሉ የሚከሰት/ሊከሰት የሚችል/ ክስተት ነው፡፡

### 2.2.3. የስነ ልቡና ቀውስ /Psychologicale Disturbance/

የሥነ ልቡና ቀውስን የሥነልቡናዊ ሞት መገለጫ አድርጎ መውሰድ ያስፈለገበት ምክንያት የሞትን ትርጉም ባየንበት ክፍል ከመዝገበ ቃላዊ ትርጉሙ እንደምንረዳው ከስነሕይወታዊ ሞት ባሻገር ተዳከም፣ቀነሰ፣አቅም አጣ፣ተስፋ ቆረጠ፣ አንድን ነገር ከተገቢው በላይ አደረገ የሚሉት ትርጉሞች በሰው ልጅ ቁመናዊ ባህሪ የሚከሰት ሥነልቡናዊ ሞቶች ናቸው፡፡ ለዚህ ባህሪ የሚያጋልጡት ደግሞ በእለት ተዕለት እንቅስቃሴው የሚያጋጥሙት በቀላሉ ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች የስነ ልቡና ቀውስ በመፍጠር ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የሰው ልጅ በቀውስ ውስጥ ሲሆን ሥነልቡናው እንዲሞት የሚያደርጉት ጭንቀት ውስጥ በማስገባት ተስፋ እንዲቆርጥ በማድረግ እና ራሱን ዝቅ አድርጎ እንዲያይ በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ጭንቀት፣ቀቢጸ ተስፋና ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር በሥነ ልቡናዊ ቀውስ ውስጥ የሥነ ልቡናዊ ሞት ጭብጦች ሁነው ይታያሉ፡፡

#### 2.2.3.1. ጭንቀት /Anxiety/

ጭንቀትን የሞት መገለጫ ነው ስንል ሞትን ከምንፈራበት ጋር በማያያዝ አይደለም፡፡ ከሞት ትረጉም አንጻር የሰውን ተፈጥሯዊ ሚዛን የሚያዛባ የአካል፣ የአእምሮና የስሜት ትንኮሳ /stimulus/ የሚፈጥር እና የሥነልቡና ቀውስ ስለሆነ ነው፡፡ የአንድን ሰው ፍላጎት ሊያንቀሳቅስ ከሚችለው የማህበራዊ ሀብቶች አቅም በለይ ሆኖ ሲታይ የሚፈጠር ስሜት ወይም ነገሮችና ሁኔታወች ከቁጥጥራችን እንደወጡ ስናስብ የሚፈጠር ስሜትም ስለሆነ ነው፡፡

በሌል በኩል የሰውልጅ በጭንቀት ውስጥ ሲሆን ከመከላከል ሥነልቡና /Defense mechanism/ ጋር በማያያዝ የተሸለ ሃሳብ እንደሚኖረው ይገለጻል ፡፡ "anxiety can be an important experience because it can reveal our core issue. Anxiety can tell us agood deal about ourselves because we are anxious situation in which our core issues are in play. (ታይሰን፣2006፣17)

ታይሰን(2006) ኮር ኢሹ/core issue/ በማለት የገለጸቻቸው የሞት ፍርሃት መገለጫዎች በሚል ከላይ ያየናቸው የመቀራረብ ፍርሃት /Fear of Intimacy/ ፣የመገለል ፍርሃት /Fear of Abandonment/ ፣የመክዳት ፍርሃት /Fear of Betrayal/ ፣ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር/ Low self Esteem ፣የማያስተማምን ወይም ያልተረጋጋ ስሜት /Insecure or Unstable

sence of self/ እንደሆኑ ገልጻለች፡፡ ዝኒ ከማሁ(ገጽ16)፡፡ ጭንቀት ሊጠቅም የሚችል ገጠመኝ ወይም ልማድ የሚሆነው በጭንቀት ውስጥ በምንሆን ጊዜ የተሸለ ሃሳብ አመንጭተን ከጭንቀታችን ስንወጣ ነው፡፡ ነገር ግን በእንቅልፍ እና እድሜ ልብወለድ የሚታየውን የሥነልቡና ቀውስ /ጭንቀት/ ለመከላከል ገጸባህሪያቱ ከፍተኛ ጥረት ሚያደርጉ ቢታይም ተከላክለው ሲድኑ ሳይሆን ለባሰ የሥነልቡና ሞትን ሲጋለጡ ነው፡፡

Hawassa online.com ድህረ ገጽ እነዳስነበበው ጭንቀት በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ጉዳት የተለያየ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ጥናቱ በሴቶች ላይ አዕምሮን በጣም የሚያሳቅቅ ወይም የሚረብሽ ነገር በሚያጋጥምበት ጊዜ "ኢንሱላ" የተባለው ስሜትና ችግርን የሚመለከት እንዲሁም የሚለካ የአዕምሮ ክፍል ከተለመደው መጠን በታች እንደሚያንስ እንዳመለከተና በአንጻሩ የወንዶች አእምሮ የሚያሳቅቅ ወይም የሚረብሽ ነገር በሚገጥምበት ጊዜ "ኢንሱላ" የተባለው የአእምሮ ክፍል ከተለመደው መጠን በላይ ጨምሮ እንደሚገኝ ጥናቱ ይገልጻል፡፡ በጥናቱ መሰረት ይህ የሚያሣቅቅ ወይም የሚረብሽ ነገር በሚያጋጥምበት ጊዜ ሴቶች ከወንዶች በበለጠ ለጭንቀት እንደሚጋለጡ ያመላክታል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ይህን ይበል እንጂ በእንቅልፍና እና እድሜ ልብወለድ በተቃራኒ ጭንቀቱ በወንዶቹ ላይ ጨምሮ ይታያል፡፡

እንደ ፍሮይድ አገላለጽ "የአሁኑ ማንነታችን የትናንቱ አስተዳደጋችን ውጤት ነው፡፡ እነዚህ የትናንት ገጠመኞቻችን በተለይ ሶስቱ ወሳኝ እንደሆኑ ይገልጻል ፡፡ እነዚህም ልጅነታችን ያለፈበት ሂደት ፤ደመነፍሳዊ ተነሳሽነታችን እና በህይወታችን በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠሙን ችግሮች ናቸው"፡፡ /ገጽ፣408/፡፡ በነዚህ ሂደቶች አልፎ የተገነባው ስብእና ሁልጊዜ እንደተመቸው ዓለም አልጋ በአልጋ አትሆንለትም፡፡ በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች ለመፍትሄ የሚቸገርበት፤የጭንቀት አደጋ የሚጋረጥበት ለራሱ ይሰጠው የነበረው ግምት ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት አጋጣሚ ይከሰታል፡፡የተለያዩ ሰዎች ስለ ጭንቀት ምንነት የሰጡት ብያኔ ማየት ያስፈልጋል፡፡

> ጭንቀት ማለት ሰዎች ከተገቢው ስጋት ውጭ የሚኖራቸው ጤናማ ያልሆነ ሀሳብ ነው፡፡ በውስጣችን ካለው ተፈጥሯዊ ስሜት ውጭ አግባብነት የሌለው ስጋት ነው፡፡ ጭንቀት የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል /worry/ የመጣው ከአንገላ ሳክስ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ መታነቅ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ብዙ ሰወች ለጉዳት በሚያደርስ ጭንቀት ይታነቃሉ፡፡ ደግሞም አዕምሯችን ልንመልሳቸው በማንችላቸው አልያም አግባብ ባልሆኑ ጥያቄዎች

> ተሞልቶ ነፍሳችን እስክትቃትት ድረስ በውስጣችን የሚተራምስ ውል የሌለው ሀሳብ ጭንቀት አልያም ብስጭት ልንለው እንችላለን፡፡ (የሽጥላ፣ 2001፣1)

በሌላ በኩል ገብሬ (2010) እነ ኪየር ጋርድ 1980፣ ዋቢ በመጥቀስ ስለጭንቀት ሲያስረዱ "የሰው ልጅ ህልውና በራሱ እውቅና የመፍጠር ሁኔታ ነው:: የሰው ልጅ ከጭንቀት አይወጣም ይሁን እንጅ ጭንቀት ለሰው ልጅ ማበብ የራሱ የሆነ በጎ ሚና አለው፡፡ የሰው ልጅ በጣም በጭንቀት ውስጥ በሆነ መጠን ትልቅ ሰው ይሆናል፡፡" ሲል ያስረዳል፡፡

ይህ የሰው ልጅ ባህሪ የሆነው ጭንቀት ደግሞ አላስፈላጊ ባህሪ ቢሆንም ነገር ግን ሰው ከገባበት አላስፈላጊ ጭንቀት፣ ስጋት፣ ፍርሀት፣ ለመውጣት ሲል የሚያደርገው ጥረት ሁሉ የሰው ልጅ የተሻለ ነገር እንዲፈልግ የሚያደርገው ስለሆነ በጎ ሚናም እንዳለው መረዳት እንችላለን ፡፡ ጭንቀት በተለያየ መንገድ ሊከሰት እንደሚችል ይገጻል፤

> ጭንቀት ከማሰብ አቅም በላይ ማሰብ ፤ የሚያስቡትን የሚያስረግጡበት እምነት ማጣት ፤ ባለፈ ወይም ይፈጠራል ብለው ከሚገምቱት አንድ ሁኔታ በፍርሀት መዋጥ፤ በመጠኑ መኖርን ጠልቶ ስለ ነገ ከማሰብ ፤ ለማይመለስ ነገር ከማሰብ ዘንድ ብዙ ጊዜን ማጥፋት ፤ የደስታን ምንጭ አለማወቅ ፤ተስፋ ቢስ ከመሆንና ተስፋ ከመቁረጥ፤ ጤናማ ካልሆነ ባልንጀርነት ናቸው:: (የሽጥላ ፤2001፤4)

የሰው ልጅ ከአቅሙ በላይ ማሰብና እምነት ማጣቱ፣ በፍርሀት መዋጡ፣ ላለፈ ነገር ማሰብ ወይም መጨነቁ ተስፋ ቢስ መሆኑ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነቱን በተገቢው መቆጣጠር ካልቻለ የመጨረሻ ውጤቱ ከነበረ ጤናማ ማንነት አስወጥቶ ለሥነ ልቡናዊ ሞት የሚያጋልጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ጭንቀት የሚጎዳው ግለሰቡን ብቻ አይደለም፡፡ ጭንቀት በሌሎችም ላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚአዊ ችግር ያስከትላል፡፡ "ሰላማዊና የተረጋጋ ህይዎት የሌለው የሚበሳጭና የሚጨነቅ ሰው የራሱን ውስጣዊ ሰላም ያጣና የሌሎችንም ውጫዊ ሰላም የሚያናጋ ነው" ይላል ፡፡ዝኒ ከማሁ ገጽ፤39/

### 2.2.3.2. ቀቢጸ ተስፋ /Despair/

ተስፋ መቁረጥ የሰው ልጅ ባህሪ ሲሆን ተስፋ እንዲቆርጥ የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ የተሻለ ሁኖ ለመገኘት የህይወት ጉዞውን እውን ለማደረግ የሚችለውን ነገር ለመፈጸም በተስፋ ይጓዛል፡፡ ራዕዩን ወይም ሀሳቡን ለማሳካት ያቅዳል በተስፋ ተገባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ ያለውን ሁሉ ይሞክራል፡፡ በሂደት ላይ እያለም ሆነ በተለያየ ጊዜ በተፈጥሮም ሆን በሰው ሰራሽ ችግር አላማውን

የሚያደናቅፍ ተስፋውን የሚያጨልም አንዳች ነገር ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህን የገጠመውን አንዳች ነገር ተቋቁሞ ማለፍ ሲያቅተው እንደገጠመው ችግር ክበደት አስፈላጊ ወዳልሆነ ጭንቀት፣ ብስጭት እና ፍርሃት ይገባል፡፡ እነዚህ አላስፈላጊ ባህርያት ደግሞ የሥነ ልቡና ቀውስ በመፍጠር አላማውን ያስቱታል ራዕዩን እንዲነጠቅ በማድረግ እና ተስፋ ቢስ በማድረግ ተስፋ ያስቆርጡታል፡፡

> እኔ ተስፋ የለኝም እንዲህ አይነት ሰው ስለሆንኩ እድን ዘንድ አልችልም፣ የእኔ መኖር ትርጉም የለውም፣ እግዚአብሄር ሳይቀር ተቶኛል ፣ የምጠቅም አይነት ሰው አይደለሁም በማለት እስከ መጮህ ያደርሳል፡፡ ሌላው ታሞ እንደሆነ መዳን ፣አጥቶ እንደሆነ ማግኘት፣ ለምኖ እንደሆነ መቀበል፣ ፈልጎ እንደሆነ ማግኘት፣ እንደማይችል እንዲያስብና እንዲጨነቅ በማድረግ ተስፋ ማስቆረጥ ነው፡፡ በሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ላይ የሚደረገው ተስፋ መቁረጥ እለት ተእለት የሰውየው ህይዎት በመታወክና በጭንቀት እየተመታ እንዲዋለል ያደርገዋል፡፡ /2001,18-19/

በማለት ተስፋ መቁረጥ እና ተስፋ ቢስነትን ይገልጻል፡፡ ተስፋ በመቁረጥ ከራዕያቸው ሳይደርሱ ህልማቸው ከንቱ ሆኖ ስለሚቀርባቸው ሰዎች

> የርዕይ መነጠቁ ብዙ ሰዎችን ቀቢጸ ተስፋ ላይ ስለሚጥላቸው ወፈፍ እያደረገ የሚሰሩትን ያሳጣቸዋል፡፡ በአስፈሪና በአስጨናቂ የአሟሟት ትዕይንት ይጥላቸዋል፡፡ ----አሳደው በብዙ ድካም የያዙት ተስፋ ድንገት ነው ከእጃቸው የሚያመልጠው ፡፡ ሁሉም የስኬትን ደፍ ረግጠው ይመለሳሉ፡፡ ይህ ደግሞ የርዕይ መነጠቁ ያጠልቀዋል፡፡ ቀቢጽ ተስፋውን ያከረዋል፡፡ የአለም ከንቱነት የህይዎት ፍሬ ከርስኪ የተገለጠላቸው ይመስል ዳግሞ አያልሙም ዳግሞ አያደርጉም፡፡ በተፈጥሮም ይባል በአምላክ ፊት አቅም ቢስ መሆናቸውን ተረድተው እጅ ይሰጣሉ፡፡ሲል ገልጿል፡፡(ቴዎድሮስ 2001፣165 እና172)

ተስፋ መቁረጥ የሥነልቡና ሞት መገለጫ ነው ሲባል የሰው ልጅ በእለት ተዕለት እንቅስቃሴው በሚያጋጥመው ቀውስ የገጠመውን ችግር ማለፍ ሲያቅተው የሚከሰት ነው፡፡ የመኖር ተስፋው ሲጨልምበት ከእንግዲህ ተስፋ የለኝም ብሎ ሲያምን ነው፡፡ ተስፋ የቆረጠ ሰው ከላይ እንደሚታየው ታሞ እንደሆን መዳን፣አጥቶ ከሆነ ማግኘት፣ ለምኖ እንደሆነ መቀበል እንደማይችል እንዲያስብ እና እንዲጨነቅ በማድረግ አዕምሮው እንዲታወክ ያደርገዋል፡፡የሥነልቡና አልባነት ስሜት እንዲሰማው በማድረግ ከመደበኛ ማንነቱ አስወጥቶ ለቀጣይ ህይወቱ እንዳያስብ እና እንዳያልም ስለሚያደርገው ነው፡፡

### 2.2.3.3. ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር /Low Self Esteem/

እንግዲህ ራዕዩን በመነጠቁ የኔ መኖር ተስፋ የለውም በሚል ተስፋ የቆርጠ ሰው ለራሱ ዝቅተኛ ክብርና ዋጋ /low seif steem/ ይሰጣል፡፡ እራሱን ያዋርዳል፡፡ ራሱንና ህይወቱን እንዳያስቀጥል የስነ ልቡና አልባነት ስሜት እና የህይወት ትርጉም ማጣት አይነት ባህሪዎች ይከሰቱበታል፡፡ እኔ በሌሎች ዘንድ ፍቅርና ትኩረት የተነፈገኝ ወይም ላገኝ የማይገባኝ ስለሆንኩ ቅጣት ነው የሚገባኝ የሚል እምነት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ይህንንም " Low self esteem- the belief that we are less worthy than other people and therefor, do not deserve attention, love or any other of life's rewards. Indeed, we often belives that we deserve to be punished by life in some way. (ታይሰን 2006, 16)

ተስፋ የቆረጠ ሰው ለራሱ ከሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት /ዋጋ/ አንጻር በቅርበት የሚያውቃቸውን ሰዎች ሳይቀር እንዲፈራ እና ከሰዎች እንዲርቅ ከማድረጉም በላይ ሌሎች ሰዎችም ለሱ ዝቅተኛ የሆነ ስሜት እና አመለካከት አላቸው ብሎ የማሰብና የመገንዘብ እድሉን ያሳድገዋል፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ራዕዩን ሲነጠቅ ያሰበው አላማ ከግቡ ሳይደርስ ሲቀር ተስፋ ይቆርጥና ለራሱ ዝቅተኛ ክብርና ዋጋ በመስጠት ሰዎች ለሱ ጥሩ አመለካከት እንደሌላቸው በማሰብ በጨለምተኝነት አስተሳሰብ ውስጥ በመውደቅ ራሱን የሚሰጠውን ክብርና ዋጋ ያሳንሳል ፡፡ በዚህ የተነሳ ለራሱም ሆነ ለማህበረሰቡ ባይታወር ይሆናል፡፡

> *የራዕይ መነጠቁ ብዙዎችን ቀቢጸ ተስፋ ላይ ስለሚጥላቸው ወፈፍ እያደረገ የሚሰሩትን ያሳጣቸዋል በአስፈሪና በአስጨናቂ የአሟሟት ትዕይንት ይጥላቸዋል፡፡... ከዚህ እውነታ የሚገጥመው ሌላው ጉዳይ በእውንና በህልም መሃል ያለው ድንበር መፍረስ፤ የሁለቱ አለማት መቀያየጥና መደበላለቅ ነው፡፡ በተቀየጠውና በተደበላለቀው አለም ውስጥ የገጸ ባህርያቱ ህይዎት ወደ ህልምነት ይቀየራል፡፡ ፍጹም ግራ ይጋባሉ፡፡ የሚያደርጉትን አያውቁም ፡፡ የሚደረግባቸውን ለመቆጣጠር አይችሉም፡፡* (ቴዎድሮስ 2001፤165 እና 171)

በሌላ በኩል ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምት ወይም ዋጋ የሚመጠው ራስን ካለማክበርና ራስን እንደ እርባና ቢስ ሰብአዊ ፍጡር ከመመልከት እንደሆነ፤ ራስን ማክበር ወይም ለራስ ከፍተኛ ግምት መስጠት ሁሌም የመሪነቱን ሚና እንደሚጫዎት ፤ በተለይም ውሳኔዎች የሚዎሰኑት ከሚያስገኙት ጠቀሜታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ራስን የማክበር

ስሜትን ከማርካት አንጻር ጭምር እንደሆነ ፤ ለራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ያላቸው ሰዎች በአብዛኛው የማንነት /የስብእና/ ቀውስ ያለባችው ራሳቸውን ለማግነት ብርቱ ፍለጋ ላይ ያሉ እንደሆኑና የራስ ማንነት ደግሞ የሚፈጠር እንጂ የሚገኝ ነገር እንዳልሆነ ማህሌትና ዳኝ(2001፤95ና96 ) ገልጸዋል፡፡

ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር የሥነልቡናዊ ሞት መገለጫ ጭብጥ ነው ሲባል አላይ እንደተገለጸው በእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ በተለያየ ምክንያት የሚያጋጥም ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እን ርዕዮተ ዓለማዊ ቀውስ ምክንያት የሰው ልጅ ለተለያዩ ፈተናዎች ይጋለጣል፡፡ ፈተናውን ወይም ያጋጠመውን የስነ ልቡና ቀውስ ማለፍ ሲያቅተው ይፈራል፣ይጨነቃል፣ ጭንቀቱ ከአቅሙ በላይ ሲሆን ተስፋ ይቆርጣል፡፡ ተስፋ መቁረጡ ደግሞ ከጤናማ ሥነልቡናዊ ማንነቱ አስወጥቶ የሥነ ልቡና አልባነት እንዲሰማው፤ ለህይወት ትርጉም እንዳይሰጥ፤ ስለነገ እንዳያስብ፣ እንዳያልም ያደርገዋል፡፡ የራሱን ማንነት ይረሳል ራሱን ዝቅ አድርጎ ይመለከታል፡፡ እኔ በሰዎች ዘንድ ትኩረት ፣ፍቅር የተነፈገኝ ነኝ በማለት የራሱን ውስጣዊ ሰላም ያጣና የሌሎችንም ውጫዊ ሰላም ያናጋል፡፡ ለኔ የሚገባኝ ቅጣት ነው በማለት በራሱ ላይ ያልተገባ ውሳኔ ይወስናል ማለት ነው፡፡

በጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ተከትሎ የርዕሰ ጉዳዩ መገለጫዎችን ምንነትና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ያላቸውን ዝምድና ከተለያዩ ስራዎችና ብያኔዎች አንጻር ካየን ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችን መዳሰሱ አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

በዚህ ክፍል ለማየት የተፈለገው ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በርዕሰ ጉዳይ፣ በቴክስት መረጣ ይሁን በንድፈ ሃሳብ ቅኝት የተቃርቦ ዝምድና ወይም የመጠራራት ባህሪ ይታይባቸዋል የተባሉ ቀደምት ጥናቶችን በመፈለግ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸውን እና የሚያለያያቸውን ጉዳይ ለይቶ ማሳየት ነው፡፡ የጥናቶቹ መረጃዎች ይገኙባቸዋል የሚባሉ ሁሉንም የመረጃ ምንጮች ሙሉ በሙሉ አይቻለሁ የሚል እምነት ባይኖረኝም የቻልኩትን ያህል ለመፈተሽ ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ ባደረኩት ፍተሻም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመመሳሰል ባህሪ ይታይባቸዋል በሚል ሦስት

የሚሆኑ  ስራዎችን አግንቻለሁ :: ጥናቶቹም በተጠኑበት ዓ.ም ቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የቴዎድሮስ አለበል (2006) "ልጅነት በማህሌት አለንጋና ምስር ሥነልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ በአዳም ረታ ስራዎች ላይ፤ሁለተኛው የእዩኤል እንደሻው(2010) "ድብቅ ባህሪያትና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ሥነልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ በአለማየሁ ገላጋይ ስራ በሆነው ቅበላ ልብወለድ ፤ ሦስተኛው የገብሬ ባይሌ(2011) "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና" በሚል ርዕስ በበእውቀቱ ስዩም የግጥም መድበሎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ናቸው፡፡

በአንደኛ  ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር የተመሳሰሎ ቀረቤታ አለው በሚል የተመረጠው የቴዎድሮስ አለበል "ልጅነት በማህሌት አለንጋና ምስር ሥነ ልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ በ2006 ዓ/ም ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤምኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ 71 ገጾች ያሉት ሲሆን በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ አዳም በማህሌት እና አለንጋና ምስር "ልጅነት" በእንደምን አይነት ሥነ ልቡናዊ እሳቤዎች፣ በተለይም ስብዕናን እንደሳለ በይነ ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም የሚል ዋና ዓላማ ይዞ የተደረገ ጥናት ሲሆን በንዑስ አላማነት የልጅነት ማህበረ-ልቡናዊ ስብዕናን መተርጎም፣ ሥነ ልቡናዊ ቀውሶችን መመርመር፣ የፍሮይድን የ"ሳይኮ ሴክሽዋል" አቀራረብን በመመርመር የተጨቆኑ ፍላጎቶችን መፈለግ…የሚሉትን ንዑሳን አላማዎች መነሻ በማድረግ እና ጥያቄያዊ ይዘት እንዲኖራቸው ከማድረግ ውጭ አላማዎቹን መልሶ የምርምሩ ጥያቄዎች በማድረግ የተደረገ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ በምዕራፍ አንድ በመግቢያው ስር የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምሩ ጥያቄዎች፣ ጠቀሜታ እና ወሰን የያዘ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት በማድረግ የልጅነት ጽንሰ ሃሳብና ልጅነትን ለመመርመር የሚያስችሉ የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦችን ዳስሷል፡፡ በዚህም ልጅነት በርካት ጉዳዮችን ዘንቆ የሚይዝ እንደሆነ የኤሬክሰንን ማህበረ ልቡናዊ እድገት፤ የፍሮይድን ባዮሎጅካዊ የሳይኮ ሴክሽዋል ንድፈ ሃሳቦችንና የስብዕና መዋቅሮች የላካንን የቋንቋና ልጅነት ማህበራዊ ጉዳዮችን እና ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች በማጣቀስ አሳይቷል፡፡

በዘሁ ክፍል በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ከሱ ጥናት የመጠራራት ወይም የመመሳሰል ባህሪ ኣላቸው ያላቸውን ጥናቶችና ጆርናሎች በመምረጥ ተመሳስሎአቸውን እና ልዩነት ያለውን አሳይቷል፡፡ በምእራፍ ሶስት አጠቃላይ የጥናቱን ትንታኔ የሰራበት ሲሆን ለስረው በመረጣቸው ሁለቱ ቴክስቶች ውስጥ በሚገኙ አራት ታሪኮችን መነሻ በማድረግ የልጅነት ማህበረ ልቦናዊ ማንነትና የአሳዳጊዎች ሚና ፣ልጅነት ማህበረ ባህላዊ ፍንገጣ፣ የጨቅላነት ግንትሮሽ እና የሁለቱ ስብእናዎች መቀያየጥ፣ Oedipus complex እና የልቦና ፍርቅነት የሚሉ ጭብጦችን በመለየት ለጭብጦቹ ማሳያነት ይሆናሉ የተባሉትን ከታሪኮቹ በመምዘዝ ትንታኔውን ሰርቷል፡፡

በምዕራፍ አራት ጥናቱን ያጠቃለለበት ሲሆን በማጠቃለያውም አዳም በታላሚ ቴክስቶቹ ሥነ ልቡናዊ ጽንሰ ሃሳቦችን እያለመደ እንደሚጽፍ  ጽንሰ ሃሳቦችን ለማልመድ ባህለዊና ሚታዊ አስተማስሎዎችን እንደ ኪናዊ ማስዋቢያነት እንደሚጠቀም፣  የሚስላቸው ገፀ ልጆችም የኤሪክሰንን "ማህበረ-ልቦናዊ" እና የፍሮይድን የ"ሳይኮሴክሽዋል" የእድገት ደረጃዎች በአፍራሽ ጎኑ የሚያጠናቅቁ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡ ይህ የእድገት መታጎል ኢሉታዊ መሆን ከአሳዳጊ ማንነት የሚመጣና ስብዕናቸውም በዚህ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ልጆች ማህበረ ባህላዊ ፍንገጣ የሚስተዋልባቸው፣ ለማህበራዊ ሃላፊነት ብቁ ያልሆኑ፣ በራሳቸውም ሆነ በአካባቢያቸው የማይተማመኑ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የተመሳሰሎ ባህሪ አለው በሚል እንዲመረጥ ያደረገው ዋና ጉዳይ ሁለቱም ሥነ ልቡናዊ ንባብን መጠቀማቸውና የዕድሜ ደረጃ ይለያያቸው እንጂ በሰው ልጅ የስብዕና ባህሪ ላይ የሚያጠነጥኑ መሆናቸው ነው፡፡ ቴዎድሮስ በመረጣቸው ቴክስቶች ሥነ ልቦናዊ ንባብ በማድረግ ልጅነትን ከአሳዳጊዎች ሚና ጋር አጣምሮ የመረመረ ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ በተመረጠው ቴክስት ላይ ሥነ ልቡናዊ ሞት ተመርምሯል ፡፡ ለአሁኑ ማንነታችን የትናንቱ አስተዳደጋችን ውጤት ነው ከሚለው የፍሮይድ አገላለጽ አንጻር በሥነ ልቡናዊ ንባብ በልጅነታችን ያለፍንበት ደመነፍሳዊ ተነሳሽነት በወደፊቱ ማንነታችን ላይ ከሚኖረው ተጽዕኖ አንጻር በተገቢው ማየቱ ጠቃሚ በመሆኑ የልጅነት የስብዕና ጥናትን መቃኘቱ  ተመሳስሎውን ያጎለዋል ከሚልም እምነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ልጅነትም ሆነ ሞት በሥነ ልቡናዊ ንባብ የሚመረመረው በሰው ልጅ ላይ በንቁም ሆነ በኢ-ንቁ አዕምሮ ውስጥ የሚርመሰመሱ ሰዋዊ ባህርያት መሆኑ የሚያመሳስላቸው ሌላው ባህሪ ነው፡፡ ቴዎድሮስ የኤሬክሰንን ማህበረ ልቦናዊ እድገት

መሰረት በማድረግ ያያቸው ሥምንት ደረጃዎች ውስጥ ወደ መጨረሻው ያሉት ሦስቱ ደረጃዎች ልጅነትን አልፈው የሚታዩ ባህርያት መሆናቸው ለሁለቱ ጥናቶች መመሳሰል አስተዋጽኦ አለው፡፡

ሁለቱ ጥናቶች የሚያመሳስላቸው እንዳለ ሁሉ የሚያለያያቸውም ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከሚለያዩባቸው ጉዳዮች ውስጥ በርዕሰ ጉዳይ፣ በቴክስት መረጣ እና በሚጠቀሙት የመተንተኛ ስልት ይለያያሉ፡፡ ቴዎድሮስ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ልጅነትን፤ ከቴክስት መረጣ አንጻር የአዳም ረታ ስራዎች የሆኑትን ማህሌትን እና አለንጋና ምስርን የተጠቀመ ሲሆን ከትንተና ስልት አንጻር በይነ ዲሲፕሊናዊ ንባብ በማድረግ የትርጉም ፍርቀቃን መሰረት ተደርጎ የተጠና ነው ፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ በተመረጠው የበውቀቱ ስዩም እንቅልፍና እድሜ ልቦለድ ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ የቴክስትና የሃቲት ትንታና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ቴዎድሮስ ልጅነትን በተለያዩ ዲሲፕሊኖች የተለያዩ አንጻሮችን በመታገግ ታሪካዊ ፣ ሥነ ልቡናዊ ፣ ሥነ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን ተከትሎ የመረመረ ሲሆን በዚህ ጥናት " The meaning of death" ን ወይም  ሞትን ሥነ ልቡናዊ ንባብን መሰረት በማድረግ በራሱ በተመረጠው ቴክስት ላይ ብቻ የተደረገ ፍካሬያዊ ትንታኔ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት ጋረ የቀረበ ተመሳስሎ አለው በሚል በሁለተኛ ደረጃ የታየው የእዩኤል እንደሸው "ድብቅ ባህሪያትና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ሥነ ልቡናዊ ንባብ"  በሚል ርዕስ በ2010 ዓ/ም ለ2ኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ 52 ገጾች ያሉት ሲሆን በ4 ምእራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው:: ጥናቱ የአለማየሁ ገላጋይ ስራ የሆነውን "ቅበላ" እረጅም ልቦለድ ውስጥ ሥነ ልቡናዊ እሳቤዎች በተለይም ስብእና እንዴት እንደተሳለ ማሳየት ዋና ዓላማ በማድረግ ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ሥነ ልቡና ገጽታዎች የሲግመን ፍሮይድን የትንታኔ ሥነ ልቡና የልቦለዱ አበይት ገጸ ባህሪያት በኢንቂ ባህሪያቸው ተጽእኖ የሚስተዋልባቸው ሥነ ልቡናዊ ቀውሶችን፤ የፍሮይድን ሳይኮ ሴክሸዋል አስቦቶች አቀራረብን በመመርመር የተጨቆኑ ፍላጎቶችን መመርመር ሥነ ልቡናዊ ገጽታዎቹ ጭብጡን እንዴት እንደመሰረቱት እና ለስነ ጽሑፍ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ትኩረት አድረጎ እነደሚያጠና ንዑሳን አላማዎቹ አድርጎ የተሰራ

ጥናት ነው፡፡ እነዚህ አላማዎች ተመልሰው ጥያቄያዊ ይዘት እንዲኖራቸው ተደርጎ የጥናቱ ጥያቄዎች ሁነው ቀርበዋል፡፡

በምእራፍ ሁለት የሲግመን ፍሮይድንና የሌሎችን ትንታኔ ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ የጥናቱን ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ቀንብቧል፡፡ አንድን የሥነ ጽሑፍ ስራ ለመረዳት የሥነ ጽሑፍ ስራውንና የደራሲውን ቁርኝት ከሶስት አቅጣጫዎች መረዳት እንደሚቻል ያሳያል፡፡ ሶስት አቅጣጫዎች ያላቸውም የደራሲውን ስብእና ተተኳሪ በማድረግ ስብእናውን ለመረዳት ስራዎቹን መፈተሽና እንደ ግለ ታሪኩ አድርጎ መገንዘብ፤ የደራሲውን ልዩ አስተውሎት እና የአዕምሮ ቅኝት ነጸብራቅ መሆኑን ለመመርመር የሥነ ጽሑፍ ውጤቱን የአነባበብ ስልት ከደራሲው ማንነት ጋር አስተሳስሮ ማየት የሚሉ ስልቶችን እንደሚከተል አስቀምጧል ፡፡

ትንታኔ የሚደረግባቸው ጉዳዮች ጋር የቅርብም ይሁን የሩቅ ተዛምዶ አላቸው በሚል ተቋቁሞ ፣ስጋት፣ ለራስ ያለ ግምት ማነስ፣ ተጋላጭና ያልተረጋጋ የማንነት ስሜት ፣ የኤዲፐስ ተጣብቆ ፣ ህልምና ፍችው ፣ ሞት ፣ ትዕምርት ፣ ገንቢና አፍራሽ ማህበራዊ ሥነ ልቡና ገጽታዎች ፣ ወሲባዊ ግፊትና የስብእና መዋቅሮች የሚሉ ንዑስ ርዕሶችን በመለየት እያንዳንዳቸውን ከሥነ ልቡና ሂስ አንጻር በማየት ምንነታቸውን ተንትኗል፡፡

በተዛማጅ ጥናት ቅኝቱ በርዕስ ጉዳይ እና በቴክስት እንዲሁም በደራሲው ሌሎች ስራወች ላይ የተሰሩ ከሱ ጥናት ጋር የተመሳሰሎ ዝምድና ያላቸው ጥናቶችን ወይም ድርሳናትን ባለማግኘቱ የንድፈ ሃሳብ ዝምድና አላቸው የተባሉ ጥናቶችን እንዳየ አመላክቷል፡፡ የንድፈ ሃሳብ ዝምድና አላቸው በሚልም ሁለት ጥናቶችንና አንድ መጣጥፍ በመምረጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሁሉም የሲግመንድ ፍሮይድን የንድፈ ሃሳብ ቴዎሪ በመጋራታቸው የሚያመሳስል ዝምድና እንዳላቸው አሳይቷል ፡፡

በምእራፍ ሶሰት የቅርብም ሆነ የሩቅ ዝምድና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር አላቸው በሚል በምዕራፍ ሁለት የመረጣቸውን ጽንሰ ሃሳቦች በከፊል እና ሌሎችንም አስፈላጊ ናቸው የተባሉ እንደ ግብረ አምኖን፣ ስድብና ስካር ፣ አቅጣጫ ማሳትና ማላከክ የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን በመጨመርና በማሻገር በንድፈ ሃሳብ ትንተናው በተገለጸው ምንነታቸው መሰረት ከተመረጠው "ቅበላ" ልብ ወለድ ከጥናቱ አላማ አንጻር ሊገልጹ የሚችሉ ማሳያዎችን በመምዘዝ ትነታኔውን አካሂዷል፡፡ የገጸ ባህሪያቱን ድብቅ ባሁሪያትና የተጨቆኑ

ፍላጎቶችን ከሥነ ልቡና አይን በማየት ያቀረባቸው ማሳያዎች አላማውን በማሳካትና ጥያቄውን በመመለስ ተሳክቶለታል ለማለት ያስደፍራል፡፡

በማጠቃለያው ስለ ጥናቱ ውጤት /ግኝት/ ሲያጠቃልል ቅበላ ጥልቅ ሥነ ልቡናዊ ገጽታ የሚንጸባረቅበት ልብ ወለድ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ የትረካ አቅጣጫው በአንደኛ መደብ ጀምሮ የዋናው ገጸባህሪ የህሊና ምስቅልቅል ከሌሎች ገጸ ባህሪያት ጋር ያለውን መስተጋብር ከሱ አኳያ ካሳየ በኋላ እንደገና በሶስተኛ መደብ የትረካ አንጻር ድርጊትን ከሀሳብ፣ ንግግርን ከስሜት እያቀናጀ የገለልተኛ ተመልካች እይተውን የሚያሳየን የሥነ ልበና ጫናው በሚፈጥረው ችግር እንደሆነ አሳይቷል፡፡ በልብ ወለዱ ውስጥ ጉልህ ሆኖ የሚታየው አቢይ የሥነ ልቡና ቀውስ ምንጩ፣ በጽኑ ፍቅር ምክንያት እና ባልተለመደ ሁኔታ ከቤተ ዘመድ ጋር በፍቅር መውደቅ ዋና ዋና መከሰቻዎቹ ሲሆኑ ይህን ተከትሎ የሚከሰተው መገዳደል ፣ መለየት፣ መረሳትና መገለል የሚፈጥረው ሥነ ልቡናዊ ግፊት ነው ሲል አረጋግጧል፡፡ በጥቅሉ በልብ ወለዱ የመለየት ፍርሀት አካል ገዝቶ ስጋ ለብሶ ይታያል ሲል ደምድሟል፡፡

የኢዩኤል ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የተመሳሰሎ ዝምድና አለው እንድል ያደረገኝ የሲግመንድ ፍሮይድን የሥነ ልቡናን ንድፈ ሃሳብ ሁለታችንም መጠቀማችንና ለርዕሰ ጉዳያችን ንድፈ ሃሳብ ማሳያነት የመረጥናቸው የጽንሰ ሃሳብ ንኡሳን ርዕሶች ብዙዎቹ ተመሳስሎ ስላላቸው ነው፡፡ እኔ ሞትን ይገልጻሉ በማለት የለየኋቸውን ኢዩኤል ደግሞ ድበቅ ባህሪያትንና የተጨቆኑ ፍለጎቶችን ያሳያሉ በሚል የመረጣቸው እንደ ፍርሃት ፤ጭንቀት ፤ክህደት ፤ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምት ያሉት የተመሳሳይ በሃሪነትን አጉልተው ያሳያሉ ፡፡

ልዩነታችን ደግሞ ከርእሰ ጉዳይ አኳያ ድብቅ ባህሪያት እና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ከሥነ ልቡናዊ ሞት ጋር የመጠራራት ባህሪ ሊኖራቸው ቢችልም ኢዩኤል የተደበቁ ፍላጎቶችን የሲግመን ፍሮይድን የህልም እና ሳይኮ ሴክሽዋል ንድፈ ሃሳብ ተከትሎ ያየ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ሞትን The meaning of death / ከሞት ትርጉም አንጻር ማየታችን ፤ የቴክስት ምርጫችን እና እዩኤል ሞትን በንኡስ ርእስነት መርጦ ከመገዳደል ጋር አያይዞ ያየው ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ ሞት በአቢይ ርእስነት ተመርጦ አካላዊ ሞትን ሳይሆን ሥነ ልቡናን መሰረት ተደርጎ የሚታይ መሆኑም አንዱ የልዩነቱ ማሳያ ነው፡፡

ሌላው በሦስተኛ ደረጃ በተዛማጅ ጽሑፍነት የታየው የገብሬ ባይሌ "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በእሳት ዳር ሃሳቦች፣ ኗሪ አልባ ጎጆዎች እና የማለዳ ድባብ ግጥም መድበሎች" በሚል ርእስ በ2011 ዓ/ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በግጥም መድበሎቹ ላይ የሚገኙትን የህልውናዊነት ጭብጦች በመተንተን ማሳየት የሚል ዋና ዓላማ ይዞ የተነሳ ሲሆን ከዋናው አላማ ብዙም ያራቁ ንኡሳን አላማዎችም አሉት፡፡ ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በምእራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፍና የቀደምት ጥናት ቅኝት በተደረገበት የህልውናዊነት ምንነትን በስፋት በማየት የህልውናዊነት ዋና ዋና ጭብጦች በሚል ባይታወርነት፣ ነጻነት፣ የፍልስፍና ህይወት መንገድ ፣ ጭንቀት ፣ ሞት ፣ ፍቅር ፣ ቀቢጸ ተስፋ እና ስደት ወይም ግዞት የሚሉትን በመለየት ለእያንዳንዳቸው ከተለያዩ የሥነ ጽሁፍ ቲዎሪና ከተለይዩ ምሁራን ስራዎች በማጣቀስ ከብያኔአቸው በመነሳት ከህልውናዊነት ጋር እንዴት ሊዛመዱ ወይም ሊጠራሩ እንደሚችሉ አሳይቷል፡፡

በምእራፍ ሦስትም ትንተናውን ሲያደርግ በምዕራፍ ሁለት የህልውናዊነት መገለጫ ጭብጦች በሚል የመረጣቸውን በማሻገር በግጥም መድበሎቹ ውስጥ እንደተጠቀሱበት የብዛት መጠን ደረጃ በማውጣት ጭብጦቹን ይገልጻሉ የተባሉ ግጥሞች ከየመድበሎቹ በመምረጥ ህለውናዊነትን ይገልጻሉ በተባሉ ጭብጦችና በርዕሰ ጉዳዩ መካከል ስላለው ግንኙነት ለማሳየት የተደረገው ጥረት ጥሩ የሚባል ነው፡፡ የገብሬ ባይሌ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የመመሳሰል ወይም የመጠራራት ባህሪ አለው ተብሎ የተመረጠበት ምክንያት ሁለቱም ጥናቶች የተጠቀሙት የሥነ ጽሑፍ ስራ በዘውግና በርዕሰ ጉዳይ ቢለያዩም የአንድ ደራሲ ወይም በደራሲና ገጣሚ በውቀቱ ስዩም ስራ ላይ መሆኑ ያመሳስላቸዋል ፡፡ ገብሬ የህልውናዊነት መገለጫ ጭብጦች በማለት ከመረጣቸው አንዱ የሆነው ሞት የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ መሆኑና እንደ ጭንቀት እና ቀቢጸ ተስፋ ያሉ ጭብጦች ደግሞ ገብሬ ህልውናዊነትን ይገልጻሉ በማለት መርጦ ትንታኔ የሰጠባቸው ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ የሞት መገለጫ ናቸው በሚል በጭብጥነት ተለይተው ትንተና የተሰራባቸው መሆኑም ሌላው የሚያመሳስላቸው ባህሪ ነው፡፡ ሌለው ሁለቱን ጥናቶች የበለጠ የሚያመሳስላቸው ባህሪ የገብሬም ሆነ ይህ ጥናት ስለሞት ምንነትና አይነት የተሰጠው ብያኔና ማብራሪያ የቴዎድሮስ ገብሬን "በይነ ዲሲፕሊናዊ የስነ ጽሁፍ ንባብ" 2001ን በአብዛኛው ዋቢ አድርገው መጠቀማቸው ነው፡፡

ይህን ጥናት እና የገብሬን ጥናት የሚያመሳስላቸው እንዳለ ሁሉ የሚያለያያቸውም ጉዳዩ አለ፡፡ የሚያለያያቸው ወይም የሚያራርቋቸው ዋና ዋና ጉዳዮችም ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ሲታይ የገብሬ ህልውናዊነትን /መኖርን/ መሰረት ያደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ሞትን /አለመኖርን/ መሰረት ማድረጉ በመኖርና አለመኖር መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ያራርቃቸዋል ፡፡ሁለቱም ስራወች ከላይ እንደተጠቀሰው የአንድ ደራሲን ስራ መጠቀማቸው ቢያመሳስላቸውም በዘውግና በርዕሰ ጉዳይ  አይገናኙም፡፡

የገብሬ በግጥም ስራዎች ላይ የተሰራ ሲሆን ይህ ስራ በአጭር ልብ ወለድ መድብሉ ላይ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ከጭብጥ አንጻርም ሲታይ ገብሬ የህልውናዊነት መገለጫ ጭብጦች በማለት የመረጣቸውና በዚህ ጥናት የሞት መገለጫ ጭብጦች በመባል የተለዩት የተወሰኑት የተመሳሳይነት ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ከሁለቱ ርዕሰ ጉዳዮች መራራቅ አንጻር የበለጠ ውግንናቸው ለየትኛው ርዕሰ ጉዳይ ነው ካልን  የቴዎድሮስ ገብሬ በይነ ዲሲፕሊናዊ የስነ ጽሁፍ ንባብ ዋቢ አድርገን ስናይ ከህልውናዊነት ይልቅ ለሞት የቀረበ ውግንና አላቸው የሚል የአጥኚው እምነት አለው፡፡  እንደ ሞት፣ የርዕይ መነጠቅ፣ ቀቢጸ ተስፋ፣ ራስ ውንጀላ፣ ባይታወርነት፣ ግዞትና ባዛናነት ያሉ ጭብጦች

> የሰውን ልጅ ህልውና ክፉኛ የሚፈትኑ የህይወት ትራጂዲያዊ ገጽታወች ናቸው፡፡ እነዚህ ገጽታዎች አንዱ ከሌላው ይዛመዳሉ፤ይዋለዳሉ ፡፡ ተዋረዳዊ የሚመስል ግንኙነት በመሃከላቸው አለ፡፡ በዚህ ተዋረድ ውስጥ ደግሞ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ዕጣ የሆነው ሞት ትልቁን ስፍራ ይይዛል ፡፡ቴዎድሮስ (2001፣147) በማለት ገልጾታል፡፡

ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ነው አጥኚው የጭብጦቹ ውግንና ከህልውናዊነት ይልቅ ለሞት የቀረበ ነው ለማለት የሚያስደፍረው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ህልውናን ክፉኛ የሚፈትን ነገር ለሞት ቅርብ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# 3 የሥነ ልቡናዊ ሞት ጭብጦች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ የሚታየው ለጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ በሚገኙ "መውረድና መውጣት"፣"ማየትና መጋረድ" እና "መቅረብና መራቅ" በሚሉ ሦስት ተከታታይ ክፍሎች ባሉት የበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍ እና እድሜ ልብ ወለድ ውስጥ የሚገኙ ገጸባህሪያት ላይ የሚታየውን የተመሰቃቀለ የህይወት ትራጄዲ ባለፉት ምዕራፎች ርዕሰ ጉዳዩን ይገልጻሉ በሚል በተለዩት ጭብጦች መሰረት ትንታኔ ማድረግ ነው፡፡ የልብ ወለዱ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ክፍሎች ርዕሶቻቸው ሲታዩ ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦችን /binary opposites/ የያዙ ናቸው፡፡ በራሱ በትንታኔው ውስጥ የገጸ ባህሪያቱን የስብዕና ማንነት፣ ተመሳሳይነት፣ ልዩነት፣መነሻና መድረሻ ከታሪኩ አንጻር ሥነ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ ተተንትኗል፡፡ ለትንታኔውም ሞትን ይገልጻሉ በሚል የተለዩት ጭብጦች ማለትም ፍርሃት፣ጭንቀት፣ቀቢጸ ተስፋ እና የዝቅተኝነት ስሜት የመተንተኛ አንጻሮች በማድረግ ተተንትኗል፡፡

በቀጥታ ወደ ትንታኔው ከመግባቱ በፊት የልብ ወለዱን አጽመ ታሪክ ለግንዛቤ እና ለመነሻ እንዲሆን አጠር አድርጎ ማየቱ አስፈላጊ ነው ከሚል እምነት ተዳስሷል፡፡

## 3.1. የልብ ወለዱ አጽመ ታሪክ

የበእውቀቱ ስዩም ስራ የሆነው እንቅልፍና እድሜ በ1999 ዓ.ም ለህትመት የበቃ ረጅም ልብወለድ ነው፡፡ ልብወለዱ በ1999 ዓ.ም ለህትመት ይብቃ እንጅ የታሪኩ የጊዜ መቼት ሲታይ 1997 ዓ.ም መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የልብወለዱ የቦታ መቼቱ ደግሞ አዲስ አበባ ነው፡፡ የልብወለዱ አጽመ ታሪክ የየራሳቸው የሆነ ገጸ ባህሪ፣ ታሪክና ጭብጥ ባላቸው ሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡

የመጀመሪያው ክፍል "መውረድና መውጣት" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት ዋና ገጸ ባህሪያትን እናገኛለን፡፡ አንደኛው የታሪኩ ነጋሪ/ ተራኪ/ የሆነው ጋዜጠኛ እንደነበረ አሁን ስራ ለቆ ያለና ገጣሚ ለመሆን ከመፈለግ ውጭ የተጸውኦ ስሙን የማይነግረን ገጸ ባሁሪ ነው ፡፡ ሁለተኛዋ ገጸባህሪ ደግሞ የሱ ተፈቃሪ የሆነችና ዘፋኝ ለመሆን የምትታትር አንድሮሜዳ የተባለች በመኪና አደጋ ህይወቷን ያጣች ሴት ናት፡፡ ለድርሰቱ መጻፍ ምክንያት የሚሆነውም አንድሮሜዳ በመኪና አደጋ ስትሞት ቀብሯ ላይ

የተገኘው  ፍቅረኛዋ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ የቀረበው አንድ አንቀጽ የማይሞላ የህይዎት ታሪኳን ሲሰማ 27 ዓመት ታሪክ ያላት ሴት አንድ አንቀጽ በማይሞላ የቀረበው ታሪኳ እሱ በሚያውቀው ልክ ባለመቅረቡ ስላሳዘነው ለምን ታሪኳን አስፍቼ አልጽፌውም በሚል መነሳሳት የተጻፈ ልብወለድ እንደሆነ ከራሱ ከልብወለዱ እንረዳለን ፡፡ ይህ ስሙን የማይነግረን ገጸባህሪ ከድሃ ቤተሰብ የተወለደ፤ ከአስራ ሁለት ወንድሞቹ ጋር በከፋ ድህነት ውስጥ ያደገና አሁንም  ስራ ለቆ በችግር ውስጥ ያለ በመሆኑ የፍቅረኛው የኢኮኖሚ ጥገኛ በመሆን ህይወቱን የሚገፋ ነው፡፡ ወደፊት ከፍቅረኛው ጋር አብሮ የመኖር  ተስፋ ይዞ እያለ በመኪና አደጋ ስትሞትበት ከፊቱ ያለው ተስፋ ጨልሞበት በወደፊት ህይወቱ ተስፋ ቆርጦ  ራሱን ለማጥፋት የሚመኝ ነው፡፡

ሁለተኛው  ክፍል "ማየትና መጋረድ" የሚል ርዕስ ያለው ነው፡፡ በዚህ ክፍል የምናገኘው ዋና ገጸባህሪ ካሱ የተባለ ሲሆን  ባለትዳር የነበረና በልጁ ሞት ምክንያት ሚስቱ በደረሰባት ታላቅ ሃዘንና ተስፋ የቆረጠ ስሜት ትታው ወደ እንግሊዝ ለመሄድ በመወሰኗ  አረጋግቶ ለማስቀረት የሚለፋ  ነገር ግን በዚህም ሆነ በሌላ የሚያደርገው  ጥረት ሁሉ ከንቱ የሚሆንበትና  ለባሰ ጭንቀት የሚዳረግ ከንቱ ደካሚ ነው፡፡ ከሚስቱ ጋር መግባባት ባለመቻሉ ሚስቱን ወደ እንግሊዝ አገር ሰዶ ብቼውን የሚኖር የዩንቨርስቲ የታሪክ መምህር የሆነ ነው፡፡ ተጨማሪ አዲስ ስራ ለመጀመር የሚያስብና በዚህ ምክንያት አዕምሮው ምስቅልቅል ህይወት ውስጥ የሚገባ ራሱን መሆን ያልቻለ በውስጡ በሚፈጠር ትርምስ መፍትሄ ፍለጋ ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ ሲዋዥቅ የሚታይ ግን የማይሳካለት ገጸባህሪ እና የሱ ሚስት የሆነችውን ሁለተኛዋን ገጸባህሪ ስቴላን እናገኛለን፡፡

ሦስተኛው ክፍል "መቅረብና መራቅ" የሚል ርዕስ ሲኖረው ሁለት ዋና ገጸባህሪያት ይገኙበታል፡፡ አንደኛው ገጸባህሪ ዮፍታሂ ሲሆን በልጅነት እስተዳደጉ በነበረበት የቤተሰብ ተገቢ ያልሆነ ቁጥጥር ነጻነቱን አሳጥቶት እንደነበር በማስታወስ ካደገ በኋላ በልጅነቱ አጥቶት የነበረውን ነጻነቱን ለማካካስ በሚመስል መንገድ ዩንቨርስቲ ሲገባ በልጅነቱ የሆነውን በወጣትነቱ ላለመሆን የራሴ የሚለውን አማራጭ ሁሉ ለመጠቀም ሲሞክር ይታያል፡፡ በልጅነቱ ላጣው ነጻነት ሁሉ ምክንያት የሚላትን እናቱን ይጠላል፡፡ ከተመረቀ በኋላ ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ላለመሄድ  ቤት ተከራይቶ ለብቻው መኖር ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ አብራው ከምትሰራው የታሪኩ ሁለተኛ ገጸባህሪ ከሆነችው አቢ ወይም አብዮት ጋር ፍቅር ይጀምርና አብረው መኖር እንደጀመሩ ከስራ በመባረሩ፤ ከሁለት ወር በኋላ አቢ

ማርገዟን ሲሰማ ያሳለፈው በቤተሰብ የታጠረው የልጅነት ሕይወቱ በኀልማሳነቱ ዳግም በቤተሰብ አጥር ውስጥ ላለመግባት ተስፋ ቆርጦ ጥሏት የሚጠፋ በሥነ ልቡና ምስቅልቅሎሽ የሚዋትት ገጸ ባህሪ ነው፡፡፡

## 3.2. ፍርሃት/Fear/

በምዕራፍ ሁለት የስነ ልቦናዊ ሞት ጭብጦች ምንነት ከፍካሬ ልቡና ንባብ አንጻር ስናይ ለሥነ ልቡና ጣጣዎች መከሰት ምክንያት ናቸው በሚል ሥነሕይወታዊ ሞት /የትዳር ወይም የፍቅር ጓደኛ፣የልጅ ወይም የቤተሰብ ሞት/፣ የገንዘብ ማጣት፣የስራ ማጣት፣ ጤና ማጣት፣የነበረን ውበት /መልክ/ ማጣት፣መከዳዳት /አለመተማመን/ እንዲሁም በቴሌቭዥን የምናያቸውና በሬዲዮ የምንሰማቸው አስደንጋጭ ድራማዎች፣የመኪና አደጋ፣በልጆች ላይ የሚደርስ ጉዳት፣ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል፣ የፍቅር ወይም የትዳር ጓደኛን መግደል እንዲሁም በልጅነታችን ገጥሞን የነበረ በኢ ንቁ አዕምሯችን ታምቆ የቆዬ ጉዳይ ሁሉ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ አይተናል፡፡(ታይሰን 2006)

በሌላ በኩል የሞት ፍርሃት መገለጫዎች ብለን የለየናቸው ጭብጦችም እንዳጣነው፣ እንዳየነውና እንደሰማነው ጉዳይ ደረጃቸው ይለያይ እንጅ ሁሉም እራሳቸውን ችለው የማይቆሙና አንዱ ላንዱ ምክንያት እየሆኑ በሰው ልጅ ላይ የሚታዩ ባህሪያት እንደሆኑም አይተናል፡፡

"መውረድና መውጣት" የሚል ርዕስ ባለው የልብወለዱ የመጀመሪያ ክፍል የምናገኘው የተጸውኦ ስሙን የማይነግረን ገጸባህሪ በ1997 ዓ/ም በነበረው ብጥብጥ ስራውን ያጣ እና የሚወዳትና የሚያፈቅራት በኢኮኖሚ የምትደግፈው ጓደኛውን አንድሮሜዳን በመኪና አደጋ ያጣ ገጸባህሪ ነው፡፡ ለሥነ ልቡናዊ ሞት አጋላጭ ከሆኑት የፍቅር ጓደኛን ማጣት፣ገንዘብ ወይም ስራን ማጣት እንዲሁም በከፋ ድህነት ውስጥ በማደጉ በኢንቁ አዕምሮው ታምቆ የቆየው የልጅነት አስተዳደጉ ተዳምረው የገጸባህሪውን አጠቃላይ ስብእና አዛብተውታል፡፡ ከነበረ ማንነቱ አስወጥተውታል፡፡ ገጸባህሪው ከድሃ ቤተሰብ የተወለደና ከአስራ ሁለት ወንድሞቹ ጋር በከፋ ድህነት ውስጥ ያደገ፣ በተለያዩ የሥነ ልቡና ጣጣዎች የሚታነቅ ነገር ግን ከሚገጥመው የሥነ ልቡን ቀውስ ለማምለጥ የሚጥር ግን የማይሳካለት ነው፡፡ ገጸባህሪው በቤተሰቡ የከፋ ድህነት ምክንያት ያሳለፈውን የልጅነት ሁኔታ ሲገልጽ "አባታችን ዘበኛ፣ እናታችን የዘበኛ ሚስት ስለነበረች እኔና ወንድሞቸ እንደማንኛውም ድሃ ኢትዮጵያዊ ጠግበን የምንበለው ያመት በዓል ቀን ብቻ ነበር" ይላል (በእውቀቱ፣ 1999፣

37)፡፡ በሌላ በኩል የልጆች ብዛትና የድህነቱ ስፋት ወላጆቹን እንዴት ያስፈራቸውና ያስጨንቃቸው እንደነበር ሲገልጽ "...ማታ ማታ ጭንቅ ነው፡፡ ሁላችንም ከየአቅጣጨው እንፈልስና ቤቱን የጥምቀት ጃንሜዳ እናስመስለዋለን፡፡ 'እናቴ እኒህን ልጆች እኔ ነኝ ወይስ ጨለማው ነው የወለዳቸው?' ሳትል አትቀርም፡፡ ባባቴ የሌሊት ዘበኝነት ሳትቀና የምትቀር አይመስለኝም፡፡ 'እሱ ምን አለበት በስራ አመካኝቶ ከልጆቹ ያመልጣል!' ስትል ሰምቻታለሁ፡፡" (በእውቀቱ፤1999፣38)

የገጸ ባህሪው ቤተሰብ በምን አይነት አሰቃቂ ድህነት ውስጥ እንዳለፈና ልጅ ለማሳደግ በወላጆቹ ላይ ያየው የነበረው ሃላፊነትን ያለመወጣት ፍርሃት በኢ-ንቁ አዕምሮው ውስጥ ታምቆ እንደቆየ ያሳያል፡፡ ከዚህ ቤተሰብ ተፈልቅቆ የወጠው ገጸባህሪ ስራ ተቀጥሮ ከቆየ በኋላ ስራ መልቀቁ በኢኮኖሚ የምትደግፈውንና የፍቅር ጓደኛውን በመኪና አደጋ ማጣቱ በቀጣይ ህይዎቱ ሊገጥመው ከሚችለው ችግር ጋር ተዳምሮ ለፍርሃት ዳርጎት ይታያል፡፡ የፍቅር ጓደኛው የቀብር ስነ ስርዓት ላይ ተገኝቶ ሃያ ሰባት ዓመት ታሪክ ያላት ሴት የህይዎት ታሪኳ በአንድ አንቀጽ ብቻ ሲነበብ ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ እና እንዲህ ሲል አናነባለን፤

> አሁን ግን ያለልማዴ ፊቴን በመዳፎቸ ቀብሬ አለቀስኩ፡፡ ያለቀስኩት አንድሮ ሜዳ ስለሞተችአይደለም፡፡ የሃያ ሰባት አመት ህይወቷ በአንድ ሽራፊ አንቀጽ ሲደመደም ስለሰማሁ ነው፡፡ ..ሁላችንም በምንወዳቸው ሰዎች ክብደት ልክ እንመዘናለን፡፡ የምንወዳቸው ሰዎች ታሪክ በአንድ አንቀጽ ሲሰፈር ስንሰማ ይህ ስፍር የኛምመሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸኔ ሆድ ብሶን ፊታችን በመዳፋችን ቀብረን እናለቅሳለን፡፡(በእውቀቱ፣1999፣ 8 )

የፍቅር ጓደኛው የሞተችበት አፍቃሪ የጓደኛው ታሪክ እሱ በሚያውቀው ልክ ሳይነገር በአንድ ሽራፊ አንቀጽ ሲነገር መስማቱ ከመሞቷ ይልቅ የታሪኳ ማጠር የበለጠ እንዲያዝን ፣የበለጠ እንዲያለቅስ፣ የበለጠ ሆድ እንዲብሰው ሲያደርገው ይታያል፡፡ ይሁን እንጅ አፍቃሪው ከአንድሮሜዳ ሞት የህይዎት ታሪኳ ማጠር በልጦበት አይደለም፡፡ ከሚገጥመው የሥነ ልቡና ቀውስ ለማምለጥ እና በጓደኛው የደረሰው ድንገተኛ ሞት ይህ እጣ ፈንታ ነገም በኔ ይደርሳል በሚል ፍርሃት መዋጡ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም "ይህ ስፍር የኛም መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸኔ ሆድ ብሶን ፊታችን በመዳፋችን ቀብረን እናለቅሳለን" ከሚለው ሃሳብ የማዘኑና የበለጠ የማልቀሱ ምክንያት ለራሱም ፈርቶ እንደሆነ ፍርሃቱን አጉልቶ ያሳይበታል፡፡ በሌላ በኩል ፊትን በመዳፍ ቀብሮ ማልቀስ የለቅሶ ባህል መገለጫ ሆኖ ሳይሆን አንድም የሰውን ፊት ከመፍራት አንድም እንባ እንቢ ሲለን ገመናችን

ለመሸሸግ ነው፡፡ አፍቃሪው ገጸባህሪ ግን ፊቱን በመዳፉ ቀብሮ የሚያለቅሰው ካለበት የእንባ ችግር ሠው ምን ይለኝን ፈርቶ እንደሆነ ከሁለት አመት በፊት በእናቱ ሞት የገጠመውን በማስታወስ እንዲህ ሲል ይሰማል

> የዛሬ ሁለት ዓመት እናቴ ሙታለች፡፡ በጣዕር ላይ እያለች የሚያስጨንቀኝ ሃሳብ ስትሞት እንባ ከየት አመጣለሁ ፡፡ የሰፈራችን ሰዎች የእናትን ፍቅር የሚለኩት በልጅ እንባ ብዛት እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ደግነቱ የፈራሁት አልደረሰም ፡፡ በቀብሯ ሰዓት ካፌያ ወረደ ፡፡ፊቴ ረጠበ፡፡ የፊቴ ርጥበት ከሰማይ ይምጣ ከቅንድቤ እርግጠኛ የሆነ ሰው አልነበረም፡፡ አሁን ግን ፊቴን በመዳፌ ቀብሬ አለቀሰኩ፡፡ (በእውቀቱ፣1999፣8/

ከላይ "ሁላችንም በምንወዳቸው ሰዎች ክብደት ልክ እንመዘናለን" የሚለው እና "የሰፈራችን ሰዎች የእናትን ፍቅር የሚለኩት በልጅ እንባ ብዛት መሆኑን አውቃለሁ" የሚሉት መለኪያዎች የምንወዳቸውና የምናፈቅራቸው ሰዎች ሲሞቱ የማዘናችን መለኪያዎች መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በነዚህ መለኪያዎች ለማለፍ በሰዎች ዘንድ ይደርስብናል ብለን ከምንፈራው ሃሜትና ሽሙጥ ለመዳን በፍርሃትና ጭንቀት እንዋጣለን፡፡

ለአንድሮሜዳ ሞት ምክንያት የሆነው የመኪና አደጋ በደረሰበት ሰዓት ገጥሞት የነበረውን ፍርሃት እና ድንጋጤ በቀጣዩ ህይወቱ ጥልቅ ጠባሳ ጥሎበት እንዳለፈ ሲገልጽ

> አንድሮሜዳ በመኪና ወደ ቤቴ እየሸኘችኝ ነበር፡፡ ከኋላ ወንበሮች በአንዱ ተቀምጫለሁ፡፡
>
> ትንሽ ከሄድን በኋላ መኪናዋ ዝግዛግ መወዛወዝ ስትጀምር "አንድሮሜዳ!" ብዬ ጮሁኩ::
>
> ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሆሰፒታል አልጋ ላይ ተኝቶ ተገኘሁ፡፡
>
> ለምን ተረፍኩ?
>
> ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ እንኳን ይሄ ጥያቄ እንደ ዛር ሰፍሮብኝ ነበር፡፡ መጭው ጊዜ
>
> እንደታከምኩበት ሆስፒታል ግድግዳ አንዳች ማራኪ ምስል ያልተሰቀለበት ሆኖ ታየኝ፡፡
>
> የአንድሮሜዳ መኪና ተጠረማምሶ ከቆመበት ቦታ የሚቀጥል የእድሜ ጎዳና አልታይህ አለኝ፡፡
>
> ራሴን እንደምገድል በጣም እርግጠኛ ሆንኩ፡፡(በእውቀቱ፣1999፣10)

ገጸ ባህሪው ፍቅረኛው የሆነችው አንድሮሜዳ በራሷ መኪና ወደ ቤቱ እየሸኘችው ባለችበት ሰዓት መኪናው ለአደጋ ሲጋለጥ እና ከአደጋው በኋላም የነበረበት ሁኔታ በተመሰቃቀለ ሥነ

ልቦና ውስጥ እንደገባ እናያለን፡፡ የተናገራቸው፣ ያሰባቸውና የተመኛቸው ሃሳቦች ሲታዩ ራሱን ስቶ ጤነኛ ባልሆነ ወይም በኢ- ንቁ የአዕምሮ መታጎል ውስጥ እንደነበረ ያሳያል፡፡

መኪናው መወዛወዝ ሲጀምር "አንድሮሜዳ ብየ ጮህኩ" የሚለው ሃሳብ "ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሆስፒታል አልጋ ላይ ተኝቼ ተገኘሁ" ከሚለው ጋር ተወስዶ ሲታይ በኋላም "ለምን ተረፍኩ"? የሚለው ጥያቄ ሲጨመርበት ጋዜጠኛው በፍርሃት፣ በጭንቀት እና ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ሆኖ ራሱን ስቶ እንደነበር ያሳያል፡፡ ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላም ይህ ጥያቄ እንደዛር ሰፍሮብኝ ነበር የሚለው ሃሳቡ አሁንም ከነበረ ማንነቱ ወጥቶ በሌላ ማንነት ውስጥ በመሆኑ ፍርሃቱና ጭንቀቱ እንዳልለቀቀው የሚያሳይ ነው ፡፡ የመጭውን ጊዜ ምንም ስዕል ካልተሳለበት የሆስፒታል ግድግዳና አደጋ ደርሶበት ተጨረማምቶ ከወደቀ የአንድሮ ሜዳ መኪና ጋር እያወዳደረ መልካም ነገር እንደማይታየው ይናገራል፡፡ ከዚህ ሃሳቡ የሚታየው ወደፊት አንድሮሜዳን በማጣቱ ተስፋው መሟጠጡንና የተሻለ ህይወት አልኖርም በሚል በፍርሃት መዋጡን እና ተስፋ መቁረጡን ያሳያል፡፡ ይህ በኢ-ንቁ አዕምሮው ውስጥ የሚርመሰመስ ፍርሃቱ ከወደፊት የመኖር ተስፋው ሲያተው ከማንነቱ ሲያስወጣውና እራሱን እንደሚያጠፋ እርገጠኛ እስከመሆን ሲያደርሰው ይታያል፡፡

በሌላ በኩል በልብ ወለዱ "ማየትና መጋረድ" በሚለው በክፍል ሁለት በሚገኘው ታሪክ ላይ የታሪኩ ዋና ገጸባህሪ /ካሱ/ በተመሰቃቀለ የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ሲገባና ከገባበት አስከፊ የህይዎት ትራጄዲ ለመውጣት ከጫፍ ጫፍ ሲረግጥ ይታያል፡፡ ካሱን ለዚህ አስከፊ የህይወት ገጽታ የሚዳርገው የልጁን ሞት ተከትሎ ሚስቱ በደረሰባት ፍርሃት ወደ እንግሊዝ አገር ለመሄድ መወሰን፣ የገንዘብ ችግር፣ ሚስቱን መክዳቱ ወይም መሃላ ማፍረሱ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ የሥነ ልቡና ጣጣዎች ደግሞ ለመገለል፣ ለመቀራረብ እና ለመክዳት የሞት ፍርሃት በማጋለጥ በወደፊት ህይወቱ ላይ ስጋትን በመፍጠር ለሥነ ልቡና ቀውስ ሲያጋልጡት ይታያል፡፡

ካሱ ሚስቱ ወደ እንግሊዝ ከሄደች በኋላ የተሻለ ቤት እንዲከራይበት፤ ኑሮውን እንዲቀይርበት ገንዘብ በየወሩ ትልክለት ነበር፡፡"ኑሮህን እንድትለውጥበት እፈልጋለሁ!" ትለው ነበር፡፡ ይህን ገንዘብ ላለችው አላማ አውየዋለሁ እያለ ሲዋሻት ቆይቷል፡፡ "እሱ ግን ጠጣበት፤ ድሃ ጓደኞቹን ጋበዘበት፡፡ አጨሰበት፡፡ በኑሮው ላይ የጨመረው የአመድ ቁልልና የባዶ ጠርሙሶች ካብ መሆኑ ተገለጸለት፡፡ "(በእውቀቱ፣1999፣70)

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር ሚስቱ ወደ አገር ቤት መመለስ እንዳሰበች ደውላ ስትነግረው ምን ይገፐ ልቆይ በሚል ፍርሃት ውስጥ የገባው፡፡ ገንዘብ ማጣት ብቻ ሳይሆን ያገኙትን ገንዘብ ባግባቡ አለመጠቀምም ለሥነ ልቡና ቀውስ እንደሚዳርግ ከካሱ ህይወት ማየት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ሚስቱ ተመልሳ ከፊል ባዶ በሆነው አንድ ክፍል ውስጥ ስታገኘው ምን ልትለው እንደምትችል እያሰበ በፍርሃትና በጭንቀት ተወጥሯል፡፡

"ካሱ በዚህ ጊዜ ስሜቱን እንደምንም አረጋግቶ ማድረግ ያለበትን ነገር ማሰብ ጀመረ፡፡ ለስቴላ መቀበያ ሦስት ክፍል ቤት መከራየት አለበት፡፡ ዓይኗን የሚያጠግብ ልብሶችንና ቁሳቁስ መግዛት አለበት፡፡ ስለዚህ ገንዘብ ያስፈልገዋል"፡፡(በእውቀቱ፣1999፣71) ይህን የገንዘብ ችግር ለመቅረፍ ነበር በአንድ የምርምር ተቋም ውስጥ ጥናታዊ ሃተታ ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበው፡፡ ካሱ "የመተማ ጦርነትና ያዬ ዮሃንስ ዕጣ!" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ያሰበውን ገንዘብና ያላሰበውን እዳ ይዞበት መጣ፡፡ ጥናቱን በሚአቀርብበት ጊዜ የተቀረጸው የቪዲዮ ካሜራ በቴሌቭዥን ሲተላለፍ ሆን ተብሎ ይሁን በስህተት ለይቶ ባልተረዳበት ሁኔታ ከስሩ የሱ ምስል እየታየ የ97 ዓ/ም ምርጫን ነጻና ፍትሃዊ ነበር በሚል የተላለፈውን ዜና ካሱ ማየቱና ከዜናው በኋለም ሆነ በሚቀጥሉት የዜና ሰዓቶች ማስተባበያ ሳይሰጥበት መቅረቱን ተከትሎ በካሱ ምርጫውን በሚቃወሙ አካላት ይደርስበኛል ብሎ ያሰበው የሞት ፍርሃት ከነበረ ማንነቱ አስወጥቶ ለሥነ ልቡናዊ ሞት ሲያጋልጠው ይታያል፡፡

ካሱ በቴሌቭዥን የታየው ምርጫ ሲያወድስ ነው፡፡ ምርጫውን የሚያወድስ እንዳለ ሁሉ የሚቃወምም አለ፡፡ ካሱ ከሁለቱም የለበትም፡፡ ነገር ግን የሱን ምስል እያሳየ የተላለፈው ዜና በከባድ ፍርሃት ውስጥ ጥሎታል፡፡ "የዜና ማስተባበያ ያቀርባሉ ብሎ ጠበቀ፡፡ ግን ምንም የለም፡፡ ፍርሃት በሰውነቱ ተለቀቀ፡፡ይህ ፍርሃት አባቶች በመተማ ጦርነት ከወደቀባቸው ፍርሃት የሚልቅ ነው፡፡ እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር አደረ፡፡"(በእውቀቱ፣1999፣76)

ጦርነት አስፈሪ ነው፡፡ በተለይም በጦርነት መሸነፍ ደግሞ ፍርሃቱን እጅግ ያከብደዋል፡፡ ካሱ ላይ የደረሰው ፍርሃት ግን ደግሞ ከጦርነትም በላይ ነው፡፡ ካሱ ከፍርሃቱ ክብደት የተነሳ እንቅልፍ አጥቷል፡፡ "ምርጫውን ማወደሱ መንግስትን ማወደስ ነው ፡፡ መንግስትን ማወደስ ደግሞ ቢያንስ መንግስትን ካልመረጠው የአዲስ አበባ ህዝብ ጋር ተጣማመደ ማለት ነው፡፡"/ ገጽ፣79/ ካሱ ምርጫ እንዳወደሰ ተደርጎ የተላለፈው ዜና በአዲስ አበባ ህዝብ ዘንድ የተጠላሁና ተፈላጊ እንድሆን አድርጎኛል የሚል እምነት እዲያድርበት

አድርጎታል፡፡ በዚህም መንግስትን ሳይሆን የአዲስ አበባን ህዝብ ይገለኛል ብሎ እንዲፈራ ሆኗል ፡፡

> ከዚህ በኋላ ከቤቱ ርቆ ለመሄድ ድፍረት እንደማይኖረው ተረዳ፡፡ በማንኛውም ሰዓት ደመ ከልብ ሊሆን እንደሚችል ገመተ፡፡ ወንድሙ በመንግስት ወታደሮች የተገደለበት ጎረምሳ ወስዶ መሽናት በተከለከለበት ታዛ ሥር ደሜን ሊያፈስብኝ ይችላል ብሎ ሰጋ፡፡
>
> ጠሽ ጠሽ የሚል የተኩስ ድምጽ ስጋቱን አናረበት፡፡ በመንግስትና በተቃዋሚዎች መካከል ያለው ጠብ እንዳልበረደ ገበው፡፡ (በእውቀቱ፣1999፣83-84)

በካሱ ላይ የሚታየው ፍርሃት ድርብ ድረብርብ ነው፡፡ በአንድ በኩል ምርጫውን ያልመረጠው የአዲስ አበባን ሕዝብ ፣ ምርጨውን መነሻ አድርጎ በተቀሰቀሰው አመጽ በመንግስት ወታደር ወንድሙ የተገደለበትን ወጣት የመንግስት ደጋፊ ነህ በሚል እና አሁንም የተኩስ ድምጽ መስማቱ ተባራሪ ጥይት ይገለኛል በሚል ፈርቷል ፡፡ ፍርሃቱ ደግሞ ከቤት እንዳይወጣ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ራሱን አግልሉ ብቻውን እንዲቀመጥ አድርጎታል፡፡

ካሱ ሚስቱ የምትልክለትን ገንዘብ ማባከን ተከትሎ የገንዘብ ችግሬን እፈታበታለሁ በሚል ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ያስከተለበት የሞት ፍርሃት ከሚስቱ አልፎ ያዲስ አበባን ህዝብ እንዲፈራ አደረገው፡፡ ካደረበት የሞት ፍራቻ የተነሳ ከህዝብ የመራቅና በቤቱ መደበቅን እንደ አማራጭ ሲጠቀም ይታያል፡፡ ካሱ ከፍርሃቱ የተነሳ "ፈጣሪው የኢየሩሳሌምን ጥፋት እንዳያይ የስድሳ ስድስት ዓመት እንቅልፍ እንደተላከለት እንደ አቤሜሌክ ይህ ቀን እስኪያልፍ እንቅልፍ ልኮ የሚያድነው አምልክ ሲፈልግ እና በብርድ ልብሱ ውስጥ ገብቶ ካካባቢው ሃሳብና ፍርሃት እንዲሸሽግ ሲመኝ ይታያል፡፡"(በእውቀቱ፣ 1999፣86)

በልብ ወለዱ ውስጥ ለካሱ ህይወት መመሰቃቀል ምክንያት የሆኑ በርካታ ነገሮች በምክንያትና ውጤት መልክ ቀርበዋል፡፡ በልጁ ሞት ምክንያት ከሚስቱ ጋር አለመግባባት ይህን ተከትሎ ሚስቱ ጥላው ወደ እንግሊዝ አገር መሄድ፣ ሚስቱ የተሸለ ቤት እንዲቀይር የላከችለትን ገንዘብ በአግባቡ አለመጠቀምና ቤት ቀይሬአለሁ ብሎ ዋሽቷት ስለነበር አሁን ሚስቱ ለመምጣት መወሰኗ ዓይኗን ለማየት ፈርቷል፡፡ ምን ይዤ ልቆዪ በሚል ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሰለመተማ ጦርነት ያቀረበው ጥናት ያስከተለበት የቴሌቭዥን ዜና ተደማምረው ሞትን እንዲፈራ አድርገውታል፡፡ ሰለሰማዊ ህይወቱ ተናግቷል፡፡ ማህበራዊ

ህይወቱን ቀውስ ውስጥ ከመግባቱ በላይ በእውንም ሆነ በህልሙ እየተከሰቱ እረፍት ነስተውታል፡፡ እንቅልፍ አሳጥተውታል፡፡(በእውቀቱ፣1999፣82) ትክ ብሎ የሚያየው እና የሚያስታውለው ሁሉ የሚይዘው፣ የሚመረምረው የሚገለው እየመሰለው ይፈራል ይጨነቃል፡፡ እንቅልፍ ናፍቆታል ፡፡ መተኛት ካልቻለ አዕምሮው በጤነኝነት መቀጠሉ ጥርጣሬ ውስጥ ከቶታል፡፡

በሌላ መንገድ "የጭንቀቴ ምንጭ ፊቴ ነው" /ገጽ፣89/ ብሎ ለጓደኛው ሲነግር እንደምንሰማው "ለዚህ ያበቃኝ ደግሞ በቴሌቪዥን የታየው ፊቴ ነው" በሚል ፍርሃት ፊቴን ያየ ይገለኛል በሚል ፊቱን ሰው እንዳያይበት እንደ መሃረም በኪሱ ጠቅልሎ ለመሸሸግ ሲመኝ ፤ድርቡሽ ለሃገሩ ነጻነት ሲል የተዋጋውን ጀግና በጦርነት ገሎ አንገቱን ቆርጦ ከወሰደው ጋር ራሱን በማመሳሰል ፊቱን ወደ ሌላ አገር አሻግሮ የሚወስድለት እንደሚፈልግ ሲመኝ የምናየው ፍርሃቱ ከቁጥጥሩ ወጥቶ ሞትን በመፍራት መልካም ነገር አልታይህ ብሎት በኢ-ንቁ አዕምሮ ውስጥ ያለ መሆኑ ማሳያ ነው፡፡ በጤናማ አስተሳሰብ ውስጥ ያለ ሰው ፊቱን እንደመሃረም ጠቅልሎ በኪስ ለመያዝ ውይም ፊቱን ወደ ሌላ ሃገር የሚወስድለት ሰው የሚፈልግ አይደለም ከራሱ ጤናማ ማንነት ወጥቶ በሥነልቡናዊ ሞት ውስጥ ያለ ሞሆኑን ማሳያ ነው

የሞት ፍርሃት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ሥነ ልቡናዊ ቀውስ በመፍጠር ከራስ ማንነት አስወጥቶ ከማህበረሰብ እና ከህገ ልቡና ነጥሎ ብቸኛ ሊያደርግ እንደሚችል እና ለሥነልቡናዊ ሞት እንደሚያጋልጥ ከካሱ ህይወት ማየት ይቻላል፡፡

በጥቅሉ በፍርሃት ምክንያት የሚከሰተው ሥነልቡናዊ ሞት በክፍል አንድ በሚገኘው ገጸባህሪ ላይ በልጅነት ጊዜው ያለፈበት የከፋ ድህነት፤የ1997 ምርጫን ተከትሎ በተከሰተው ሁከት ከስራ መባረሩ፤በገንዘብ ስትደግፈው የነበረችው የፍቅር ጓደኛው አንድሮሜዳ በመኪና አደጋ መሞት፤የእናቱ ሞት ምክንያት ሲሆኑ በዚህ ምክንያት የወደፊት ህይወቱን የሚያስቀጥልበት ተስፋ አልታይህ ሲለው ብቸኝነት እና የሥነልቡና አልባነት እየተሰማው ከመኪና አደጋ ለምን ተረፍኩ በማለት በተደጋጋሚ ራሱን ለማጥፋት ሲመኝ መታየቱ ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላው ከፍርሃት ጋር በተያያዘ በክፍል ሁለት የሚገኘው ካሱ በልጁ ሞት፤ በሚስቱ ጥለው መሰደድ፤ሚስቱን በመክዳት መሃላ በማፍረሱ የተላከለትን ገንዘብ በማባከኑና

መዋሸቱ፣ምርጫ ማወደሱን መንስኤዎች ናቸው፡፡ የሥነልቡና ሞቱ ደግሞ የሚስቱንና የልጁን ፍቅር ማጣቱና መገለሉ ወይም ብቸኛ መሆኑ፣ ክህደት መፈጸሙ፣ ፌቴን ያየ የአዲስ አበባ ሕዝብ ይገለኛል ብሎ መገለሉ ፣ፌቱን ሰው እንዳያይበት እንደመሃረም አጣጥፎ በኪሱ ለመያዝ እና ወደሌላ ሃገር ፌቱን የሚወስድለት መፈለጉ እና ከአዲስ አበባ ወጥቶ ለመሸሽ መመኘቱ የስነልቡናዊ ሞቱ ማሳያዎች ናቸው፡፡

## 3.3. ጭንቀት /Anxiety/

ስለ ጭንቀት  ምንነት ባየንበት ክፍል ጭንቀት አካላዊና አዕምሯዊ በሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል የሥነልቡና ቀውስ እንደሆነ አይተናል ፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ በልብ ወለዱ ታሪክ ውስጥ የተከሰቱ  የሥነ ልቡና ቀውሱ የፈጠራቸውን ጭንቀቶችን ከልብ ወለዱ ማሳያዎችን እየመዘዝን እንተነትናለን፡፡

በክፍል ሁለት ታሪኩ ባለቤት የሆነው ካሱ የገጠመውን የገንዘብ ችግር እፈታበታለሁ ብሎ ያዘጋጀው ጥናታዊ ጽሁፍ የፈለገውን ገንዘብ ቢያገኝበትም ያላሰበውን እዳ ይዞበት በመምጣቱ ካሱ ለከፍተኛ ጭንቀት መዳረጉን /ገጽ 75/ ላይ እናያለን፡፡

ካሱ ለገጠመው ጭንቀት መፍትሄ ይፈልጋል በሚል ለጓደኛው " የጭንቀቴ ምንጭ ፊቴ ነው" በማለት በቴሌቭዥን የታየው ፊቱ እንደሚያስጨንቀው ሲነግረው ጓደኛው ላጋጠመው ችግር መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ "ይህን ያህል ፊትህ ሊያሳስብህ አይገባም!፡፡ ...እውነቴን ነው! ካንተ የባሰ ፊት ያላቸው ብዙ ሰዎችን አውቃለሁ"!፡፡ (ገጽ፣89) ማለቱ ካሱ በቴሌቭዥን ምርጫ ሲያወድስ ከታየው ፊቱ  ይልቅ መልከ ጥፉ ነኝ የሚለው የባሰ ጭንቀቱን ከፍ እንዳደረገው እና ያድነኛል ወይም ይፈልገኛል ከሚለው የከተማ ሰው ከከተማው በመውጣት ማምለጥ የሚቻል ሲሆን ከማያምር ፊት ግን ከሞት ሌላ ሊገለግል የሚችል እንደሌለ እንዲህ ይገልጻል፡፡

"የከተማው ሰው ሁሉ ይከታተለኛል ብሎ መጨነቅ ማራኪ አይደለሁም ብሎ  ከመጨነቅ ጋር ሲነጻጸር ኢምንት ሆኖ ታየው፡፡ ምክንያቱም የከተማውን ሰው ከከተማ ወጥቶ ማምለጥ ይቻላል፡፡ ከማያምር መልክ የሚገላግል ምን አለ? ምናልባት ሞት! ምናልባት ሂምሎክ፡፡" (በእውቀቱ፣1999፣97)

ለሥነ ልቡና ችግር ከሚያጋልጡ ጣጣዎች አንዱ መልክን ወይም ውበትን ማጣት አንደሆነ አይተናል፡፡ ካሱ አሁን ከፊቱ ጋር በተያያዘ በሁለት መንገድ ጭንቀት ገጥሞታል፡፡

የመጀመሪያው ባላሰበው ሁኔታ ምርጫ ሲያወድስ በቴሌቭዥን የታየውን ፊቱን ያየና ምርጨውን ያልደገፈ ወይም ምርጨውን ተከትሎ በተነሳው ብጥብጥ ቤተሰቡ የተገደለበት ያአዲስ አበባ ሕዝብ ይገለኛል በሚል ተጨንቋል፡፡  በሌላ በኩል መልከ ጥፉ ነኝ ብሎ አስቦት የማያውቀውን ጓደኛው "ይህን ያህል መልክህ ሊያሳስብህ አይገባም ካንተ የባሰ ፊት ያላቸው ብዙ ሰዎች አውቃለሁ" ያለው የበለጠ ጭንቀቱን አንሮት ካሱ ከኖረበት ማህበራዊ ኑሮው፣ ከቤተሰቡ ተፈናቅሎ ከአዲስ አበባ ሸሽቶ ለማምለጥ ሲያስብ በሌላ በኩል የትም ቢኸድ ከመልከ ጥፉነቱ ከሞት በቀር ሊገላግለው የሚችል እንደሌለ በማመን ሞትን ሲመኝ ይታያል፡፡ ሽሽት ለጭንቀት ጤናማው አጸፌታ እንደሁነ በምዕራፍ ሁለት አይተናል፡፡

ካሱን ጭንቀት ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገው ሌላው መንሰኤ መሃላ ማፍረሱ ወይም እምነት ማጉደሉ ነው፡፡ ሚስቱ ወደ እንግሊዝ አገር ስትሄድ ቤተክርስቲያን ወስዳ "እኔ እስከመለስ ከሌላ ሴት ጋር ላትተኛ ማልልኝ" ብላ ስታስምለው /ገጽ100/ ላይ ይታያል ፡፡ እሱ ግን ሚስቱ በሄደች በአንድ ወር ውስጥ ከአንዲት የቀድሞ ተማሪው ጋር በመተኛት መሃላውን በማፍረሱ ቀውስ ወይም ጭንቀት ውስጥ ሲገባ ይታያል፡፡ ካሱ እረፍት ከነሳው መሃላ የማፍረስ ፍርሃት እና ጭንቀት ለመገላገል ስበባ ስበቦችን በመደርደር ራሱን ለማረጋጋት ከጭንቀቱ ለማምለጥ ሲጥር ይታያል፡፡  በኮንዶም ወሲብ ማድረግ መሰረታዊ የወሲብ በሃሪ የለውም በሚል ከገባበት ጭንቀት ለመገላገል ሲፈልግ "በሄደች በወሩ ከቀድሞ ተማሪዎቼ ካንዷ ጋር ተኛ፡፡ 'ዛሬ በኮንዶም ባልለው ኖሮ መሃላዬን አፍርሽ ነበር!' አለ ሽኝቷት ወደ ቤቱ ተመልሶ ከስቴላ ፎቶ ጋር ሲፋጠጡ፡፡ በኮንዶም ከሴት ጋር የተኛ ወንድና ዳምኖ ያልዘነበ ሰማይ አንድ ናቸው አለ በልቡ"፡፡(በእውቀቱ፣1999፣100)

በምእራፍ ሁለት ፍርሃትን ስንገልጽ ከፍርሃት አይነቶች አንዱ የመክዳት ፍርሃት /Fear of betrayal/ እንደሆነ አይተናል፡፡ ይህ ፍርሃት የሚከሰተው ደግሞ ባል ወይም ሚስት ሌላ ሴት ይዟል/ይዛለች/ በሚል አለመተማመን የሚፈጠር ክህደት እንደሆነም አይተናል፡፡ ፍርሃት ሲያድግና ከቁጥጥር ሲወጣ ጭንቀት እንደሚሆንም አይተናል፡፡ ካሱ የሚስቱን መሃላ ማፍረሱና ሚስቱን መክዳቱ አካላዊ ጭንቀት ብቻ ሳይሆን ህሊናዊ ጭንቀትም ደርሶበታል፡፡ አብራው ያደረችውን ሴት ሸኝቶ ወደ ቤቱ ሲገባ የሚስቱን ፎቶ ሲያይ እንግሊዝ ያለችው ሚስቱ በአካል ወሲብ ሲፈጽም ያየችው እስኪመስለው ድረስ ተጨንቋል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በጭንቀት ውስጥ ሲሆን ከገባበት ጭንቀት ለመውጣት መፍትሄ ማፈላለግ የጭንቀትም አንዱ በጎ ጎኑ መሆኑን  አይተናል፡፡ ካሱ መሃላ ማፍረሱ

ወይም ሚስቱን መክዳቱና ወሲብ ሲፈጽም በአካል ያየችው የመሰለውን ጭንቀቱን ለመከላከል እና ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያስከትለው የአባላዘር በሽታ እያዛለሁ በሚል የደረሰበትን ጭንቀትና ይህን ተከትሎ ከመጣበት የህሊና ቀውስ ለመውጣት በኮንዶም የተፈጸመ የግብረ ስጋ ግንኙነት የወሲብን መሰረተ ሃሳብ አያሟላም በሚል ከጭንቀቱ ለመውጣት የሚከተለውን ሃሳብ ይናገራል፡፡

> ወንዱ ወሲብ አደረገ የሚባለው ወደ ሴቷ ገላ ፈሳሹን ሲያወርድ ነው፡፡ ሴቷም ስትረጥብና ስታረጥብ ነው፡፡ ያለፈሳሽ ቅብብሎሽ ወሲብ አይታሰብም፡፡ በኮንዶም የሚደረግ ግንኙነት የወሲብ መሰረተ ነገር የሆነውን የርጥበት ልውውጥ ስለሚያግድ ወሲብ አይደለም፡፡...ኮንዶም ከበሽታ ፍርሃት ብቻ ሳይሆን ከህሊና ወቀሳም ሰወረው፡፡(በእውቀቱ፣1999፣101)

ካሱ መሃላ አፍርሶ ክህደት ፈጽሞ የደረሰበትን አካላዊና አዕምሯዊ ጭንቀት ለመከላከል የተለያዩ ስበቦችን እየፈለገ ለማምለጥ ቢሞክርም ማምለጥ ግን አልቻለም ፡፡ በእውንም በህልምም ጉዳዩ እረፍት እና እንቅልፍ ነስቶታል፡፡ የሚያስበውም ሆነ የሚያልመው ሥለ ሚስቱ ሆኗል፡፡ አንድ ቀን ተኝቶ ስለሚስቱ እያሰበ ሳለ ስላየው ህልም እንዲህ ይገልጻል "ሳይጣን የገንዛ ገላውን ደምስሶ በምትኩ የእንግሊዝ ወንዶችን እርቃን ምን እንደሚመስል ናሙና ያቀረበለት መሰለው፡፡ ስቴላ ከእንግሊዝ ወንዶች ጋር ተኝታ በሃሳቡ ታየችው፡፡ ሰውነቱ በቅናት እንደ በረዶ ቀዘቀዘ "፡፡(በእውቀቱ፣1999፣105)

ካሱ እራሱ ያፈረሰው መሃላ ያመጣበት ጭንቀት "ሳይጣን ለወዳጁ ቅርብ ነው" እንደሚባለው የራሱን ገላ ደብቆ የእንግሊዝ ወንዶችን ገላ እንዲያይ አደረገው ፡፡ ሚስቱ ከነዚህ ወንዶች ጋር ተኝታ አያት፡፡ ለጊዜው ባደረበት ቅናት ስሜቱ እንዲጠፋ ሰውነቱ እንዲቀዘቅዝ ቢያደርገውም ችግሮቹ ተደማምረው እንቅልፍ ነስተውታል፡፡ ጭንቀቱን ከፍ አድርጎበታል፡፡ ያጋጠመውን የእንቀልፍ እጦት መፍትሄ ፍለጋ በኢንቁ ልቦናው ከሶቅራጥስ ጋር የሚከተለውን ውይይት ያደርጋል፡፡

> ሶቅራጥስ ለመሆኑ ምንድን ነው የፈለከው?
> ካሱ መተኛት፡፡ማለቴ ተኝቶ መነሳት፡፡
> ሶቅራጥስ ለምን መፍትሄ አልጠቁምህም፡፡
> ካሱ ምን መፍትሄ አለ?
> ሶቅራጥስ ወሲብ! ወሲብ ጥሩ መፍትሄ ነው፡፡
> ካሱ እንዴት?
> ሶቅራጥስ ወሲብ እንቅልፍ ያመጣል፡፡ አራት ነጥብ፡፡(በእውቀቱ፣1999፣99)

ካሱ መሃላ ማፍረሱና ሚስቱ ከእንግሊዝ ወንዶች ጋር ተኝታ በሃሳብ በማየቱ ምክንያት የገባበት ጭንቀት የነሳውን እንቅልፍ በሃሳቡ ከሊቁ ጋር ባደረገው ዲያሎግ ያገኘውን መፍትሄ እውነት ብሎ በመቀበል እና እንቅልፍ ነስቶት የቆየውን የስነልቡና ቀውስ ወይም ጭንቀት ለመበቀል በሚመስል መንገድ ያለ ፍላጎቱ ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ ለመፈጸም ይነሳሳል፡፡ ካሱ በዚህ ወቅት ለወሲብ የተነሳሳው የሶቅራጥስን ምክር ተቀብሎ በጭንቀት አጥቶት የቆየውን እንቅልፍ ለመተኛት እንጂ የወሲብ ፍላጎቱን ለማርካት አልነበረም፡፡ የእንቅልፍ እንጅ የወሲብ ፍላጎት ሳይኖረው ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ ይፈጽማል ፡፡ የወሲብ ፍላጎት አለመኖሩን እንዲህ ይገልጸዋል ፡፡" 'ከላይ ልሁንልህ?!' አለችው ኮንዶሙን ካጠለቀችለት በኋላ፡፡ 'እንዳሻሽ!' አላት፡፡ በየትም ብትሆን ግድ አልሰጠውም፡፡ እንቅልፍ እንጅ ወሲብ ፈልጎ እንዳልመጣ ያውቃል፡፡" (ገጽ፣109) ካሱ መሃላ ማፍረሱ ያስከተለበት የእንቅልፍ እጦትና የጭንቀት ጣጣ ያለፍላጎቱ በድጋሜ ከሌላ ሴት ወሲብ እንዲፈጽም አስገድዶታል፡፡

የሶቅራጥስን ምክር ተቀብሎ ከገባበት የህሊና ወቀሳ ለመውጣት ለሁለተኛ ጊዜ አንቅልፍ አገኝበታለሁ ብሎ ያደረገው ወሲብ ግን የፈለገውን እንቅልፍ ሳይሆን ያላሰበውን ተጨማሪ ጭንቀት ይዞበት ሲመጣ ይታያል፡፡ ካሱ ከዚህ ቀደም መሃላውን አፍርሶ ከቀድሞ ተማሪው ጋር ያደረገው ወሲብ ቢያስጨንቀውም ከጭንቀቱ ለመውጣት ሲል በኮንዶም የተፈጸመ ወሲብ ከእርጥበት አለመተላለፍ ጋር በማያያዝ የወሲብ መሰረተ ነገር የለውም በማለት ከሚስቱ ጋር የገበውን መሃላ አንዳላፈረሰ እና ኮንዶም ከበሽታ ፍርሃት ብቻ ሳይሆን ከህሊና ወቀሳም ሲጋርደው እና ከህሊና ወቀሳ ለማምለጥ ሲሞክር አይተናል፡፡ ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ የፈጸመው ወሲብ ያስከተለበትን ጭንቀት በምንም ሊጋርደው አልቻለም፡፡ አሁን የገባበትን ጭንቀት እና ፍርሃት የሚጋርድበት ምክንያት የለውም፡፡

> …ቁጭ ብድግ ማለቷን ድንገት አቆመች፡፡
>
> "ኤጭ!" አለች፡፡
>
> "ምንድን ነው?" አላት የሆነ ነገር እየቀፈፈው፡፡
>
> "ተቀዷል!"
>
> "ምኑ?"
>
> "ኮንዶሙ"

"ምን ቀደደው?" አለ ደንግጦ፡፡

"እግርህ ልበልህ?"

ፊቱን በእጆቹ ሸፈነ፡፡ ከላዩ ላይ በዝግታ ወረደችና "አይዞህ ያለ ነገር ነው!" አለችው፡፡

"እንዴት?"

"በዚህ ወር እንኳ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥመኝ አንተ አራተኛው ነህ!" አለችው፡፡

በተሸነቆረው ኮንዶም በኩል ነፍሱ ሾልካ የሄደች ይመስል ላፍታ ያህል በድን ሆኖ ቆየ፡፡/ገጽ፣110/

ካሱ አሁን የገጠመው ጭንቀት መሃላ የማፍረስ ያለማፍረስ ብቻ አይደለም፡፡ ሚስትን የመክዳት ያለመክዳት ብቻም አይደለም፡፡ አሁን ያጋጠመው ጭንቀት በህይወት የመኖር ያለመኖር ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ አሁን ያጋጠመውን ጭንቀትና ፍርሃት በምንም ማላከክ በምን መጋረድ አልቻለም፡፡ አሁንም መሃላ አፍርሷል፡፡ ሚስቱን ክዷል፡፡ ወሲብ በመፈጸም አገኘዋለሁ ያለውን እንቅልፍ አጥቷል፡፡ አሁን በተደረገው ወሲብ በኮንዶሙ መቀደድ ምክንያት የእርጥበት ትልልፍ ተካሂዷል፡፡ አሁን የተደረገው ወሲብ መሰረታዊ የወሲብ ባህሪን አሟልቷል ፡፡ አብራው የተኛችው ሴት በሴተኛ አዳሪነት ህይወቷን የምትመራ ናት፡፡ በዚህ ወር እንኳን አብረዋት ካደሩ ወንዶች ከአራቱ ጋር በተደረገ ወሲብ የኮንዶም መቀደድ እንደገጠማት ትነግረዋለች፡፡ በኤች አይ ቪ ላለመያዙ ዋስትና የለውም፡፡ ካሱ በደረሰበት ጭንቀት ነፍሱ የሾለከችው መስሎታል፡፡ ለጊዜውም ቢሆን በድን ሆኗል፡፡ ሥነልቡናው ሙቷል፡፡ በሞትና በህይወት መካከል ቆይቶ ወደ ቀልቡ ተመልሶ ልብሶቹን ቢለብስም ከገባበት ጭንቀትና ፍርሃት መመለስ አለመቻሉን እንዲህ ይገልጸዋል፡፡

> ወደ ቀልቡ ሲመለስ ልብሶቹን መልበስ ጀመረ፡፡ ወደ ሱሪው ገባ፣ ወደ ኮቱ ገባ፣ በመጨረሻምወደ ጫማው ገባ፣ ግን በኮንዶሙ ሽንቁር በኩል ከገባው አዲስ ፍርሃት ገላው መጋረድ አልቻለም ፡፡ ከx-pub ሲወጣ ወደ ላይ አንጋጠጠ፤ በሰማዩ ገጽ ላይ ከዋክብት እንደፈንጣጣ ተበትነዋል፡፡ (በእውቀቱ፣1999፣110)

ካሱ ከገጠመው አስፈሪና አስጨናቂ ችግር ለመውጣት የሚሞክራቸው ነገሮች ሁሉ ለገጠመው ችግር መፍተሄ ከማስገኘት ይልቅ የባሰ እና ተጨማሪ ጭንቀትና ፍርሃትን ነው የሚያመጡበት፡፡ ካሱ መሃላ ማፍረሱን ተከትሎ ከመጣበት ችግር ያወጣኛል ያለው ወሲብ ያላሰበውን ጭንቀት በማስከተል በመኖርና ባለመኖር መሃል አስቀምጦታል፡፡ ለጊዜው

ራሱን አረጋግቶ ወደ ቀልቡ ቢመለስም " በሽንቁሩ በኩል ከገባው ፍርሃት ገላውን መጋረድ አልቻለም" የሚለው በተቀደደው ኮንዶም በኩል ኤችአይ ቪ ላለመተላለፉ እርግጠኛ መሆን ባለመቻሉ ጤነኛነቱን ማመን አለመቻሉ ነው የሚያሳየው፡፡

ወደ ሰማይ አንጋጦ የተበታተኑ ኮከቦችን ማየቱ በልብ ወለዱ ውስጥ የሞቱ ሰወች ወደ ኮከብነት እንደሚለወጡ በተገለጸው መሰረት እሱም በጭንቀት ውስጥ ሆኖ በኮንዶሙ ሽንቁር በገባበት የፍርሃት በሽታ የሚመጠውን ሞቱን እያየ ነው፡፡ገጽ(፣36 እና49)

ስለ ጭንቀት በልብ ወለዱ ውስጥ ሌላው ማሳያ መቅረብና መራቅ በሚለው ክፍል ውስጥ የሚገኘው ዮፍታሄ የተባለው ገጸባህሪ ነው፡፡"የልጅነት አስተዳደጋችን ላሁኑ ማንነታችን ወሳኝ ነው" የሚለው የፍሮይድ ፍልስፍና ከፍካሬ ልቡና ንባብ አንጻር በግልጽ ሚታየው ከዚህ ላይ ነው፡፡ ዮፍታሄ በልጅነቱ ከልክ ባለፈ የቤተሰብ ቁጥጥር ነጻነቱን አጥቶ በጭንቀት ያደገ ነው፡፡ በልጅነቱ ያጣውን ነጻነት በወጣትነት ዘመኑ አጥቶ ላለመኖር ሲሸሽ የሚታይና ለማምለጥም በጭንቀት የሚሰቃይ ገጸባህሪ እንደሆነ በልብ ወለዱ አጽመ ታሪክ አይተናል ፡፡ አሁን ላይ ለሚታየው ጭንቀቱ መንስኤ የሚሆነውም የልጅነት አስተዳደጉ ነው፡፡ በልጅነቱ ለታየው የከፋ ቁጥጥር መንስኤ የሚሆነው ደግሞ ታላቅ ወንድሙ በነጻነት በማደጉ ለአካለ መጠን ሲደርስ ወጥቶ በመጥፋቱ እንደ ወንድሙ እንዳይሆን በስርዓት ማደግ አለበት በሚል የቤተሰብ ውሳኔ እንደሆነ "የዮፍታሄ ልጅነት የታላቅ ወንድሙን የአስተዳደግ ስህተት ማረሚያ ሆነ"፡፡ የሚለው ሃሳብ ያስረዳል ፡፡ ገጽ(129)

ዮፍታሄ በልጄነቱ ሲበላም፣ ሲጠጣም፤ ሲተኛም፣ ሲያጠናም አጠቃላይ እንቅስቃሴው ሁሉ በእናቱ የታጠረ ነበር፡፡ በልጅነት አስተዳደጉ እሱ የመረጠውን ምግብ ሳይሆን እናቱ የመረጠችውን የስጋ አይነት ተገዶ ይበላል፡፡ እሱ በፈለገው ጊዜ መተኛተ እሱ በፈለገው ሰዓት ማጥናት አይችልም፡፡ እናቱ በምታዘው እና በምተፈቅድለት ሰዓት ነው፡፡ ማንኛውም አጠቃላይ እንቅስቃሴው በእናቱ የተከበበ ወይም የታጠረ ነበር፡፡ በአጠቃላይ አናቱ ከሱ የምትርቀው አባቱ ከቤት በሚመጡባቸው ጥቂት ጊዜያት ብቻ ነው፡፡ (በእውቀቱ፣1999፣129-130)

ዮፍታሄ ከእናቱ ያልተገባ ቁጥጥር የሚያመልጥበት መፍትሄ በማጣቱ ያስጨንቀው እንደነበር አንድ ቀን እናቱ "ስታድግ ምን ታደርግልኛለህ"? በማለት ስትጠይቀው "እንደ አባየ ብዙ ጊዜ ፊልድ የምትወጭበት ሥራ እሰጥሻለሁ"፡፡ ይላል፡፡ አባቱ መስክ በመውጣቱ

ከሚስቱ እቅፍ እንደሚገላገለው ሁሉ  እሱም እናቱ መስክ ስትወጣ ከእናቱ ያልተገባ አጥር ለመገላገል መመኘቱ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ህጻንነቱ አለፈ፡፡ ዮፍታሄ አደገ ዩንቨርሲቲ ገባ ፡፡ ዩንቨርሲቲ እንደገባ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ተገዶ እንዲበላ ሲያስጨንቀው የነበረውን ስጋ የነካው ምግብ መተው ነው፡፡ ሌላው ገንዘብ ካልቸገረው በስተቀር ወደ ወላጆቹ ቤት አለመሄድ ነበር ፡፡ ይህን ያደረገው ደግሞ የናቱን ስልጣን ለመቀነስ ነው፡፡(በእውቀቱ፣1999፣131)

ዮፍታሄ ዩንቨርሲቲ መግባቱ በእናቱ ምክንያት የሚመጣበትን ጭንቀት ቢቀንስለትም የእናትና አባቱ ቤትና መንፈስ ካለበት ከተማ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ መሆኑ ሙሉ ነጻነቱን ስላላጎናጸፈው ከክፍለ ሃገር ከቤተሰቦቻቸው እርቀው በመጡ ተማሪዎች ይቀናል፡፡ (በእውቀቱ፣1999፣፣131)

ዮፍታሄ ከዩንቨርሲቲ ከተመረቀ በኋላ ወደ ወላጆቹ ቤት ከመሄድ ይልቅ ከወላጆቹ በጣም የራቀ መንደር ውስጥ ተከራይቶ መኖር ጀመረ፡፡ ለአንድ ዓመት ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ሳይሄድ ኖረ ፡፡/ገጽ፣132/

ከዚህ ማንነት ውስጥ ተፈልቅቆ የወጣው ዮፍታሄ አብራው ከምትሰራው አቢ/አብዮት/ ጋር ፍቅር ጀመረ፡፡ ፍቅር በጀመረ በሳምንቱ ከስራ ተባረረ፡፡ ከስራ በተባረረ በሦስተኛው ቀን ለቤት ኪራይ የሚከፍለው ገንዘብ ስላልነበረው ከባድ ጭንቀት ውስጥ ገባ ፡፡ በዚህ ጭንቀት ውስጥ እንዳለ በአጋጣሚ አቢ ልትጠይቀው ቤቱ መጣች፡፡ ካላት ከራሷ ከሌላት ከሌላ ሰው ተበድራ ላንድ ወር የቤት ኪራይ የሚሆን ገንዘብ ሊጠይቃት ፈለገ፡፡ ግን ደግሞ ለመጠየቅ ፈራ፡፡ በዚህ ፍርሃትና ጭንቀት ውስጥ እንዳለ " 'ከሁለት ቀን በኋላ ቤት አይኖረኝም' የሚል ቃል እንደ ንጥሻ አመለጠው"፡፡ /ገጽ፣135/ አቢም መልሳ "እኔ እስካለሁ ድረስ ስለቤት ማሰብ የለብህም" ፡፡ በማለት የቤት አለመኖር ጭንቀቱን ለጊዜውም ቢሆን ስታባርርለት ይታያል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የጥናቱን ንድፈ ሃሳብ ባየንበት  የመቀራረብ ፍርሃትን ስናይ ገንዘብ ማጣት እና ስራ ማጣት ፍርሃትንና ጭንቀትን ሰለሚያባብሱ ለሥነ ልቦናዊ ሞት እን ቀውስ ምክንያት እንደሆኑ አይተናል፡፡

በማግስቱ አቢ ፈቃደኛነቱን ሳታረጋግጥ ኮንትራት ታክሲ ይዛ መጥታ ሻንጣዎቹን መጫን ስትጀምር ሌላ ጭንቀት ወረረው፡፡ እኔ እሰካለሁ ስለቤት አትጨነቅ ያለችው የአቢ ተስፋ

ተመልሶ ጠፋ። አቢ ስለቤት አትጨነቅ ያለችው ከኔ ቤት በጥገኝነት ትኖራለህ ማለቷ እንደሆነ የገባው በዚህ ጊዜ ነበር። ዮፍታሄ ከሁለት ወገን በጭንቀት ተወረረ። ወደ አቢ ቤት ሂዶ በጥገኝነት መኖርን እንቢ እንዳይል ለጊዜውም ቢሆን ገንዘብ እና ቤት የለውም። እሽ ብሎ ከአቢ ጋር በአቢ ቤት እንዳይኖር ከእናቱ የራቀበት እስር ቤት ተመልሶ መጣበት። በብቸኝነቱ አግኝቶት የነበረው ነጻነት ያለፍላጎቱ በገንዘብ ማጣት ምክንያት ወደማይፈልገው የቤተሰብ አጥር ውስጥ ሊከተው ነው። ዮፍታሄ "እሪ ብሎ መጮህ አማረው" ነገር ግን አማራጭ ስላልነበረው "ሳይጮህ በቤቷ ውስጥ ለጥቂት ወራት ኖረ"። ገጽ(135) ከዚያቀን ጀምሮ ተለያይተው አያውቁም ። በመካከላቸው የነበረችው ስንዝር የምታክል እርቀት ጠፋች። ዮፍታሄ በእናቱ አቅፍ ውስጥ በነበረ ህይወቱ ባጣው ነጻነት የገባበትን ጭንቀት ከናቱ በመራቅ ለመገላገል ቢችልም አሁን ደግሞ አብሮ በመኖሩ ጭንቀቱ በአቢ ተደገመ።

> ለዮፍታሄ ፍቅር እንደ ሞባይል ቴሌፎን በየቀኑ ቻርጅንግ ይፈልጋል። ይህ ቻርጅንግ ናፍቆት ነው። ናፍቆት የሚኖረው ደግሞ የአቢ ድምጽ ድርሽ በማይልበት ቦታና ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው። ለአቢ ግን ፍቅር ማለት አግዜር ነው። ርቀትን ይደመስሳል። ስለዚህ እንደ እናቱ ሁል ጊዜ አብራው ናት።(በእውቀቱ፣199፣136)

ዮፍታሄ አቢን በፍቅር ይፈልጋታል ። ነገር ግን ዮፍታሄ ፍቅር ትርጉም የሚኖረው ተራርቆ ሲኖሩ ነው ብሎ ሰለሚያምን አቢ እንደናቱ ሁል ጊዜ አብራው መኖሯ በብቸኝነት ኑሮ የጀመረውን ነጻነት ሰለሚያሳጣው ከአቢ ጋር ለመኖር በአቢ ቤትመኖሩ ሲያስጨንቀው ይታል። ለአቢ ደግሞ ፍቅር ትርጉም የሚኖረው አብሮ ሲኖሩ ነው በማለት የሚያስጨንቃት ከዮፍታሄ መራቅ ነው።

ዮፍታሄ በልጅነቱ የሆነውን በወጣትነቱ ላለመሆን አስቧል። ተመልሶ ወደ ነበረበት በቤተሰብ የታጠረ የህይወት ጭንቀት ላለመግባትና ከአቢ ጋር የጀመረውን ፍቅር በርቀት መቀጠል ፈልጓል። "ፍቅሩን ከውድቀት ለማዳን ጥቂት እርቀት ማግኘት እንዳለበት ተሰማው። ቶሎ ስራ እንዲያገኝ ፀለየ። ፀሎቱ ተሰማ ። ለግዜው ስራ ማግኘቱን ለአቢ ሊነግራት አልፈለገም" ። /ገጽ፣136/ ስራ ማግኘቱን መንገር ያልፈለገው ደግሞ ሁለቱ ፍቅርን የሚረዱበት መንገድ የተለያየ ስለሆነ ስራ ካገኘ ጥሎኝ ይሄዳል በሚል እንዳታኮርፈው እና በመሄድ መመለስ አለና የቀጣይ ህይወቱ ስላስጨነቀው እንደሆነ እንረዳለን።/ገጽ፣140/

ዮፍታሄ በዚህ ከባድ ጭንቀት ውስጥ እያለ ሌላ ጭንቀት ፣ ሌላ ፍርሃት ሌላ አብሮ ለመኖር የበለጠ ተስፋ የሚያስቆርጥ ችግር ተፈጠረ፡፡ አቢ "አረገዘች" እናም ሲታጠር የነበረው ስብዕናው፣ ነጻነት ሲሻ የነበረው ማንነቱ አደጋላይ እንደወደቀ ተሰማው፡፡ አሁን የገጠመውን ጭንቀት አድራሻን አጥፍቶ ከመራቅ ውጭ የሚገለግለው የለምና የት እንደሄደ ሳይነግራት ጥሏት ጠፋ፡፡

ዮፍታሄ የራሱን ታሪክ ሰው እንዲያውቅበት አይፈልግም፡፡ ስለማንነቱ ልቡናው አስገድዶት ስለራሱ የሚናገረው ታሪኩ አድራሻውን ሳይናገር መጥፋቱን ያረጋግጣል ፡፡ ትልቅ መዳፍ ካላት እናት፣ትልቅ ሳምሶናይት ከሚያንጠለጥል አባት፣አዲስ አበባ ተወለድኩ፡፡ ከዞያ በፊት ባንድ በሌላ ማእከል ውስጥ 'አማካሪ' በሚል የስራ ክፍል አገለግል ነበር ፡፡ ከማዕከሉ ስባረር አቢ የተባለች ቆንጆ ወደ ቤቷ ወሰደችኝ፡፡ ከዚያ ያለፍቃዴ አረገዘችብኝ፡፡ አንድ ቀን ሥራ አገኘሁ፡፡ ከዚያ ከቤቷ ወጣሁ፡፡ እስካሁን አልተመለስኩም፡፡ በማለት ከቤተሰብ እና ከጓደኛ ሸሽቶ ለብቸኝነት ተጋልጦ እንደሚኖር ያሳያል፡፡ ገጽ(114)

## 3.4. ቀቢፀ ተስፋ /Despair

ቀቢጸ ተስፋ ወይም ተስፋ መቁረጥ የሰው ልጅ አንድ ነገር ለመስራት፣ ለማግኘት ፣ለመድረስ አስቦ እየተጋ ባለበት ጊዜ በሚያጋጥመው ሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሯዊ ሁኔታ ካሰበው ወይም ከተመኘው ሳይደርስ ሲቀር ወይም የገጠመውን ችግር ታግሎ ማለፍ ሲያቅተው የሚከሰት አካላዊ ወይም ሥነ ልቡናዊ ጉዳይ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት አይተናል፡፡

ይህ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ደግሞ በልብ ወለዱ ውስጥ ካሰቡት ሳይደርሱ የተመኙትን ሳይሆኑ የሚገጥማቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ታግሎ ማለፍ የሚያቅታቸው ገጸባህሪያት ይታያሉ፡፡ ተስፋ ቆርጠው ራዕያቸውን ተነጥቀው ወይም በልጅነታቸው ያጡትን ነጻነት በጎልማሳነታቸው ላለማጣት ሞክረው ሲያቅታቸው ተሰፋ በመቁረጥ ራሳቸውን ለማጥፋት የሚጥሩ፣ ከማህበራዊ ኑሯቸው ተፈናቅለው የሚሰደዱ እና ከቤተሰባቸው እርቀውና ትዳራቸውን ትተው በብቸኝነት ራሳቸውን አግልለው የሚኖሩ ገጸባህሪያትን እናያለን፡፡

ጋዜጠኛው ገጸባህሪ ከድሃ ቤተሰብ ተወልዶ በድህነት ያደገና የ1997 ምርጫ ተከትሎ በተከሰተው ብጥብጥ ከመደበኛ ስራው የተፈናቀለ ነው፡፡ አንድሮ ሜዳ የሃብታም ልጅ በመሆኗ በኢኮኖሚም ትደግፈው እንደ ነበር "አንድሮሜዳ ቤቷ እየወሰደችኝ፣ አንዳንዴም ምሽት ቤት እየጋበዘችኝ፣ ትንሽ ተላመድን፡፡ እስከ አኩለ ሌሊት አብረን እንቆያለን፡፡ ቡና ታፈላልኛለች፣ ሲጋራ ትጋብዘኛለች፣ ወረቀትና እስክቢርቶ ትሰጠኛለች"፡፡ በዚህ ሁኔታ በመተሳሰብና በመረዳዳት ለወደፊትም አብረው ለመኖር ይመኝ የነበረ ነው፡፡ ነገር ግን ህይወት እንዳሰበውና እንደተመኘው አልሆነችም፡፡ አንድ ቀን አንድሮሜዳ በራሷ መኪና ወደ ቤቱ እየሸኘችው እያለ ባጋጠማት የመኪና ግጭት ሞተች፡፡ እሱም በድንጋጤ ራሱን ስቶ ስለነበረ ምን እንደተፈጠረ ማን እንደወሰደው በማያውቀው ሁኔታ ሲነቃ ራሱን ሆስፒታል አልጋ ላይ እንዳገኘ ይገልጻል፡፡/ገጽ፣10/ እሷ ሙታ እሱ መትረፉ የቀጣይ ህይወቱ ተስፋ እንደሌለው በማመን "ለምን ተረፍኩ" ብሎ ራሱን ይጠይቃል፡፡ የቀጣይ ህይወቱን ተስፋ ቢስነት እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ "መጭው ጊዜየ እንደ ታከምኩበት ሆስፒታል ግድግዳ አንዳች ማራኪ ምስል ያልተሰቀለበት ሆኖ ታየኝ፡፡ የአንድሮሜዳ መኪና ተጠረማምሶ ከቆመበት ቦታ የሚቀጥል የእድሜ ጎዳና አልታይህ አለኝ፡፡ እራሴን እንደማጠፋ በጣም እርግጠኛ ሆንኩ፡፡"( በእውቀቱ፣1999፣10)

ገጸባህሪው ከአንድሮሜዳ ጋር ጀምሮት የነበረው የመረዳዳት የመተሳሰብ እና የፍቅር ሕይወት በወደፊት ህይወቱ ላይ ሰንቆለት የነበረው ተስፋ በሷ መሞት ባንዴ ተሟጦ ሲጠፋበት ይታያል፡፡ የመኖር ተስፋው ወደ ቀቢጸ ተስፋነት ተለወጠ፡፡ ከፊቱ ህይወቱን የሚያስቀጥል መልካም ነገር አልታይህ አለው፡፡ የቀጣይ ህይወቱ አንዳች ማራኪ ነገር ከማይታይበት የሆስፒታል ግድግዳ እና ግጭት ደርሶበት ተጨረማምቶ ከቆመ ተጠግኖ ሊያገለግል ከማይችል መኪና ጋር ተመሳስሎ ታየው፡፡ የገጠመው የሥነ ልቡና ቀውስ ከነበረ ማንነቱ አስወጥቶ ወደ ሌላ ማንነት አባረረው፡፡ አማራጩ ራስን ማጥፋት ሆኖ ታየው፡፡

ነገር ግን ለአንድሮሜዳ ካለው ፍቅር የተነሳ በቀብር ስነ ስርዓቷ ላይ የተነበበው አንድ አንቀጽ የማይሞላ የህይወት ታሪኳን ሲሰማ ለጊዜውም ቢሆን እራሱን ከማጥፋት ይልቅ የበለጠ ለቅሶ የበለጠ ሃዘን ሲሰማው ይታያል ፡፡ ይህንንም እንዲህ ይገልጸዋል ፡፡

> አሁን ግን ያለ ልምዴ ፊቴን በመዳፎቸ ቀብሬ አለቀስኩ፡፡ ያለቀስኩት አንድሮሜዳ ስለሞተች አይደለም ፡፡ የሃያ ሰባትዓመት ጎይወቷ በአንድ ሽራፊ አንቀጽ ሲደመደም ስለሰማሁ ነው ፡፡ ይህን የጻፍኩት ከዚህ በመነሳት ይመስለኛል ፡፡ አንድሮሜዳን አፈቅራት ነበር ፡፡ ፍቅር የያዘኝ ከአንድ አንቀጽ የማይበልጥ ህይወት ታሪክ ካላት ሴት ጋር ነው ብሎ ለመቀበል ግን ከበደኝ ፡፡ የተሸበሸበ ታሪኳን ማራኪ ቀለም እንዳለው ዣንጥላ ካልተዘረጋ እንደማያምር ገባኝ ፡፡ ገድሏን ከአንድ አንቀጽ ወደ ብዙ ገጾች ላሳድገው ተነሳሁ ፡፡(በእውቀቱ፣1999፣8)

በማለት የአንድሮሜዳን ታሪክ አስፋፍቶ ለመጻፍ ሲነሳና ጽፎ ሲጨርስ በኢ-ንቁ አዕምሮው የያዘውን ተስፋ የቆረጠ ስሜት ተግባራዊ ለማድረግ "ጽፌ ስጨርስ ምን ይቀረኛል? ራሴን ማ…ማ… ማጥፋት"፡፡/ገጽ፣10/ በማለት የመኖር ተስፋውን ተስፋ በመቁረጥ ሲያጨልመው ይታያል ፡፡

ገጸባህሪው ጓደኛው አንድሮሜዳ ከሞተች በኋላ ቀጣይ የተሻለ ህይወት እንደማይኖር ተስፋ መቁረጡን  በተደጋጋሚ ራሱን ለማጥፋት ከሚያስበው እና ከሚመኘው መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህ መጥፎ ሃሳብና ምኞት የተዳረገው ደግሞ በአንድሮሜዳ ሞትና እሱም ከመኪና አደጋ ከተረፈ በኋላ በነበረው ጤናማ ሥነ ልቡናዊ  ማንነት እንዳልቀጠለ በሁለት የተለያዩ ሥነ ልቡናዊ ማንነቶች ውስጥ እየኖረ እንዳለ እንዲህ ይገልጸዋል ፡፡

"ከመኪና አደጋ ከተረፍኩ በኋላ የዱሮው አይደለሁም፡፡ ከሆስፒታል አልጋ ላይ የተነሳሁት እንደ ሄርማፍሮዳይት ሁኜ ነው፡፡ ከፊሉ ገለየ ንጉስ ሻርያር፣ ከፊሉ ሻራዛድ፡፡" /ገጽ፣11/፡፡ ገጸባህሪው ከመኪና አደገው በፊት  በነበረ ሥነ ልቡናዊ ማንነቱ አለመቀጠሉን "የዱሮው አይደለሁም"፤በሁለት የተለያዩ ማንነቶች ውስጥ መግባቱን "ከፊሉ ገለየ ንጉስ ሻርያር ከፊሉ ሻራዛድ" ነው፡፡ ሲል ይገልጻል፡፡ አንድ ጤነኛ የሆነ ሰው ሁለት የተለያየ ጤናማ ሥነ ልቡናዊ ማንንት  አለኝ ለማለት ሳይሆን  ባጋጠመው አደጋ ተስፋ በመቁረጥ ሥነ ልቡናዊ አስተሳሰቡ በንቁና ኢ-ንቁ ሥነ ልቡናዊ ማንነት ውስጥ መግባቱን እና በቀውስ ውስጥ ያለ መሆኑን  ነው የሚነግረን ፡፡

በገጸባህሪው ላይ አያደገና እየሰፋ የመጠው የቀቢጸ ተስፋ ስሜት ገጸባህሪው እንዳሰበውና እንደተመኘው በፍጥነት እራሱን ወደማጥፋት ባይሄድም ሙያውን አዳብሮ የሙያው ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ጤነኛ ያልሆነው ሥነ ልቡናዊ አስተሳሰቡ ወይም ከሦስቱ የአዕምሮ ክፍሎቹ ኢድ/Ed/ አብዝቶ እየጨመረ በመሄዱ ለመስራት ተስፋ እየቆረጠ ለተለያዩ ሱሶች ተገዥ እየሆነ ከመደበኛ የህይወት እንቅስቃሴው ሲወጣ ይታያል፡፡

"አንድሮሜዳ ከተቀበረች ሦስት ሳምንት ሆናት፡፡ እጠጣለሁ ከትናንት የተሸለ ስካር ፍለጋ ከቡና ቤት ወደ ቡና ቤት እዞላለሁ ፡፡ ከዚያም ሃረግ በለበሰ አጥር ስር እሸናለሁ "፡፡(በእውቀቱ፣1999፣8 እና 48) ገጸባህሪው ሟች ፍቅረኛውን እያስታወሰ ሞትን በመጠጥ የሚበቀለው ይመስል በየቡና ቤቱ እየዞረ የመጠጥ ሱሰኛ ሲሆንና ተስፋ ቆርጦ ከመደበኛ ማንነቱ ሲርቅ ይታያል፡፡ ይህም ሥነልቡናዊ ሞቱን ያሳያል፡፡

ከቀቢጸ ተስፋ ጋር በተያያዘ ማየትና መጋረድ በሚለው በክፍል ሁለት የሚገኙ ካሱና እስቴላ የሚባሉ የሁለት ገጸባህሪያትን ጉዳይ ማየት ተገቢ ነው፡፡ ሁለቱ ገጸባህሪያት በፍቅር ተጣምደው በአንድ ጣራ ስር የሚኖሩ ነበሩ፡፡ ሁለቱም ልጅ ወልደው አይናቸውን በአይናቸው ለማየት የሚጓጉ ጥንዶች ነበሩ፡፡ /ገጽ፣57-59/ ነገር ግን ህይዎት እነሱ እንዳሰቡትና እንደተመኙት አልሆነላቸውም፡፡ መጀመሪያ ያረገዘችውን በአንድ ወሯ አስወረዳት፡፡/ገጽ፣58/ "ሃዘኑ እንዳለፈላት እንደገና ለመሞከር ወሰነች፡፡ …ከሦስት ወር በኋላ እንደገና ጸነሰች፡፡ እንደ ተመኘው ሴት ልጅ ተወለደችለት፡፡" ካሱ ሴት በመውለዱ ከፍተኛ ደስታ ውስጥ ገብቶ በየቀኑ የሚያመላልሰው አበባ የቤቱን ሩብ ሸፍኖታል፡፡ በሃገራችን ባህል መሰረት አበባ በብዛት የሚቀመጠው ቀብር ላይ ነው፡፡ ለዚህ ይመስላል በካሱ ቤት በተከማቸው አበባ ምክንያት ቀጣይ ሊመጣበት የሚችለውን መከራ ሲተነብይ "ካሱ ይጠንቀቅ! ያበባ ብዛት፣የመጭው ቀብር ንግርት ነው" ይላል /ገጽ፣60/፡፡ ንግርቱ እውነት ሆኖ "አራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ልጁ ሞተች"፡፡ ቤቱ በሃዘን ተሞላ ፡፡ በዚህ የልጃቸው ሞት ምክንያት ከገባችበት ሃዘን ለመገላገል ስትል እስቴላ ከዚህ ቀደም በምትሰራበት መስሪያ ቤት አግንተው የነበረውን ወደ እንግሊዝ አገር የመሄድ ሃሳብ ያነሳችው፡፡

ካሱ በበኩሉ ሚስቱ ልጅ ወልዶ ለማሳደግ የታደልኩ አይደለሁም በሚል ከገባችበት ከባድና ተስፋ አስቆራጭ የሀዘን ቀውስ የተለያዩ ማባበያዎችን ተጠቅሞ ሀዘኗን በማስረሳትና የእንግሊዝ አገር ጉዞዋን አስቀርቶ በትዳራቸው አብረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ሲጥር ይታያል፡፡ በዚህ ለባልና ሚስቱ ተስፋ መቁረጥ ምክንያት የሚሆነው በተደጋጋሚ ሞክረው ያልተሳካላቸው ልጅ ወልዶ የማሳደግና የልጅን ፍቅር የማጣት የሥነ ልቡና ጣጣ ነው፡፡ ሌለው ሚስቱ በዚህ ልጅ ወልዶ የማሳደግ፣ የልጅን ፍቅር የማግኘት እድል የለኝም በሚል ተስፋ ቆርጣ ለስደት መነሳቷ ካሱን ከፊቱ የታየው የሚስትን ፍቅር አጥቶ በብቸኝነት የመኖር አባዜ ለፍርሃት፣ ለጭንቀትና ለተስፋ ቆራጭነት እንዳጋለጣቸው ያሳያል፡፡

ካሱ ከዚህ ተስፋ የቆረጠ ሥነ ልቡናዊ ጣጣ ሊገለግለው የሚችለው ቢያንስ ልጁን ባያገኝ ሚስቱን ላለማጣት ከብቸኝነት ለመራቅ የተለያዩ የማባበያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሚስቱን ከስደት ማስቀረት ነበር፡፡ ለዚህም ሚስቱን ለማባበል ከተጠቀመበቀቸው ዘዴወች አንዱ በቀጥታ እንበዋን በማበስ ሲሆን እሷ ግን አልቅሳ እርሟን እንዳታወጣ የማልቀስ እድል እንዳልሰጣት በመቁጠር ድካሙን ከንቱ ታደርግበታለች፡፡

> *አሁን ለምን ለመሄድ ፈለገች? ካሱን ማየት አስጠልቷታል፡፡ እንደ ወፍ በርራ እሱን በማታይበት ቦታ መሄድ ፈለገች፡፡ እሱ ግን ብቸዋን ተኮርትማ እንድትቀመጥ እንኳን አይፈቅድላትም ነበር፡፡ አንደልቧ እንድታለቅስ እድል አይሰጣትም፡፡ በጠንካራ ክንዱ ያቅፋትና በጣቶቹ እንበዋን ይጠርግላታል፡፡ ልጇን የገነዘበት ጣቱ የሞት ጣት መስሎ ይታያታል፡፡ ይቀፋታል፡፡ ከዚህ ጣት በብዙ ማይል ርቆ የመቆየት ዕድልን ያለመቅማማት መቀበል ነበረባት፡፡*(በእውቀቱ፣1999፣62)

ካሱ እሷን ለማጽናናት ሀዘኗን ለማስረሳት የሚያደርገው መልካም ነገር ከመቀበል ይልቅ ስበባ-ስበብ እየፈለገች ለበጎ ያለውን ወደ መጥፎ እያዞረች እሷን ለማጽናናት ያቀፈበትን እና እንበዋን የጠረገበት እጁን የሞት እጣት መስሎ ታየኝ በሚል የሞ ፍርሃት እሱን አየጠላች ከሱ ለመራቅ እየፈለገች ስትመጣ ሌላ የማባበያ ስልት መጠቀም ፈለገ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ለማጽናኛነት ወይም ሃዘኗን ለማስረሳት የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀም ይታያል ፡፡ ከነዚህም በመጀመሪያ በአንድ ወሯ ማስወረዷን እና አሁን የሞተችውን ልጃቸውን ታሳቢ በማድረግ "አይዞሽ የኔ ማር በሶስተኛው ጥሩ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም"፡፡/ ገጽ፣62 / በማለት የሦስት ቁጥርን በሃይማኖት ወይም በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ የሚገኘውን የዮናስን እና የኢየሱስን በሶስተኛ ቀን ከአሳነባሪ ሆድ መዉጣትና ከሞት መነሳትን በመንገር እኛም በሶስተኛው ጥሩ ይሆናል በማለት ሊያጽናናት ይሞክራል ፡፡ /ገጽ፣62-63/ ነገር ግን አሁንም ማጽናኛውን ከመቀበል ይልቅ " 'የኔን ማህጸን ከአሳ ነባሪ ሆድ ጋር ስታመሳስለው ትንሽ አታፍርም' በማለት የበለጠ እንድታለቅስ አደረጋት" /ገጽ፣63/ ካሱ እሷን ለማጽናናት የሚያደርገው ሙክራ በሷ በኩል ተቀባይነት ባያገኝም እሷ ከገባችበት ተስፋ የመቁረጥ ስሜት በማስወጣት ካሰበችው የእንግሊዝ አገር ስደት ለማስቀረት አሁንም ተስፋ ሳይቆርጥ ሌላ የማጽናኛ ስልት ይጠቀማል ፡፡

ለሶስተኛ ጊዜ የተጠቀመው የማጽናኛ ስልት የአባ አርጌነስን ፍልስፍና ተጠቅሞ ነበር፡፡ የአባ አርጌነስ ፍልስፍና "አለም ከመፈጠሩ በፊት ነፍሳችን እግዜሩን በድለዋል፡፡ ለዚህም በወህኒ እንዲቀጡ ተፈርዶባቸዋል፡፡ ወህኒው የሰው ስጋ ነው፡፡ አንድ ሰው በዚህ ምድር ላይ መቶ ዓመት ኖረ ማለት ነፍሱ መቶ ዓመት በወህኒ ስጋ የሚያስቀጣ በደል ፈጽማለች ማለት ነው "፡፡ /ገጽ፣63/ ይህን ታሪክ ነግሮ "ልጁ የሞተችው በሥጋ ታስራ ለብዙ ዘመን መኖር ስለማይገባት ነው፡፡ ህዋውን እንደጉም ከሞሉት ነፍሶች ውስጥ የተሻለ ቅድስት ስለነበረች ነው፡፡" ብሎ በድጋሜ ሊያጽናናት ሞከረ ፡፡ /ገጽ፣64/ ካሱ ይህን ሃሳብ ተጠቀውሞ ለማጽናናት ይሞክር እንጅ አሁንም እስቴላ በልጆቿ ሞትና በካሱ የማባበያ ስልት የበለጠ ሆድ ሲብሳት ይታያል፡፡ በሚቀርበው የማጽናኛ ሃሳብ ሃዘኗን ከመርሳትና የስደት ሃሳቧን ከመቀየር ይልቅ የበለጠ ሆድ እየባሳት የበለጠ ተስፋ እየቆረጠች እንደትሄድ አድርጓታል ፡፡

ካሱ የአባ አርጌነስን ፍልስፍና ተጠቅሞ ልጃችን የሞተችው በስጋ ታስራ መኖር ስለሌለባት ነው፡፡ ከሌሎች የተሸለ ቅድስና ስላላት ነው፡፡ ሲላት እስቴላ ጉዳዩን ወደ ራሷ በማዞር የበደለኝነት የህጢአተኝነት ስሜት ተሰማት " ልክ ነህ! አለች እስቴላ 'እኔ ይህን ያህል እድሜ የቆየሁት የልጀን ያህል ቅድስና ስለለለኝ ነው' በማለት የበለጠ ሆድ ባሳት"፡፡ /ገጽ፣64/ እስቴላ በልጆቿ ሞት ከገባባት ተስፋ የመቁረጥ ስሜት አስወጥቶ፣ ከስደቷ አስቀርቶ በሰላም ከሚስቱ ጋር ለመኖር በሚል ካሱ የተጠቀመው የማጽናኛ ሃሳብ ሁሉ በእስቴላ በኩል ከመጽናናት ይልቅ የበደለኝነት እና የጥፋተኛነት ስሜት ተጨምሮበት ለበለጠ ሃዘን፤ ለበለጠ ሆድ ብሶት፤ ለበለጠ አለመግባባት፤ ለበለጠ ተስፋ መቁረጥ ሲዳርጋት ይታያል፡፡ በተለይም ካሱ የአባ አርጌነስን ፍልስፍና ተጠቅሞ ያቀረበው ማጽናኛ እስቴላን ከልጆቿ ሃዘን በተጨማሪ እኔ የልጀን ያህል ቅድስና የለኝም በሚል ከሥነህይወታዊ ሞት በተጨማሪ በደለኛ ነኝ ጥፋተኛ ነኝ በሚል የነፍስ ሞትን በመፍራት ሃሳቧን ከልጇ ወደ ራሷ በመውሰድ የበለጠ ተስፋ እንድትቆርጥ መሆኗ ካሱ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ በመቅረቱ እስቴላን ከሃዘኗ አስወጠቶ የእንግሊዝ አገር ጉዞዋን አስቀርቶ በሰላም አብረን እንኖራለን የሚለው ተስፋው ተሟጠጠ፡፡

እስቴላ በልጆቿ ሞትና በካሱ የማጽናኛ ሃሰቦች ምክንያት ተስፋ በመቁረጥ ከካሱ ጋር ላለመኖር፤ ካሱን ላለማየት፣ ከካሱ ርቆ ለመሄድ እንደተመኘችው ሁሉ ካሱም ሚስቱን ከገባችበት ተስፋ የቆረጠ ስሜት አስወጥቶ በሰላም እኖራለሁ በማለት ያደረገው ጥረት ሁሉ

ተቀበቀይነት ሳያገኝ መቅረቱና የባሰ ተስፋ እንድትቆርጥ ማድረጉ እሱም የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶት ተስፋ በመቁረጥ እስቴላን ላለማየት ወሰነ፡፡እስቴላ ወደ አሰበችው "ወደ እንግሊዝ እንድትሄድለት፤እንድትሄድለት፤እንድትሄድለት የተመኘው ይኸኔ ነው" ሲል ይታያል፡፡ /ገጽ፤64/

ባልና ሚስቱ ገጸባህሪያት የተመኙትን ወልዶ የማሳደግ እድል ባለማግኘታቸው በስቴላ ላይ የፈጠረው ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ስሜታቸውን ተቆጣጥረው ተደማምጠው መፍቴሄ ላይ መድረስ ባለመቻላቸው የገጠማቸውን ችግር ተቋቁሞ ማለፍ እና በትዳራቸው መቀጠል አቅቷቸው ተሸናፊ ሲሆኑ ይታያል፡፡ በሁለቱም በኩል እያደገ የመጣው ተስፋ ቆራጭነት ከመሸነፍ የመጣ ነው፡፡ መሸነፍ ደግሞ አንዱ የሥነልቡና ሞት ባህሪ ነው፡፡ የሥነ ልቡና ሞቱ ደግሞ እስቴላን ለስደት፤ ካሱን ለብቸነት /ለመገለል/ ሲዳርጋቸው ይታያል፡፡

## 3.5. ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ግምት /Low self Esteem/

ለራስ የሚሠጥ ዝቅተኛ ክብር የርዕይ መነጠቅን እና ተስፋ ቆራጭነትን ተከትሎ የሚመጣና እኔ ከሌሎች በሃብት፣ በእውቀትና በአስተሳሰብ ያነስኩና በሌሎች ዘንድ ትኩረት የተነፈገኝ ነኝ ፡፡ ለጥፋት የተፈጠርኩ ነኝ፡፡ ለኔ የሚገባኝ ቅጣት ነው ከሚል የሞራል ውድቀት የሚመጣ እንደሆነ በምእራፍ ሁለት አይተናል፡፡

በልብ ወለዱ ውስጥ ለራሷ ዝቅተኛ ክብር መስጠቷ በግልጽ ከሚንጸባረቅባቸው ገጸባህሪያት ውስጥ በክፍል አንድ የአቢይ ገጸባህሪው ወይም የጋዜጠኛው ተመላላሽ እንጀራ ጋጋሪና ልብስ አጣቢ የሆነችው ሸዋየ የተባለች አስተኔ ገጸ ባህሪን አናገኛለን፡፡ ሸዋየ ድህነቷንና አለመማሯን ብቻ መሰረት በማድረግ እራሷን ዝቅ አድርጋ የምታይ እራሷን እንደጥፋተኛ የምትቆጥር ለኔ የሚገባኝ ቅጣት ነው ብላ የምታምን ገጸባህሪ ናት፡፡

የልብ ወለዱ የጊዜ መቸት ሲታይ 1997 ዓ/ም አካባቢ እንደሆነ ከላይ አይተናል፡፡ የታሪኩ የቦታ መቸትም አዲስ አበባ ነው፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ ለአዲስ አበባ የሁከትና የብጥብጥ ወቅት ነበር ፡፡ ሸዋየ የተለመደ ስረዋን ለማከናወን በተመላላሽ ወደምትሰራበት ቤት እንደሄደች በአዲስ አበባ አመጽ መነሳቱን በማወቅ አሰሪዋ ሸዋየ ስትሰራ ውላ ወደ ቤቷ ብትሄድ ችግር ይገጥማታል በሚል ቅንነት የተሞላበት ሃሳብ ሸዋዬን ምክር ቢጤ እንዲህ ይሏታል፡፡

"ታክሲ በከተማው የለም፣ ባውቶብስም መሄድ አጉል ነው፡፡ በመንገድ ላይ በተባራሪ ጥይት የሞቱ ሰወች አሉ ፡፡ እዚህ ብታድሪ ይሻላል"፡፡ አልኳት፡፡ ወዲያው በጭስ ይሁን በሃዘን በምን እንደረጠበ የማይታወቀውን ዓይኗን በእጅጌዋ እያበሰች "አይ! አይ! አይ አሁን እኔ መሃይሟ እያለሁ ስንቱ የተከበረ ሙቶ ይሆን" ትል ጀመር ፡፡/ገጽ፣41ና42/

አሰሪዋ በሰው ሰውነቷ ክብር ሰጥቶ በዚያ ሰዓት ወደ ቤቷ ብትሄድ ችግር ይገጥማታል በሚል የሷን ህይወት ለመታደግ እያሰበ እያለ  እሷ እራሷን  ዝቅ በማድረግ  በአለመማሯ ከሰው በታች እንደሆነች በመቁጠር  እኔ የማልጠቅም ሰው ነኝ የሚል እምነት በውስጧ በማሳደር እራሷን እኔ መሃይሟ ተቀምጬ ስንቱ የተከበረ ሙቶ ይሆን  በሚል መሞት ያለብኝ እኔ ነኝ በሚል ተስፋ የቆረጠ ስሜት ለራሷ ዝቅ ያለ ክብርና ዋጋ ሰጥታ ስትናገር ትታያለች፡፡

በሸዋየ ራሷን ዝቅ አድርጎ ማየትና ራስን ማዋረድ የተናደደው አሰሪዋ  "ለምንድን ነው ራስሽን የምታዋርጅው?"/ገጽ፣42/ በማለት ስሜት በተቀላቀለበት ሁኔታ ጥያቄ ሲያቀርቡላት ለቀረበላት ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ አሰሪዋ እንደጥፋት ያልያዘውን፤ አንች አጥፍተሻል ያልተባለችውን ፤"ለመሆኑ በዚህ ወር የሰረሁትን በደል ዘንግተውት ነውን እንዲህ የሚሉኝ?" እኔ አጥፍቻለሁ፡፡ ከፍተኛ በደል ፈጽሜአለሁ፡፡  በሚል የጥፋተኝነት እና የበደለኝነት ስሜት እየተናነቃት ጥፋት ናቸው ያለቻቸውን ነገሮች እየዘረዘረች "ይህን ሁሉ ጥፋት ስፈጽም እርሰዎ አይተው እንዳላዩ ዝም አሉኝ፡፡ ጭጭ አሉኝ" ፡፡ በማለት ላጠፋሁት ጥፋት ቅጣት ይገባኝ ነበር በሚል ስሜት ስትናገር ትታያለች፡፡

ሸዋየ አጠፋሁት ያለችው ጥፋት ሌላ ቤት ፈጽመው ቢሆን ሊደርስባት የሚችለውን ቅጣት ለአሰሪዋ ስትገልጽ እንዲህ ትላለች

ሌሎች ቢሆኑ ኖሮ ምን እንደሚሉኝ ምን እንደሚያደርጉኝ እኔ ነኝ የማውቀው፡፡ ምን ይሉኛል? አንች ደረመናም! የደረመናም ልጅ! አንቺ መናጢ ድሃ የመናጢ ድሃ ልጅ! ቤታቸውን አፍርሽ ተብለሽ ነው የተላክሽ? ይሉና እመቤቲቱ ወርቅ በተገጠገጠበት ጣታቸው ደግመው ደጋግመው በጥፊ ያነባርሩኛል፡፡ ባልየው በበኩሉ ከአምስት መቶ እስከ ስምንት መቶ ብር በሚገመት ቆዳ  ጫማ በካልቾ ልቤን ይሉኛል፡፡ ባልየው እግሩን ካልጣመነው፣ እመቤቲቱ ጣታቸውን  ካልደከማቸው በቀር አይተውኝም ፡፡ አርሰዎ ግን ዝም አሉኝ ፡፡/ገጽ፣42/

ሸዋየ ንጽህነዋን አለመጠበቋ፤ ድሃና የድሃ ልጅ መሆኗ  በሌሎች ዘንድ ዝቅ ብየ እንድታይ አድርጎኛል የሚል እምነት አሳድሮባታል፡፡ ምክንያቱም ማንም ሳይሰድባት

እንዲህ ይሉኝ ነበር የሚለው ትንበያ በውስጧ ያለውን ለራሷ የምትሰጠውን ዋጋ፣ እምነትና አመለካከት ነው የሚያሳየው፡፡

ሽዋየ አድርሻለሁ ላለችው ጥፋት ተገቢውን ቅጣት ባለማግኘቷ የውስጥ ሰላሟን ረፍት ነስቷታል፡፡ እሷ አጥፍቻለሁ የምትለው ጥፋት በአሰሪዋ ዘንድ እንደጥፋት አልታየም ፡፡ አሰሪዋ በሽዋየ ድህነት በማዘን እንዲያውም ሽዋየ እንድትለወጥ በመፈለግ ከደመወዟ ውጭ ብር በመስጠት ፀጉርሽን ተሰሪበት፣ ቀሚስ ግዥበት ብሎ ገንዘብ ሲሰጣት እንዴት ይህን ሁሉ ጥፋት አጥፍቸ ዝም ማለቱ አንሶ ሌል ገንዘብ ይሰጠኛል በማለት ስታለቅስ ማደሯንና ላጠፋሁት ጥፋት ቅጣት ያስፈልገኛል በሚል የጥፋተኝነት ስሜት በተላበሰ ሥነ ልቡና ለአሰሪዋ እንዲህ ትናገራለች፡፡

> ይህ አልበቃ ብሎ ዘጠና ብርዎን መሽልቀው ሠጡኝ፡፡ ፀጉርሽን ተሰሪበት፣ ቀሚስ ግዥበት ማለተዎ! ውነቴን ነው የምለዎ ትናንት ልቤ ተነክቶ እንድችው ሳለቅስ ነው ያደርኩት! እና የሰው ሱሪ አስዘርፌ ቀሚስ ልግዛ!? ቢሆንልኝስ እንደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከገደል ጫፍ በጭንቀላቴ ቆሜ አርባ ዓመት ሙሉ ወየው ወየው ባልኩ! ቢሆንልኝስ እንደ ክርስቶስ ሰምራ በአደፈ ውሃ ውስጥ ተኝቸ አሳውና አለቅቱ በብብቴ በተመላለሰ! ቢሆንልኝስ እንደ ንጉስ ዳዊት አመድ በላየ ነስንሼ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ጦሽ ብየ ባለቀስኩ፡፡ እንዲህ ስትለኝ አመሸች፡፡(በእውቀቱ፣1999፣43)

ሽዋየ ድህነቷንና አለመማሯን መሰረት አድርጋ እኔ ከሰው በታች ነኝ ፡፡ እኔን ሰው እንደሰው አያየኝም በሚል ተስፋ ቆርጣ ራሷን ጥፋተኛና በዳይ አድርጋ ታስባለች፡፡ ኢምንት የሆነውን በተበዳይ ዘንድ እንደበደልና ጥፋት ያልታየውን ራሷ አጉልታ አሳይታለች፡፡ ላደረስኩት በደል ላጠፋሁት ትፋት ቅጣት ይገባኛል የሚል እምነት አድሮባታል ፡፡ የበዳይነት ስሜት ተሰምቷታል፡፡ አዝናለች፡፡ አልቅሳለች፡፡ በራሷ ቅጣት ለመቀበል ተመኝታለች፡፡

ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ሽዋየ በአሰሪዋ ላይ አደረስኩት ላለችው ጥፋት እሷ ከአሰሪዋ ቅጣት አየጠበቀች አሰሪዋ ተጨማሪ ገንዘብ በመስጠት ራሷን እንድትቀይርበት ሲሠጣት ስጦተውን አመስግና ከመቀበል ይልቅ እንዴት ያጠፋሁት አንሶ ተጨማሪ ገንዘብ ይሰጠኛል በሚል ስታለቅስ ትታያለች፡፡ ሽዋየ የጥፋተኝነት ስሜቷ በለቅሶ አልወጣላት ብሎ በራሳቸው ምንም ጥፋት ሳይኖርባቸው ለዓለም ምህረት እንዲሰጥላቸው ፈጣሪያቸውን በሰው ልጅ አቅም ሊደረግ የማይችል ስቃይና መከራ ከተቀበሉት ፃድቃንና ሰማዕታት ከነ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ቤት ንብረታቸውን ትተው ከመነኑት ከነ ክርስቶስ ሰምራ ጋር

የፈጣሪየን ትእዛዝ ተላልፌአለሁ ፈጣሪየን አስቀይሜአለሁ በሚል ፈጣሪው ባጠፋው ጥፋት ይቅርታ እንዲያደርግለት ሱባኤ ከገበው ከንጉስ ከዳዊት ጋር ራሷን እያወዳደረች እንደነሱ ከፍተኛ የሆነ ስቃይና መከራ ለመቀበል ሥትመኝ ትታያለች፡፡

በሌላ በኩል ለራሱ ዝቅተኛ ግምት የሰጠ ሰው  እኔ ከሌሎች ያነስኩ ነኝ ብሎ በውስጡ የዝቅተኝነት ስሜትና እምነት ካደረበት ከኔ የተሻለ ነው  ብሎ ከሚያምንበት ሰው ጋር ከሚበለው ለመብላት ከሚተኛበት ለመተኛት ድፍረት ያጣል፡፡ ይኸ ለኔ አይመጥንም በሚል ራሱን ያዋርዳል፡፡ ለራሱ የወረደ ምግብ ይበላል፡፡ ከወረደ ምኝታ ላይ ይተኛል፡፡

ሸዋየ በአዲስ አበባ በተቀሰቀሰው አመፅ ምክንያት በተመላላሽ ከምትሰራበት ቤት ለማደር ተገዳለች፡፡ እስካሁን ልብስ አጥባ ምግብ አብስላ መሄድ እንጅ ቤት አድራ  ምግብ በልታ አታውቅም ፡፡ ዛሬ ግን ልታድር ስለሆነ ምግብ መብላት መተኛት አለባት ፡፡ ሸዋየ ለአሰሪዋ ራት ዶሮ ሰርታ ቢራ ከፍታ ለሱ ካዘጋጀቸው መብል መብላት ከሱ እኩል መሆን መስሎ ስለታያት ሌላ ድስት ጥዳ ሽሮ ሰትሰራ፣ ከራት በኋላ ወለል ላይ ለመተኛት ስታነጥፍ አሰሪዋ አልጋ ላይ እንድትተኛ ሲጋብዛት "ምድር ስለለመድኩ አልጋ ላይ እንቅልፍ አይወስደኝም" በማለት  አሰሪዋ አልጋ ላይ እሷ ወለል ላይ ሲያድሩ/ ገጽ 44/ እናያለን፡፡

ሸዋየ ለአሰሪዋ ከሰራችው ዶሮ ብትበላ ከተጋበዘችበት አልጋ ብትተኛ ለአሰሪዋ የሚጎድልበት የለም፡፡ ለሷም ከአልገው ወለሉ ተመችቷት አይደለም፡፡ ለራሷ  ከሰጠችው ዝቅተኛ ክብር እና ዋጋ የተነሳ ነው፡፡ ራሷን ከሰው እኩል አለመቁጠሯ ነው፡፡ ከሰው ያነስኩ ነኝ የሚል ስሜትና እምነት ስላደረባት ነው፡፡ የሰው ልጅ ለራሱ ዝቅተኛ ክብርና ዋጋ የሚሰጠው ደግሞ በህይወት የመኖር ተስፋው ሲጨልምበት ፣ የስነልቡና አልባነት ስሜት ሲሰማው፣በአጠቃላይ ከነበረ ማንነቱ ሲወጣና የሞራል ውድቀት ሲያጋጥመው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሥነ ልቡና ሞቱ የሚያመጣው ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "ሥነልቡናዊ ሞት በበእውቀቱ ስዩም እንቅልፍ እና እድሜ ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ የተደረገ ነው፡፡ ጥናቱ በተመረጠው ቴክስት ውስጥ በሚገኙ መውረድና መውጣት፣ማየትና መጋረድ እና መቅረብና መራቅ በሚሉ ሦስት ታሪኮች ውስጥ የሚገኙ ገጸባህሪያት የሚታየው የተመሰቃቀለ ህይወት ፍካሬ ልቡናዊ ንባብ በማድረግ ቢጠና ሥነልቡናዊ ሞትን በመረዳት በኩል ጥሩ ውጤት ያስገኛል፤ጥበቡን በማሳደግ በኩልም አስተዋጽዖ ያበረክታል በሚል አነሳሽ ምክንያት የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በተመረጠው ልብወለድ ሥነ ልቡናዊ ሞት ከሰው ልጅ ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያው እና ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ጋር የቀረበባቸውን ሰብዓዊ ጉዳዮች ተንትኖ ማሳየት የሚል ዋና ዓላማና ቴክስቱ ለሥነልቡና ሞት መከሰት መንስኤዎችን፣ ተጽዕኖዎቹን እና ተጋላጮችን መለየትና መመርመር የሚሉ ንዑሳን ዓላማወችን መሰረት ተድርጎ የተጠና ነው፡፡

ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አላማ ተኮር የልብወለድ አመራረጥን በመጠቀም የሃቲት ትንተናን የመረጃ መተንተኛ ስልት በማድረግ ተጠንቷል፡፡

የስነ ልቡና ሞት መገለጫ ጭብጦች ናቸው በሚል ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ቀቢጸ ተስፋና ለራስ የሚሰጥ ዝቅተኛ ክብር የሚሉት ተለይተው ስለምንነታቸው ከተለያዩ ስራዎች እና ብያኔዎች አኳያ በማየት የጥናቱ የመተንተኛ ጭብጦች በማድረግ ትንታኔው ተሰርቷል፡፡ ጭብጦቹ ከሥነ ልቡና አኳያ ሲታዩ የሰውን ልጅ ስሜትና በሃሪ የሚገልጹ እንደመሆናቸው መጠን በልብወለዱ ውስጥ የሚታዩት ገጸባህሪያት በፍርሃት ፣ በጭንቀት ፣ በቀቢጸ ተስፋ እና ለራስ በሚሰጥ የዝቅተኛ ክብር ስሜት ውስጥ ሆነው ከነበረ የራሳቸው ማንነት እየወጡ ባልነበረ ማንነት እየገቡ ለስደት ፣ ለሞት፣ ለብቸኝነት እና ለሽሽት እየተጋለጡ ከህገ ልቦናና ከማህበረ ልቦና እየተፋቱ ጥፋተኛነት እየተሰማቸው የወደፊት ተስፋቸው ጨለማ ሆኖ ሲታያቸው ተስፋ በመቁረጥ እራሳቸውን ለማጥፋት ሲመኙ፣ ከሰው ልጅ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ጻድቃንና ሰማእታቱ በሚፈተኑበት ፈተና ለመፈተን እንደሚመኙ ጥናቱ ያሳያል ፡፡

ገጸ ባህርያቱ ከመደበኛ ስብእናቸው ወጥተው ባልነበረ ማንነት ውስጥ እንዲገቡና በሥነ ልቡና ሞት ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጓቸው ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ርዕዮተ

አለማዊ  ሁኔታዎች በሚታዩበት ጊዜ በጥናቱ  እንደተረጋገጠው  የኢኮኖሚ ችግር ወይም ጥገኝነት፣ ያልተገባ የልጅነት አስተዳደግ፣ የወቅቱ ያልተረጋጋ ርዕዮተ ዓለም ፣ ጥንቃቄ የጎደለው የሚዲያ አገልግሎት፣ ጥንቃቄ የጎደለው/ ልቅ የሆነ/  የግብረ ስጋ ግንኙነት እና ሞት ዋና ዋናዎቹ  እንደሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ለሥነ ልቡና ሞት ተጋላጭነት አንጻር ሲታይ ሁሉንም ገጸባህሪያት የሚነካካ ሲሆን ደረጀውን በምናይበት ጊዜ ፍርሃት፣ ጭንቀትና ተስፋ ቆራጭነቱ ከሴት ገጸባህሪያት ይልቅ በወንድ ገጸባህሪያት ላይ ከፍ ብሎ ይታያል ፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያት የሚሆነው  በጥናቱ እንደሚታየው   ወንድ ገጸባህሪያቱ የልጅነት አስተዳደጋቸው ሲታይ አንዳንዶቹ  በከፋ ድህነት ውስጥ ያደጉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከልክ ባለፈ የቤተሰብ ቁጥጥር  ለከፋ ሥነ ልቡናዊ ማንነት ተጋልጠው ያደጉ መሆናቸውና  ወቅታዊ ሁኔታቸው ሲታይ ደግሞ ሁሉም በሚባል ደረጃ የሴት ጓደኞቻቸው የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆናቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ለራሷ ዝቅተኛ ክብርና ዋጋ በመስጠት ለከፋ የዝቅተኝነት እና የጥፋተኝነት ስሜት ተጋልጣ የምናገኛት ጥናቱ ላይ በግልጽ እንደተገለጸው በልቦለዱ ውስጥ በአስተኔ ገጸባህሪነት የምናገኛት በልብስ ማጠብና ምግብ ማብሰል በተመላላሽ ሰራተኛነት ተቀጥራ የምትሰራው ሸዋየ ናት፡፡ ለዚህ ችግር የሚያጋልጣት ደግሞ አልተማርኩም የሚለው አስተሳሰቧና ድህነቷ ነው፡፡

በመሁኑም ለሥነልቡና ሞት ተጋላጭ የሆኑት በጥናቱ እንደተረጋገጠው  የአስተዳደግ ችግር ያለባቸውና በኢኮኖሚ ዝቅተኛ ወይም ጥገኛ የምንላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው ማለት አስችሏል፡፡

ሌለው በጥናቱ የታዘብኩት ነገር ቢኖር በአገራችን ባህል በአብዛኘው ጎልቶ የሚታየው ሴቶች ወደ ወንዶች ቤት በመሄድ እንደሚኖሩና የኢኮኖሚ ጥገኛ እንደሚሆኑ ነው ፡፡ ነገር ግን በተመረጠው ቴክስት ውስጥ የሚታየው  በተቃራኒው መንገድ ወንዶች ወደ ሴቶች ቤት በመሄድ እንደሚኖሩ እና  የሴቶቹ  የኢኮኖሚ ጥገኛ ሲሆኑ ይታያልና ይህን ዘርፍ ራሱን ችሎ ቢጠና ጥሩ ነው የሚል በዘርፉ ማጥናት ለሚፈልጉ እጋብዛለሁ፡:

# ዋቢ ጽሑፎች


ማህሌት ጥላሁንና ዳኘ መላኩ (2001) ለአሸናፊነት መገዛት፣አዲስ አበባ፣(ትርጉም)፡፡

በእውቀቱ ስዩም (1999) እንቅልፍ እና እድሜ፣ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

ቴዎድሮስ አለበል (2006)" ልጅነት በማህሌት እና አለንጋና ምስር፤ስነ ልቦናዊ ንባብ"፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ፣የሂውማኒቲስ፤የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክለር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናት ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ (2001) በይነዲሲፕሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፡፡

ኢዩኤል እንደሸው (2010) "ድብቅ ባህሪያት እና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ሥነልቡናዊ ንባብ" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነሑጽፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምለቃ መርሃ ግብር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፡፡

ዛሪሁን አስፋው (1992) የሥነጽሑፍ መሰረታውያን፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የሽጥላ ሞገስ (2001) ያለጭንቀት የመኖር ሚስጢር፣ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993) አማርኛ መዝገበ ቃላት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዳዊት ወንድማገኝ (2009) አለመኖር ፡፡ ፋልኮት ማተሚያ ቤት፡፡ አምስተኛ እትም፡፡

ገብሬ ባይሌ (2010) "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በእሳት ዳር አበቦች፤በኗሪ አልባ ጎጆዎች እና የማለዳ ድባብ የግጥም መድበሎች"፣ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

David L.Shores (2014) Psychoanalysis In Literary study. Publshed By Taylor and Francis, Ltd.

Edel, Leon (1961) Literature and psychology incomparative Literature,Method and Perspective, Newton p, stallknecht and Carbondale ;southern Illinois press.

Fathali M,Moghaddam (---) From ‘psychology in Literature’ to ‘psychology is Literature’. An Exploratio of Boundaries and Relationship, George town University.

Gregory Castle (2007) The Blackwell Guid to Literary Theory. Blackwell Publishing. By Marcono Print Media Pte Ltd.

Julie Rivkin and Michael Ryan (2004) Literary Theory An Antropoiogy. Blackwell Publishing. 2ndEd.

Keith Green and Jill Le Bihan (1996) Critical Theory and practice Acourse book.11 New Fetter Lane, London EC4P 4EE.

Klein, Thompson (2005) Humanities, culture and interdiscilinarity, the changing American Academy.New York, University of New York press.

Michel, Man. S (2008) Historical dictionary of existentialism, USA.Thescarecrow press Inc.

Tyson, Lois. (2006) Critical theory today. A user friendly Guide 2nd ed.New York and London Routledge.

Zekkour, Mohammed (2016) An Existentialist analysis of J.D.salinger’s the catcter in the Rye